# አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና ("በ7ኛ" ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተተኳሪነት)

ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ

የማህበራዊ ሳይንስና  ስነ-ሰብዕ ትምህርት ክፍል

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር

በ

እመቤት እሸቴ

መስከረም /2011 ዓ.ም

ደብረ ብርሃን

ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ

የማህበራዊ ሳይንስና  ስነ-ሰብዕ ትምህርት ክፍል

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር

# አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና ("በ7ኛ" ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተተኳሪነት)

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

በ

እመቤት እሸቴ

አማካሪ

ከበደ ይመር (ዶር.)

መስከረም /2011 ዓ.ም

# ምስጋና

*በቅድሚያ በነገሮች ሁሉ ለረዳኝ ለልዑል እግዚያብሔር ክብር ምስጋና ይግባው፡፡በመቀጠል ለዚህ ጥናት መሳካት ውድ ጊዜያቸውን መስዕዋት አድርገው በየጊዜው ሳይሰለቹ ስህተቶችን በማረም፣የአሰራር ስልቶችን በመጠቆምና በማበረታታት ክትትላቸው ላልተለየኝ አማካሪዎቼ ለዶ/ር ከበደ ይመርና ለአቶ ገደፋው አለልኝ ምስጋናዬ እጅግ የላቀ ነው፡፡ እንዲሁም በዩኒቨርስቲው በነበረኝ ቆይታ በሞራልም ሆነ በሃሳብ እገዛው ላልተለየኝ ለውድ ባለቤቴ ለአቶ ገብረፃድቃን በርሄ ያለኝን ልባዊ ምስጋና ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡*

*ከዚህም በተጨማሪ የመመረቂያ ጽሁፉን ለማከናወን የሚያስፈልገኝን በጀት በመመደብ እገዛ ላደረገልኝ ለደብረ ብርሃን ዩኒቨርስቲ፣በጥናቱ ሂደት አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ በአዲስ አበባ ከተማ በቦሌ ክፍለ ከተማ በህዳሴ፣በጎሮ፣በቦሌ ለሚ፣በምስራቅ በር ቁጥር ሁለት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ለመማሪያ መጽሐፉ አዘጋጆች በመጨረሻም ለስራው መሳካት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ላበረከቱልኝ ግለሰቦች በሙሉ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡*

## ማውጫ

ርዕስ

ገጽ

ምስጋና…………………………………………………………………………………………………………………i

ማውጫ…………………………………………………………………………………………………………………..ii

የአባሪ ማውጫ……………………………………………………………………………………………….v

የሰንጠረዥ ማውጫ……………………………………………………………………………………….vii

አጠቃሎ……………………………………………………………………………………………………………viii

ምዕራፍ አንድ፣መግቢያ………………………………………………………………………………1

1.1. የጥናቱ ዳራ…………………………………………………………………………………………..1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት.................................................................3

1.3. የጥናቱ አላማ………………………………………………………………………………………….4

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ………………………………………………………………………………….5

1.5. የጥናቱ

ወሰን………………………………………………………………………………………5

1.6 የቃላትና ሀረጋት ጽንሰ ሀሳባዊ

ፍቺ……………………………………………………………..6

ምዕራፍ ሁለት፡- የተዛማጅ ጽሁፎች

ቅኝት…………………………………………………………..7

2.1.የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሳሪያዎች

……………………………………………7

2.1.1. የመርሃ ትምህርት

ምንነት………………………………………………………………7

2.1.2.የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ምንነት-

…………………………………………………8

2.1.3.የመማሪያ መጻህፍት

ባህሪያት……………………………………………………………9

2.2. የቋንቋ ክሂሎችና የይዘት

ምንነት…………………………………………………………………10

2.3.የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ

ምንነት…………………………………………………11

2.3.1 .የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረቢያ

ዘዴዎች…………………………………12

2.3.2.የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ

ጠቀሜታ………………………………..13

2.4. አንብቦ  መረዳት ምንድነው?

…………………………………………………………………14

2.4.1. የንባብ ትምህርት

አስፈላጊነት……………………………………………………………15

2.4.2.አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ………………………………………………………16
2.4.3. አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ምንነትና ሲዘጋጁ ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች………………………………………………………………….18
2.5. የጽህፈት ክሂል ምንነት……………………………………………………………………………20
2.6. የጽህፈት ትምህርት አስፈላጊነት……………………………………………………………….21
2.7.የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ትስስር………………………………………………………………21
2.7.1.አንብቦ መረዳትንና መጻፍን ክሂል በቅንጅት የማቅረብ አስፈላጊነት…………………22
2.7.2. አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማዳበር የሚረዱ ብልሃቶች…….23
2.8. የቀደምት ስራዎች ቅኝት ………………………………………………………………………..26
ምዕራፍ ሦስት፣ የአጠናን ዘዴ ………………………………………………………………..30
3.1. የጥናቱ ንድፍ ……………………………………………………………………………………30
3.2. የጥናቱ የመረጃ ምንጮች……………………………………………………………………….30
3.3. የናሙና አመራረጥ………………………………………………………………………………...31
3.3.1.የጥናቱ ክልል አመራረጥ……………………………………………………………….31

3.3.2. የትምህርት ቤቶች ናሙና

አመራረጥ……………………………………………31

3.3.3. የክፍል ደረጃ

አመራረጥ……………………………………………………..31

3.3.4. የመምህራን ናሙና

አመራረጥ…………………………………………………..32

3.3.5.የመጽሀፉ አዘጋጆች

አመራረጥ……………………………………………………32

3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ

መሳሪያ………………………………………………………………….32

3.4.1.ሰነድ

ፍተሻ……………………………………………………………………………32

3.4.2. የጽሁፍ

መጠይቅ…………………………………………………………………….33

3.4.3.

ምልከታ………………………………………………………………………………3

3

3.4.4. ቃለ

መጠይቅ……………………………………………………………………………34

3.5. የመረጃ አተናተን

ዘዴ………………………………………………………………………34

3.5.1.የመረጃ አለያየትና ለትንተና ዝግጁ

ማድረግ…………………………………………………34

3.5.2 የመተንተኛ

ስልት……………………………………………………………………..35

3.5.3.የትንተናው
ትኩረት…………………………………………………………………………………35

ምዕራፍ አራት፣የመረጃ ትንተና እና የውጤት
ማብራሪያ……………………………………………..36

4.1 የመረጃ ትንተና-
………………………………………………………………………………………36

4.1.1.የመጽሐፉ አጠቃላይ
ዳራ…………………………………………………………………36

4.1.2. የተተኳሪ መምህራን ዳራዊ
መረጃ……………………………………………………………..37

4.1.3. በመማሪያ መጽሐፉ የተካተቱ የንባብ ክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች

አቀራረብ…………………………………………………………………………………
.38

4.1.4.አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አቀራረብ
ትንተና………………………………………38

4.1.5. አንብቦ የመረዳት ትምህርት የይዘቶች አቀራረብ
ትንተና……………………………46

4.1.6. በመጽሀፉ ውስጥአንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ

አቀራረብ…………………………………………………………………………………...48

4.1.7. አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት ማስተማሪያ እንዲሆኑ

የተዘጋጁት መልመጃዎች
ግምገማ……………………………………………………………..55

4.1.8.የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ለአንብቦ መረዳትና ለመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ

አቀራረብ ያላቸው

እገዛ……………………………………………………………………………58

4.1.8.1.የመርሃ ትምህርቱ አጭር መግለጫ

……………………………………………………58

4.1.9. መምህራን ስለ ማንበብና መጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ

ያላቸው

ግንዛቤ……………………………………………………………………………………6
3

4.1.9.1.የመምህራኑ የማንበብና መጻፍ ክሂሎች ክሂሎች

አቀራረብ………………………64

4.1.10.መምህራን አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸው

ብልሃቶችና

ስልቶች……………………………………………………………………………………6
8

4.2. የውጤት

ማብራሪያ……………………………………………………………………………70

ምዕራፍ አምስት፣ማጠቃለያና

አስተያየት……………………………………………………73

5.1.ማጠቃለያ…………………………………………………………………………
……………73

5.2.አስተያየት

……………………………………………………………………………………74

ዋቢ ጽሑፎች
……………………………………………………………………………………………..
76

አባሪዎች…………………………………………………………………………………
…………………81

አባሪ "አንድ"   ቅድመ ንባብ
ጥያቄዎች………………………………………………………………..81

አባሪ "ሁለት" ንባብ ሂደት ጥያቄዎች (ክንውኖች)
…………………………………………………89

አባሪ "ሶስት" ድህረንባብ (አንብቦ መረዳት)
ጥያቄዎች……………………………………………92

አባሪ" አራት"   የጽሁፍ
መጠይቅ……………………………………………………………… …….114
አባሪ" አምስት" ምልከታ
…………………………………………………………………………… 118

አባሪ "ስድስት"
ቃለመጠይቅ…………………………………………………………… ……..121

## የሰንጠረዥ ማውጫ

የሰንጠረዥ መለያ ቁጥር አርዕስት

ገጽ ሰንጠረዥ ፡-1. የጽሁፍ መጠይቅ ስለሞሉ መምህራን የተገኘ አጠቃላይ መረጃ................37

ሰንጠረዥ ፡- 2. በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ባህርይ............40

ሰንጠረዥ ፡- 3. ለአንብቦ መረዳትና ለመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ እንዲሆኑ የተዘጋጁት መልመጃዎች የትምህርቱን አላማ የማሳካት ብቃታቸው..............................43

ሰንጠረዥ ፡- 4. በመጽሀፉ ውስጥ የሚገኙ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች መመሪያ

አቀራረብ........................................................................................45

ሰንጠረዥ ፡- 5. የአንብቦመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች የተማሪዎችን ልዩልዩ ሁኔታዎችን ትኩረት ያደረጉ

ስለመሆናቸው.................................................................................47

ሰንጠረዥ ፡- 6. በመጽሀፉ ውስጥ የሚገኙ ጠቅላላ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች............49

ሰንጠረዥ፡ -7. መልመጃዎቹ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅ ለማስተማር ያላቸው

እገዛ........................................................................................53

ሰንጠረዥ፡- 8. የክፍለ ጊዜያቱ ይዘቶች አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀት ያላቸውን እገዛ ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ መረጃ......................64

ሰንጠረዥ ፡- 9. የመምህራንን የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ለማወቅ

ከምልከታ የተገኘ
መረጃ..........................................................................65

ሰንጠረዥ፡-10. መምህራን የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶችና ስልቶችን ለማወቅ ከምልከታ
የተገኘ
መረጃ.................................................................................................67

## አጠቃሎ (Abstract)

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የነበረው በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብን መተንተን ነው፡፡ይህን ዓላማ ለማሳካትም በሰነድ ፍተሻ፣በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የጥናቱን መረጃዎች ለመተንተን ገላጭ የመረጃ መተንተኛ ስልት በተግባር ላይ ውሏል፡፡ የተሰበሰበው መረጃ በአግባቡ ተደራጅቶ ትንተና ተደርጎበታል፡፡ከመረጃዎቹ የተገኙት ውጤቶች የሚያመለክቱት አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን የሚመለከቱ ይዘቶች አቀራረብ ለመማር ማስተማሩ ሂደትም ሆነ ለተማሪዎቹ ልምምድ አመቺ መሆናቸውን፤ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ የተማሪዎችን ደረጃ፣ዕድሜና ችሎታ እንዲሁም ዳራዊ እውቀታቸውን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ መሆናቸውን፤የመማሪያ መጽሀፉ አቀራረብ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች በተቀናጀ መልኩ እንደተዘጋጁና የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማስተማር እገዛ እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡በአንጻሩ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን የሚመለከቱ መልመጃዎች አቀራረብ ለትምህርቱ ከተመደበው ሰዓት ጋር ያለመጣጣም ችግሮች መኖራቸውን፣አልፎ አልፎ ስለ መልመጃዎቹ አሰራር ሙሉ መረጃ የማይሰጡ መመሪያዎች በመጽሀፉ ውስጥ መካተታቸውን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ከዚህም በተጨማሪ አብዛኛዎቹ መምህራን ስለማንበብና መጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ እውቀቱ ቢኖራቸውም ትኩረት ሰጥቶ አቀናጅቶ በማቅረብ ረገድ አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡በአጠቃላይ በመጽሐፉ ውስጥ በሚገኙ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች

አቀራረብ ላይና በመምህራን ቅንጅታዊ አተገባበር ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ ስልቶች በመፍትሄ ሀሳቦች ስር ተጠቁመዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ ፤ መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣የጥናቱ አላማ፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣የጥናቱ ወሰንና የቃላትና ሀረጋት ጽንሰ ሃሳቦች አጠቃቀም ብያኔዎች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎች እየተማሩት ባለው ቋንቋ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ብቻ ሳይሆን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ብቃት በማዳበር እንዲግባቡበት ማድረግ ነው፡፡ይህን ለማድረግ ደግሞ የመማሪያ መሳሪያዎች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ስለ ቋንቋ ትምህርት ሲነሳ ቁልፉን ቦታ የሚይዙት የመማሪያ መሳሪያዎች መሆናቸውን በተለያዩ ጊዜያት በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ጥናታቸውን ያደረጉ ተመራማሪዎች Grant (1987)፣ Cunnings worth (1995) እና Richads (2001)ገልጸዋል፡፡

የማስተማሪያ መሳሪያዎች የምንላቸው ስርዓተ ትምህርት፣መርሃ ትምህርት፣የተማሪው መማሪያ መጽሀፍና የመምህሩን መምሪያ ያጠቃልላል፡፡ እነዚህም መሳሪያዎች የቋንቋን ትምህርት ሂደት የተሳካ እንዲሆን የሚያግዙ የትምህርት መሳሪያዎች ናቸው፡፡ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ዝግጅት በተመለከተ ምሁራን እንደሚከተለው አብራርተዋል፡፡

ተስፋዬ (1981፡89) "የቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች የሚባሉት ሆን ተብለው ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተዘጋጁት ወይም የተመደቡት ብቻ ናቸው፡፡ ሆን ተብለው ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተዘጋጁት ለአንድ የተወሰነ ክፍል እንዲያገለግሉ ስርዓተ ትምህርቱን

ወይም የክፍሉ ተማሪዎች ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ችሎታ መሰረት በማድረግ ለማስተማሪያ ተብለው የሚዘጋጁ ናቸው" በማለት ገልጸዋል፡፡እንዲሁም Richard and Rodgers (1986፡25) በበኩላቸው የቋንቋ ማስተማሪያ መጻህፍት የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደትን የሚመሩ፣የቋንቋ ትምህርቱን መነሻና መድረሻ የሚጠቁሙ፣የተለያዩ ይዘቶችን በምሳሌ አስደግፈው የሚያቀርቡ፣መልመጃዎችንና የተለያዩ ተግባራትን በማቅረብ ተማሪዎችን እንዲለማመዱ የሚያደርጉ አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሂደት እንቅስቃሴ መረጃ የሚሰጡ በመሆናቸው በጥንቃቄ ሊዘጋጁ እንደሚገባቸው ገልጸዋል፡፡

ቋንቋን ለማስተማር ሲታቀድ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችና ስልቶች አብረው ይነሳሉ፡፡ ይህም እንደ ትምህርቱ ዓላማና ግብ እንዲሁም በዘመኑ እንደነበረው የቋንቋ ፍልስፍና መሰረት የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች በተለያዩ ምሁራን ሲነደፉ ይታያሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ የሚያግዘው ተግባቦታዊ አቀራረብ የቋንቋ ትምህርት በሚፈለገው ሁኔታ ግብ እንዲመታ ያግዛሉ ተብለው ከተጠቀሱት አቀራረቦች ውስጥ አንዱ ነው (Little Wood 1981:93)::ተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ እንዲያጎለብቱ ለማድረግ በጥንቃቄ የታቀደ የቋንቋ ትምህርት ያስፈልጋል፡፡ይህም የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ በአግባቡ ማስተማር የሚያስችል የአቀራረብ ስልት መርጦ ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል፡፡

በቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚቀርቡት ይዘቶች ከሚኖራቸው ዋና ዋና አላማዎች መካከል አንዱ የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎት ብቃት ማጎልበት ነው፡፡በመሆኑም ክሂሎች እንደ አይነታቸው በተገቢ መንገድ ተቀናጅተው ለተማሪዎቹ ተስማሚ በሆነ መንገድ መቅረብ እንዳለባቸው (Cunnings Worth 1995:74) አስረድተዋል::

በቋንቋ ትምህርት ከሚቀረፁት ዓበይት ዓላማዎች ውስጥ አንዱ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማዳበርና ማጎልበት ሲሆን ከቅርብ አመታት ወዲህ በቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ከፍተኛ ትኩረት እየተደረገ መምጣቱን (Byrne 1981:107) ገልጸዋል፡፡የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነትን አስመልክተው ምሁራን እንደሚከተለው ገልጸዋል::

የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ማለት በቋንቋ ክሂሎች አቀራረብ ወቅት አንዱ ክሂል ሲነሳ ሌላው ክሂል ተከትሎ የሚነሳ በመሆኑ ተያያዥነት ያላቸውን የቋንቋ ክሂሎች በማቀናጀት ማስተማርን የሚመለከት ነው (Byrne1981:108) እና (McDonugh and Shaw

1992:201):: ከምሁራኑ ሃሳብ እንደምንረዳው የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ማለት በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ክሂሎችን በማጣመር ወይም አንዱ ሲነሳ ሌሎቹ አብረው እንዲነሱ በማድረግ እንዲተገበሩ የሚደረግበት ዘዴ ነው፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው ዓላማዎች መካከል አንዱ "የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን ማዳበር" የሚል ነው፡፡ ይህ አላማ ከግብ ሊደርስ የሚችለው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ችሎታን ያዳብራሉ ተብለው የሚካተቱ ይዘቶች በተገቢው መንገድ ተቀናጅተው ሲቀርቡ ነው፡፡ተማሪዎች በታቀደው ይዘት ተጠቅመው በተደጋጋሚ መለማመድ ሲችሉ የታሰበው ግብ ሊገኝ ይችላል፡፡ ስለዚህ በማንበብ እና በመጻፍ ክሂሎች ቅንጅት ላይ ጥናት ማድረግ እና አቀራረቡ እንዲሻሻል ማድረግ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው፡፡

ሞገስ(1999) ባደረጉት ጥናት Beerdgew(2003)ን ዋቢ አድርገው እንደገለጹት "በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ዓመታት ማንበብና መጻፍ በሙያ ተኮር (Subject Centered) ስርዓተ ትምህርት አቀራረብ እንደተለያዩ አላባዊያን ተደርገው ይወሰዱ ነበር፡፡ በዚህም በማንበብና በመጻፍ ትስስር ላይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ የተለመደ አልነበረም፡፡ "በተጨማሪም "በ1970ዎቹና በ1980ዎቹ አመታት ላይ ግን በሁለቱ ክሂሎች መካከል ያለውን ዝምድና ለማጥናት ጥረት ተደርጓል፡፡ምርምሮቹ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች በውህደት ከቀረቡና በልምምድ ከተተገበሩ ለክሂሎቹ መጎልበት ጥሩ ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል፡፡"እንዲሁም በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች Harp, etal.(1996) እና Ruddel (1997) እንደገለጹት በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች መካከል የጠበቀ ትስስር መኖሩንና በውህደት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ የተመራማሪዎቹ ሃሳብ እንደሚያመለክተው የዚህ ጥናት አቅራቢም ከተሞክሮዋ እንደተገነዘበችው ለክሂሎቹ አለማደግ እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶች ቅንጅት አለመኖር ነው፡፡

### 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚዋ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ለስድስት አመታት ያህል አገልግላለች፡፡በነዚህ ጊዜያት የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታ ስትመለከት ችግር እንዳለበት ታዝባለች፡፡ በሌላ በኩል በአንብቦ መረዳትና

በመጻፍ ክሂል ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ሞገስ (1999)እና እሸቱ (2003) ክለሳ እንደሚያሳየው፣የሁለቱ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ችግር እንዳለበት አመልክተዋል፡፡ ከችግሮች መካከል ለአብነት ያህል አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ትግበራ ተማሪውን የሚያበረታታ ሆኖ አለመቅረቡ፣በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተካተቱት መልመጃዎች ዓላማን ለማሳካት የሚያስችሉ አለመሆናቸውን በጥናታቸው ውጤት ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም የዚህ ጥናት አቅራቢ በ2008 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው "በ7ኛ" ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረበው አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል የይዘት ቅንጅታዊ አቀራረብ ምን ይመስላል?እንድትል አድርጓታል፡፡ምክንያቱም የመማሪያ መጻህፍት በዝግጅትም ሆነ አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት መገምገም ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች የተገለጹትን መሪ ሀሳቦች ከግብ ለማድረስ ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመረምራል፡፡

- በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት ይዘቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ ቀርበዋል ወይ?
- በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ ምን ይመስላል?
- የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን እንዴት እንዳቀረቧቸውና መምህራን ክሂሎችን አቀናጅተው እንዲያቀርቡ እገዛ ያደርጉላቸዋል? ወይስ አያደርጉላቸውም?
- መምህራን ስለማንበብና መጻፍ ክሂሎች ታስቦበትና ታቅዶበት ለሚከናወን ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል?
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅተው ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ምን ምን ናቸው? የሚሉት ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡

## 1.3. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል የክፍል ደረጃ ተዘጋጅቶ በ2008ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው "የ7ኛ" ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምን

እንደሚመስል መመርመር ነው፡፡ ይህንን አብይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ተካተዋል፡፡

- በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት ይዘቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ መቅረባቸውን ወይም አለመቅረባቸውን መመርመር ፣
- በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምን እንደሚመስል መመርመር፣
- የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን እንዴት እንዳቀረቧቸውና መምህራን ክሂሎችን አቀናጅተው እንዲያቀርቡ ድጋፍ ማድረግ አለማድረጋቸውን መመርመር
- መምህራን ስለማንበብና መጻፍ ክሂሎች ታስቦበትና ታቅዶበት ለሚከናወን ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸውን ግንዛቤ ነቅሶ ማውጣት፣

- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን አቀናጅተው ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ምን እንደሚመስሉ መመርመር የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በአንብቦ መረዳት እና በመጻፍ ክሂሎች መካከል ያለውን ቅንጅታዊ አቀራረብ መገምገም እንደሆነ ቀደም ብሎ በዓላማው ላይ ተገልጿል፡፡ስለሆነም ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡

- ለመምህራን፡-በመጻህፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን የሚመለከቱት ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ ምን እንደሚመስል ስለሚገመግም መምህራን የሚያስተምሩበትን መማሪያ መጻሐፍ እንዲገነዘቡት ስለሚያስችል ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

➢ ለመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች፡-ጥናቱ ክሂሎች በምን መልኩ ተቀናጅተው መቅረብ እንዳለባቸው ስለሚያጠና ምናልባትም ለመማሪያ መሳሪያ አዘጋጆች የመረጃ ምንጭ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

➢ ለጥናት አድራጊዎች፡- ወደ ፊት ይህን መሰል ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ ጥናት ለሚያደርጉ አጥኝዎች እንደመነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.5.የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታ አኳያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ በሚገኙ በህዳሴ፣በጎሮ፣በቦሌ ለሚና በምስራቅ ቁጥር ሁለት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የተገደበ ነው፡፡ ከይዘት አንጻር ሲታይ በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በ2007ዓ.ም ታትሞ በ2008ዓ.ም በስራ ላይ በዋለው "የ7ኛ" ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ያተኩራል፡፡ ስለሆነም ሌሎቹን የቋንቋ ክሂሎች በቀጥታ አይመለከትም፡፡

## 1.6. የቃላትና ሀረጋት ጽንሰ ሀሳባዊ ፍቺ

❖ ቅንጅታዊ አቀራረብ:- የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ማለትም በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ክሂሎችን በማጣመር አንዱ ሲነሳ ሌሎቹ አብረው እንዲነሱ ወይም እንዲተገበሩ የሚደረግበት ዘዴ ነው(Byren 1981)፡፡

❖ አንብቦ የመረዳት ክሂል:- የአንድን ጽሁፍ መልዕክት የመገንዘብ ሂደት ነው (Green wood 1981)፡፡

❖ የመጻፍ ክሂል፡- መጻፍ የሀሳብ አቀነባበርን፣የሃሳብ ፍሰትን፣የቃላት አመራረጥን እና የአገላለጽ ስልትን የሚጠይቅ የቋንቋ ክሂል ነው (Byren 1988)፡፡

❖ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ:-ሁለቱን ክሂሎች በትስስራቸው መሰረት አቀናጅቶ የማቅረብ ሂደት ነው(Ruddel 1997)፡፡

# ምዕራፍ ሁለት ፤የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

ይህ ክፍል ጥናቱ የሚካሄድበትን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክቶ የተለያዩ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች የሚዳሰስበት ነው፡፡በዚህም መሰረት ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጉዳዮች በዝርዝር የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የቋንቋ መማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ምንነት፣የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ባህሪያት፣ የቋንቋ ክሂሎች የይዘት ምንነት፣የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነት፣ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ዓላማ፣ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ጠቀሜታ፣አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት የማስተማር አስፈላጊነት፣ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በማቀናጀት የማስተማሪያ ዘዴዎችና የቀደምት ስራዎች ቅኝት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 2.1.የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሳሪያዎች

የማስተማሪያ መሳሪያዎች የቋንቋ ትምህርት የተሳካ እንዲሆን አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ እነዚህም ስርዓተ ትምህርት፣መርሃ ትምህርት፣የተማሪውን መማሪያ መጻህፍትና የመምህሩን መምሪያ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ስለመሳሪያዎቹ ምንነት፣ባህሪያትና ዓይነቶች እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 2.1.1. የመርሃ ትምህርት ምንነት

መርሃ ትምህርት ከስርዓተ ትምህርት ጠበብ ያለ፣የትምህርቱን አጠቃላይና ዝርዝር አላማዎችን በግልጽ የሚያሳይ የማስተማሪያ ዘዴዎችን የሚጠቁም፣የምዘና ዘዴዎችንና መርጃ መሳሪያዎችን የሚያሳይ ሰነድ ነው(Cunnings Worth1984:22):: እንዲሁም Dubin እና Olshtain(1986:37) መርሃ ትምህርት ስርዓተ ትምህርትን መሰረት አድርጎ የሚዋቀር የስርዓተ ትምህርት ፍልስፍና እውን የሚሆንበት ሰነድ ነው፡፡መርሃ ትምህርት የመማር ማስተማር ተግባር ተከታታይነት ባለው ሁኔታ የሚተገበርበት፣የትምህርቱ ዓላማዎች ግብ የሚመቱበት ሁኔታ የሚመቻችበት ዝርዝር የትምህርት እቅድን የያዘ ሰነድ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Widdson (1990:129) የቋንቋ መርሃ ትምህርት ለመምህራን እንደመመሪያ ሆኖ እንደሚያገለግላቸው የተለያዩ ስነ ዘዴዎችን በማሳየት የመማር ማስተማር ሂደትን እንዴት እንደሚተገብሩና የማስተማር ክንውኖችን እንዲያጎለብቱ የሚጠቁም መሆኑን ያብራራሉ፡፡

በአጠቃላይ ከምሁራን ሀሳብ እንደምንረዳው መርሃ ትምህርት ማለት ከስርዓተ ትምህርት ጠበብ ያለ፣ ስርዓተ ትምህርትን መሰረት አድርጎ የሚዋቀር፣ የትምህርቱን አጠቃላይና ዝርዝር አላማዎችን በግልጽ የሚያሳይ የማስተማሪያ ዘዴዎችን የሚጠቁም፣የምዘና ዘዴዎችንና መርጃ መሳሪያዎችን የያዘ ሰነድ መሆኑን ነው፡፡

መርሃ ትምህርት በሚቀረጽበት ጊዜ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ምሁራን እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡ዓለም (1995) አገላለጽ በመርሃ ትምህርት ዝግጅት ወቅት የሚከተሉትን ነጥቦች ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ ምሁራኑ ይገልጻሉ፡፡

- ❖ ተማሪ አሳታፊ የሆኑ ክንውኖችን ማካተት
- ❖ክንውኖች በተማሪ ፍላጎትና ደረጃ ላይ መመስረታቸው
- ❖ክሂሎች ተቀናጅተው መካተታቸው

ክንውኖች በተማሪዎች ሊተገበሩ የሚችሉ መሆናቸው የሚሉት ናቸው፡፡ከዚህ በመቀጠል የማስተማሪያ መሳሪያዎች ከሆኑት መካከል ስለመምህሩ መምሪያ ምንነት እንመለከታለን፡፡

የመምህሩ መምሪያ መምህሩ የተማሪውን የመማሪያ መጽሀፍ እንዴት ማስተማር እንዳለበት አቅጣጫ የሚያመለክት መሳሪያ ነው፡፡ የተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ደግሞ ተማሪዎች የመማር ማስተማር ሂደቱን እንዲከታተሉበት የሚረዳና የተለያዩ ተግባራትን እንዲሰሩ የሚያችል የማስተማሪያ መሳሪያ ነው፡፡ Harmer (1991፡257) አገላለጽ የቋንቋ ማስተማሪያ መጻሀፍት የመማር ማስተማር ሂደትን የሚመሩ፣የቋንቋ ትምህርትን መነሻና መድረሻ የሚያመላክቱ፣የተለያዩ ይዘቶችን በምሳሌ በማስደገፍ የሚያቀርቡና የተለያዩ ተግባራትን በማቅረብ ተማሪዎችን እንዲለማመዱ የሚያደርጉ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

## 2.1.2. የቋንቋ መማሪያ መጻሀፍት ምንነት

በአንድ አገር ውስጥ የተቀረፀውን ስርዓተ ትምህርት አጠቃላይ የትምህርት ግብ ከዳር ለማድረስ ከሚያስፈልጉ መሳሪያዎች አንዱና ዋነኛው መማሪያ መጽሀፍ ነው፡፡ስለ መማሪያ መጽሀፍ ምንነት የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ ለአብነትም ያህል የሚከተሉትን እንመለከታለን፡፡

Richads (2001:254) ሲገልጹ መማሪያ መጻሀፍት የቋንቋ ትምህርት መርሐግብርን ለማሳካት የተለያዩ አቅጣጫዎችን በመጠቀም የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ይህንን ሀሳብ በማጠናከር Ur (2006፡183) የመማሪያ መጽሀፍ የሚባለው የአንድ ትምህርት አይነት አጠቃላይ ይዘቶችን አካቶ የያዘ ጥራዝ ነው፡፡ ይህም ጥራዝ መምህሩም ሆነ ተማሪዎቹ ሊከተሉት የሚገባውን መርህ የሚጠቁምና ለቋንቋ ትምህርት መሰረት የሆነ የመማሪያ እና የማስተማሪያ መሳሪያ ነው በማለት አብራርተዋል፡፡ በተመሳሳይ Cunnings Worth (1995) እንደገለጹት መማሪያ መጻሀፍት በስነ-ትምህርት ባለሙያዎች ተመርጠውና ለአንድ የክፍል ደረጃ ይመጥናሉ ተብለው የተዘጋጁ የትምህርት ይዘቶችን ወይም የእውቀት ዘርፎችን አካተው የያዙ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረቡት የምሁራን ሀሳብ እንደምንረዳው የቋንቋ መማሪያ መጻሀፍት የትምህርቱን ሂደት የሚመሩ፣ለመምህሩም ሆነ ለተማሪው ጠቃሚ የተግባር መመሪያ በመሆናቸው ከተለያዩ የቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ጥቅም አንጻር ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዙ መሆናቸውን ነው፡፡

## 2.1.3. የመማሪያ መጻሀፍት ባህሪያት

ከቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች መካከል አንዱና ዋነኛው የመማሪያ መጽሀፍ መሆኑን ቀደም ሲል ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ከዚህ በመቀጠል ስለ መማሪያ መጻህፍት ባህሪያት የምሁራንን ሀሳብ እንመለከታለን፡፡

ለተወሰኑ የክፍል ደረጃዎች መማሪያ እንዲሆኑ ታስበውና ሆን ተብለው የሚዘጋጁ መጻህፍት በሚዘጋጁበት ወቅት እውነተኛነት፣ግልጸኝነት፣ተለጣጣቂነት፣ተግባራዊነት፣ተገቢነት የሚሉትን ባህሪያት ማሟላት ይጠበቅባቸዋል (ተስፋዬ፡1981)፡፡ ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዳቸውን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

**እውነተኝነት፡-**ለትምህርት የቀረበው የቋንቋ አካል እውነት የቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ የሚለው መሆን አለመሆኑን የሚዳኝበት ነው፡፡ተማሪው እንዲማር እንዲለማመደው የሚያደርገው የቋንቋ አካል ቋንቋውን ይበልጥ የሚያሳውቅ፣በቋንቋው ይበልጥ የባለቤትነት ስሜት የሚያሳድር መሆን አለበት፡፡

**ግልጸኝነት፡-**የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ የያዟቸው ትምህርት ጉዳዮች መምህሩ እንዲያስተምር ተማሪው እንዲማር ለማገዝ በግልጽ መስፈር አለመስፈራቸው የሚመዘንበት ነው፡፡ግንዛቤ እንዲኖራቸው የቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ጉዳዮች ምንነታቸው በማያሻማ ስልት እንዲቀርብ ያስፈልጋል፡፡

**ተለጣጣቂነት፡-**በአንዱ መጽሀፍ ልዩ ልዩ ምዕራፎች መካከልም ሆነ ለተለያዩ ክፍሎች በተዘጋጁ መጻህፍት መካከል ተለጣጣቂነት የቅደም ተከተል ጉዳይ ነው፡፡ተማሪው ቀጥሎ የሚደርስበት ምዕራፍ ካለፈው የተለየና ያደገ መሆኑን የሚደግም ከሆነ ግን እድገት ወይም አዲስነት የለበትምና መሰላቸት ይከተላል፡፡

**ተግባራዊነት፡-**ተግባራዊነት መምህሩ እንዲያስተምር ተማሪውም እንዲማር የሚያግዝ መሳሪያ የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡የተዘጋጀው የማስተማሪያ መሳሪያ የያዘው የትምህርት ይዘት በተማሪው ተግባራዊ የሚደረግ መሆን ይኖርበታል፡፡

**ተገቢነት፡-**የተገቢነት ጉዳይ የማስተማሪያው መሳሪያ በይዘቱ ለተማሪዎች ደረጃ ፣ለተማሪዎች እድሜ ለተማሪዎች ችሎታና ለተማሪዎች ፍላጎት የሚመጥን መሆን እንዳለበት የሚያመለክት ነው፡፡ ለትምህርቱ ሂደትም ቢሆን የማስተማሪያ መሳሪያው ብቃት የሚታየው በዚሁ ዘርፍ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መገንዘብ የሚቻለው በየትኛውም የክፍል ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች መማሪያ እንዲሆኑ የሚዘጋጁት መጻህፍት ሊያሟላቸው የሚገቡ ባህሪያት መኖራቸውን ነው፡፡ይህን ከቋንቋ ትምህርት አኳያ ስንመለከት በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡ ነገሮች ተናጋሪው ህብረተሰብ ዘንድ እውነትነታቸው የተረጋገጠ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ከዚህ ጎን ለጎን ይዘቶቹ ለመማር ማስተማር ሂደት አመቺ መሆናቸውንና በግልጽ ቋንቋ መቅረባቸውም አብሮ ይታያል፡፡ከእነዚህ በተጨማሪ መጽሀፉ የያዛቸው ትምህርታዊ ክንውኖች ከተማሪዎች ልዩ ልዩ ሁኔታዎች አኳያ የተዘጋጁና ዳራቸውን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል::

እነዚህ መሳሪያዎች በሚዘጋጁበት ወቅት የተለያዩ ነገሮች ላይ ትኩረት ያደረጉ ቢሆንም በዚህ ጥናት ማየት የተፈለገው ለአንብቦ መረዳትና ለመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ የሰጡትን ትኩረት፣ የይዘት ተገቢነትና የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን አቀናጅቶ ለማቅረብ ያላቸውን አስተዋጽኦ ነው፡፡

## 2.2.የቋንቋ ክሂሎችና የይዘት ምንነት

የቋንቋ ትምህርት አራት ክሂሎችና ሁለት የእውቀት ዘርፎች አሉት፡፡የአራቱ ክሂሎች ዓብይ ትኩረት ቋንቋውን የሚማሩ ተማሪዎች ክሂሎቹን በተገቢ ሁኔታ ተለማምደው በአስፈላጊ ጊዜና ቦታ መግባባት እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡

የአራቱን የቋንቋ ክሂሎች የይዘት ምንነት አስመልክተው Widdowson (1978:57) ሲገልጹ ማዳመጥና መናገር መልዕክትን ወይም ሃሳብን በቃል የመቀበልና የማቀበያ ዘዴዎች ሲሆኑ ማንበብና መጻፍ ደግሞ በሚታዩ ምልክቶች አማካኝነት መልዕክትን የመቀበያና የማስተላለፊያ ስልቶች ናቸው በማለት አስረድተዋል፡፡

በማንኛውም ደረጃ የሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች በሚገባ ተክነው በትክክል መገልገል እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡እንዲሁም ተማሪዎቹ የስነ ጽሁፍና የስነ ልሳን እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ሌላው የቋንቋ ትምህርት አላማ ነው፡፡ ከቋንቋ ትምህርት አላማዎች መካከል ቀዳሚው የቋንቋ ክሂሎችን ብቃት ማሳደግ መሆኑ ቀደም ሲል ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ቋንቋን የመማር ማስተማር ሂደት ሲታሰብ የተለያዩ

የማስተማሪያ ዘዴዎችና ስልቶች አብረው ይነሳሉ፡፡የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ግቡን ሊመታ የሚችለውም አራቱ ክሂሎች በተገቢ ሁኔታ ተቀናጅተው መቅረብ ሲችሉ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ በመሆኑ የቅንጅታዊ አቀራረብን ምንነት፣ ክሂሎችን በቅንጅት የማስተማር ጠቀሜታን፣የማስተማሪያ ስልቶችን ከዚህ በመቀጠል በዝርዝር እንደሚከተለው ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

## 2.3.የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነት

ቋንቋን የመማር ማስተማር ሂደት ሲታሰብ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችና ስልቶች አብረው ይነሳሉ፡፡ለምሳሌ የቋንቋ ትምህርት በሚፈለገው ደረጃ ግቡን እንዲመታ ያግዛሉ ተብለው ከሚጠቀሱት አቀራረቦች ውስጥ አንዱ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረብ ነው Little Wood (1981:93)፡፡

በቋንቋ ትምህርት ከሚቀረፁት ዓበይት ዓላማዎች ውስጥ አንዱ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማዳበርና ማጎልበት እንደመሆኑ መጠን ከቅርብ አመታት ወዲህ በቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ከፍተኛ ትኩረት እየተደረገ መምጣቱን Byrne (1981:107) ገልጸዋል፡፡የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነትን አስመልክተው ምሁራን እንደሚከተለው ገልጸዋል::

እውናዊውን የቋንቋ አጠቃቀም ስንመለከት ንግግር በማዳመጥ ጽህፈት በንባብ ወዘተ የሚታገዝ ነው፡፡በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት አላማም ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ አጠቃቀም በትክክለኛው መንገድ እንዲጠቀሙ ማስቻል በመሆኑ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረቡ ተግባቦታዊ ብቃትን የማጎልበት አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው (Gilbert: 1982)::

የቋንቋ ክሂሎችን አቀራረብ ስናስብ በአንድ መማሪያ ክፍል አንድን የቋንቋ ክሂል ነጥሎ ማቅረቡ አስቸጋሪ ነው፡፡የንባብ ክሂልን ለማስተማር ሲታለም የመጻፍ ክሂል አብሮ መምጣቱ አይቀርም፡፡ እንደዚህ ዓይነቱን ትስስር የቋንቋ ባህሪ የሚፈጥረው ቢሆንም በቋንቋ ትምህርት

ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ይህን ሀሳብ በተመለከተ Byren (1981:108) እንደሚከተለው ያብራሩታል፡፡

የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ድንገት የሚፈጠረውን ቅንጅት ሳይሆን ሆን ተብሎና ታቅዶበት ተማሪዎቹን በልምምድ ብቁና የቋንቋው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያግዝ ሂደት ነው፡፡የክሂሎች ቅንጅታዊ አተገባበር ከክፍለ ጊዜው የትምህርት ዕቅድ ጋር በሚስማማ መልኩ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባውን ክሂል በዋናነት ትኩረት እንዲቸረው ለማድረግ ያስችላል፡፡አክለውም የቋንቋ ክሂሎች እርስ በእርስ ተሳስረው አንዱ ሲነሳ አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሌሎች ክሂሎችን በማስከተል ተዋህደው የሚቀርቡበት የቋንቋ ክሂሎችን የማስተማሪያ ሂደት ነው በማለት አብራርተዋል፡፡እንዲሁም Rivers(1981:297) በበኩላቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን በሚማሩበት ጊዜ ሌሎችንም ክሂሎች አብረው እንዲያዳብሩ ለምሳሌ ተማሪዎች በሳል ድርሰት እንዲጽፉ ከተፈለገ በሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ያላቸውን ችሎታ መዳበር እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጣም ጥሩ የሆነ አንብቦ የመረዳት ክህሎት የመናገርና የማዳመጥ ብቃት ካላቸው ጥሩ ጽሁፍ እንደሚጽፉ የታመነ ነው፡፡ በመሆኑም ጽህፈትን ስናስተምር ሌሎችም አብረው እንዲመጡ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ከምሁሩ ሃሳብ እንደምንረዳው የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ማለት በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ክሂሎችን በማጣመር አንዱ ሲነሳ ሌሎቹ አብረው እንዲነሱ ወይም እንዲተገበሩ የሚደረግበት ዘዴ መሆኑን ነው፡፡

### 2.3.1.የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረቢያ ዘዴዎች

በመማር ማስተማር ሂደት የቋንቋ ክሂሎችን አዋህዶ ለማቅረብ የሚያስችሉ የተለያዩ ዘዴዎች እንዳሉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ከዚህ በመቀጠል ጥቂቶችን ለማየት ተሞክሯል፡፡

Celece-Muricia (1991:313) እና Oxford (2001:3) የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ ስርዓተ ትምህርትና መርሀ ትምህርት ቀራጮች፣መጽሀፍ አዘጋጆችና መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም እንዳለባቸው ገልጸው በተለይም ይዘትን መሰረት ያደረገ፣ተግባር ተኮር የሆነ ወይም ሁሉንም ዘዴዎች ያዋሀደ ዘዴን ተጠቅመው ክሂሎችን በተቀናጀ መልኩ ማቅረብ እንደሚችሉ አስረድተዋል፡፡ከዚህ በመቀጠል ስለ ይዘት ተኮር እና ስለ ተግባር ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ እንመለከታለን፡፡

ይዘት ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ በዋናነት ይዘት ላይ ትኩረት ያደረገ የቋንቋ ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴ ነው፡፡በዚህም አማካኝነት ተማሪዎቹ የትምህርቱን ይዘት እየተማሩ የቋንቋ ችሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡

Celce-muricia (1991፥316) ይዘት ተኮር ዘዴ ትኩረት የሚያደርገው በቋንቋ ቅርጽ ላይ ሳይሆን ተማሪዎች ርዕሰ ጉዳዩን መሰረት በማድረግ እንዲረዱት የሚያደርግ አቀራረብ ነው ሲሉ Atkins etal (1996፥223) በበኩላቸው የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ ተማሪዎች ክሂሎችን አዋህደው እንዲጠቀሙና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ ከማድረግም በተጨማሪ የሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ይዘቶች በጥልቀት እንዲገነዘቡ ማስቻልም ነው ይላሉ፡፡

ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው ይዘት ተኮር የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ዘዴ ዋና ዓላማ ቋንቋን በይዘት ማስተማር በመሆኑ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ከማዳበር ባሻገር የተለያዩ ይዘቶችን በጥልቀት እንዲያውቁ የሚያደርግ ዘዴ መሆኑን ነው፡፡

ተግባር ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራርብ የሚያተኩረው ደግሞ ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆነ ተግባር ላይ እየተሳተፉ ቋንቋውን ለመማር የሚያስችላቸው ዘዴ ነው፡፡ይህን ዘዴ በተመለከተ ምሁራን እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡ተግባር ተኮር የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆኑ የቋንቋ ተግባራት የሚሳተፉበትና ተግባቦታዊ የቋንቋ አጠቃቀምን የሚያዳብሩበትን ተግባራትን የሚያከናውኑበት ዘዴ መሆኑን (Oxford፥2001) ያስረዳሉ፡፡

ከምሁራን ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ተግባር ተኮር ዘዴ ተማሪዎች በጥንድና በቡድን በተለያዩ ተግባራትና ክንውኖች እየተሳተፉ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅተው እንዲጠቀሙባቸው የሚያደርግ ዘዴ መሆኑን ነው፡፡ይህን ዘዴ ተግባራዊ ማድረግ ተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀምን እየተገነዘቡ ተግባቦትን የሚያዳብሩበትና መረዳታቸውን የሚያጎለብቱበት ዘዴ መሆኑን ነው፡፡ቀጥሎ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረብ ያለውን ጠቀሜታ እናያለን፡፡

### 2.3.2.የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ጠቀሜታ

Oxford (2001:2) የቋንቋ ክሂሎች ተናጠላዊ አቀራረብ በጥንታዊው የቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ከመገደብ ባለፈ በሌሎችም ትምህርታቸው ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርግ እንደነበር በመግለጽ ለዚህም እንደምክንያት የገለጹት ስርዓት

ትምህርትና መርህ ትምህርት የሚቀርጹ ባለሙያዎች የቋንቋ ትምህርቱን በቋንቋ ቅርጽ ላይ እንዲያተኩር በማድረግ የተነጣጠሉ የቋንቋ ክሂሎችን ማቅረባቸው ነው፡፡በዚህ ሁኔታ የተማሩ ተማሪዎች

ሊኖራቸው የሚችለው የቋንቋ እውቀት ደግሞ ስለቋንቋው ከማወቅ ባለፈ በታላሚው ቋንቋ የመጠቀም ችሎታቸውን እንዳያጎለብቱና ተግባቦታዊ ብቃታቸው በተገቢው መጠን እናዳይጨምር ትልቅ እንቅፋት ሆኗል በማለት ያብራራሉ፡፡እንዲሁም McDonough and Shaw (1992:217) በበኩላቸው የቋንቋ ክሂሎችን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ አቀናጅቶ ማቅረብ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ዋና ዋና ዋናዎቹ የተማሪውን ፍላጎት ማነሳሳት፣የተማሪውን ግንዛቤ ማሳደግና የመማር ማስተማርን ሂደትን ማፋጠን መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ከምሁራን ሀሳብ እንደምንረዳው የቋንቋ ክሂሎችን ነጣጥሎ ከማቅረብ ይልቅ አቀናጅቶ ማቅረቡ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ነው፡፡በየትኛውም ደረጃ የሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎቹ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በሚገባ ተክነው መገልገል እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ይሁን እንጅ የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ በአንብቦ መረዳትና በመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው ዓላማዎች ውስጥ "የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን ማዳበር" የሚል ይጠቀሳል፡፡ ይህ አላማ ከግብ ሊደርስ የሚችለው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ችሎታን ያዳብራሉ ተብለው የሚካተቱ ይዘቶች በተገቢው መንገድ በመፃሀፉ ውስጥ ተቀናጅተው ሲቀርቡ ነው፡፡ተማሪዎች በታቀደው ይዘት ተጠቅመው በተደጋጋሚ መለማመድ ሲችሉ የታሰበው ግብ ሊገኝ ይችላል፡፡በመሆኑም ከዚህ በላይ ከቀረቡት ቅኝቶች በመነሳት አጥኝዋ ክሂሎች በውህደት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ታምናለች፡፡ ስለሆነም በመጀመሪያ ስለክሂሎቹ ምንነትና አስፈላጊነት መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡በዚህም መሰረት ስለ አንብቦ መረዳት ምንነት፣የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት፣ ስለመጻፍ ክሂል ምንነትና የመጻፍ ክሂል ትምህርት አስፈላጊነትን በተመለከተ እንደሚከተለው ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

## 2.4. አንብቦ መረዳት ምንድነው?

አብዛኞቻችን አንብቦ መረዳት ማለት አንድን ምንባብን ካነበብን በኋላ ጥያቄዎችን መመለስ መቻል ነው ብለን ልናስብ እንችላለን፡፡ ይሁን እንጅ እንደዚህ ከተረዳን

ትክክለኛ የሆነ ግንዛቤ አለመሆኑን ማወቅ ይኖርብናል፡፡የአንብቦ መረዳትን ምንነት በተመለከተ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ጥቂቶችን እንደሚከተለው ለማየት ተሞክሯል፡፡

አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የሚፈለገውን መረጃ ለይቶ በማውጣት ጽሁፍን የመገንዘብ ሂደት ነው፡፡አንባቢው በተገቢው ፍጥነት የሚፈለገውን መረጃ የሚለይበት ተራ ያልሆነ ጥልቅ ግንዛቤን የሚመለከት ነው Williams (1990:3)፡፡ Grellet (1981:3) በበኩላቸው አንብቦ መረዳት ማለት ከሚነበበው ጽሁፍ ውስጥ አንባቢው ወይም ተማሪው እስከሚቻለው ድረስ በብቃት የሚፈለገውን መረጃ ማውጣት መቻል ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

ከምሁራኑ ሃሳብ እንደምንረዳው አንድ ተማሪ ወይም አንባቢ የሚያነብበትን አላማ አውቆ ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችለውን መረጃ ካገኘና ለይቶ ካወጣ አንብቦ ተረድቷል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም አንብቦ መረዳት ማለት የሚፈለገውን መረጃ ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ ለይቶ ማውጣት ሲሆን አጠቃላይ የጽሁፉን መልዕክት የመገንዘብ ሂደት ነው፡፡

ስለአንብቦ መረዳት ምንነት ሲነሳ የተለያዩ ክሂሎች ጥምረት መሆኑን ምሁራን ይገልጻሉ፡፡Durkin (1977:399) እና Grellet (1991:8) እንደሚያስረዱት አንብቦ መረዳት የምንባብን ሃሳብ የመገንዘብ፣የማብራራት፣የመከለስ ፅንሰ ሃሳቦችን የማዛመድ፣አንድነትና ልዩነቶችን የመመርመር፣የመከራከርና የመወያየት ችሎታዎች ማንጸባረቂያም በመሆኑ ከመጻፍ፣ከማዳመጥና ከመናገር ክሂሎች ጋር ተነጣጥሎ ሊታይ አይችልም፡፡ይህም ሲባል ለንባብ የቀረበ ጽሁፍን በሚገባ ካነበቡ በኋላ በጽሁፉ ሀሳብ ዙሪያ መከራከርና መወያየት ከንግግር፣የጽሁፉን ሀሳብ መከለስና ማስታወሻ መያዝ ከጽሁፍ እንዲሁም ጽሁፉን ከሚደመጥ ነገር ጋር ከዜናና ከሌሎች ዘገባዎች መለየት ከማዳመጥ ክሂል ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መንገድ አንብቦ መረዳት አንባቢ የፀሀፊውን ሃሳብና አመለካከት ለመረዳት ሲል ከጽሁፍ ያገኘውን ሃሳብ ከቀደመ እውቀቱ ጋር እያገናዘበ የራሱን አዲስ አመለካከት የሚንጸባረቅበት ሂደት ነው ማለት ይቻላል፡፡

### 2.4.1.የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት

አሁን ባለንበትም ሆነ በቀደምት ጊዜያት ንባብ ቋሚ ከሆነው መረጃ ማለትም ከጽሀፈት እውቀት የምንቀስምበት ብቸኛ ክሂል እንደሆነ ይታመናል፡፡ የንባብ ትምህርትን

አስፈላጊነት አስመልክተው Williams (1990:19) ሲያስረዱ አንድን ጽሁፍ አንብቦ መልዕክቱን የመረዳት ችሎታን ለማዳበር፣በማንበብ እውቀትን ለመገብየት እንዲሁም ከተለያዩ የንባብ ባህሪያት ጋር ለማስተዋወቅና የንባብ ችሎታን ለማጎልበት የንባብ ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡Mc Donough and Shaw (1993:102) ሲገልጹ ንባብ መረጃ ለማግኘት፣አንድ ነገር መቼና የት እንደተከናወነ ለማወቅ እንዲሁም በጋዜጦች፣በመጽሄቶች የሚቀርቡትን ሀሳቦች ለመረዳትና ለመዝናናት ወይም ለመደሰት አስፈላጊ ነው በማለት አስረድተዋል፡፡

ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምንረዳው ንባብ ለትምህርት ብቻ ሳይሆን ለምናከናውናቸው ተግባራት መረጃ በመስጠት፣ለመዝናናትና ታሪክን ለማወቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው እንረዳለን፡፡ በመሆኑም ይህ ክሂል እንዲዳብር የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ Lindsay and Knight (2006:74) ሲያስረዱ የንባብን ክሂል ለማዳበር የምናዘጋጃቸው ጽሁፎች የሚከተሉትን ሶስት ነጥቦች ከግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን አለባቸው፡፡

<u>እነሱም</u> ፡-

- ርዕሰ ጉዳይ፡- የምንመርጠው ጽሁፍ የተማሪዎቻችንን ፍላጐት ያማከለ መሆን ይኖርበታል፡፡
- ደረጃ፡- ጽሁፉ የተማሪዎችን የእውቀትና የክፍል ደረጃ ያማከለ ሊሆን ይገባል፡፡በውስጡ የሚካተቱ ቃላት፣ አረፍተ ነገሮች ወዘተ. ውስብስብነት ከተማሪዎች የእውቀት ደረጃ ጋር የተመጣጠነ መሆን አለበት፡፡
- የጽሁፉ ርዝመት (መጠን)፡- የምንመርጠውን ጽሁፍ ስፋት ወይም መጠን ክፍል ውስጥ ካለን ጊዜ አንፃር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ጽሁፍን ለማንበብ የሚወስድብን ጊዜ እና ከንባብን በኋላ ለሚሰሩ ተግባራት የምንሰጠው ጊዜ ከአለን አጠቃላይ ጊዜ ጋር ካልተጣጣመ ልናዳብረው የፈለግነውን የንባብ ክሂል ውጤታማ ልናደርገው አንችልም በማለት ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ፅሁፍ እንደምንረዳው የንባብ ክሂልን ለማዳበር የማስተማሪያ ፅሁፎችን ትኩረት ሰጥቶ መምረጥና የተማሪዎችን የቀደመ ችሎታ ማወቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ነው፡፡

## 2.4.2.አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ

የንባብ ትምህርት ሲቀርብ ተማሪዎችን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ ክንዋኔዎችን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

የንባብ ትምህርት አቀራረብ ቅድመ ንባብ፣የንባብ ጊዜና ድህረ ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተ የትምህርት አቀራረብ እንዲሆን የመስኩ ምሁራን የሚገልጹ ሲሆን በእነዚህ አቀራረብ ማስተማር ደግሞ የተሻለ ውጤታማ መሆኑን Lindsay and Knight (2006:74-81) ገልጸዋል፡፡

**ቅድመ ንባብ ተግባራት**፡- የምንለው ተማሪዎች ለምንባቡ የሚኖራቸውን እውቀት ከወዲሁ ለመጠቀም የሚያገለግለን ነው፡፡

የቅድመ ንባብ ተግባራት አስፈላጊነትም ፡-

- ተማሪዎችን ለንባብ ለማዘጋጀት
- ተማሪዎችን በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ያላቸውን የቀደመ እውቀት ለማረጋገጥ
- የንባብ ፍላጎት እንዲኖራቸው ለማድረግ እና ሌሎችም ጠቀሜታዎች አላቸው፡፡

ቅድመ ንባብ ተግባራት በሁለት መንገድ ይካሄዳል፡፡

እነሱም፡-

1. በጥያቄና መልስ መልኩ ይካሄዳል፡፡
2. ድርጊቶችን በማከናወን /ለምሳሌ፡- ስዕሎች መሳል እና ችግር ፈቺ በሆኑ ጥያቄዎች ዙሪያ እንዲወያዩ በማድረግ ይካሄዳል በማለት Lindsay and Knight (2006:75)ገልፀዋል፡፡

   ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች የሚነበበውን ጽሁፍ አስመልክቶ ከንባብ በፊት የሚሰሩ በመሆናቸው የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሏቸው፡፡

እነሱም ፡-

- ተማሪዎቹ ቀድመው ስለሚዘጋጁ ወደ ዋናው ምንባብ በሚገቡበት ጊዜ ምን መስራት እንደሚጠበቅባቸው ያውቃሉ፡፡ ይህም መማርን ቀላል፣ ተፈጥሯዊና ትርጉማዊ ያደርገዋል፡፡

- ቅድመ ንባብ ተግባራት ተማሪዎች የጋራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያግዛሉ፣ ልምዳቸውን፣ ሃሳባቸውንና ጽሁፉን አስመልክቶ የገመቱትን ከማንበባቸው በፊት ስለሚለዋወጡ የተሻለ ግንዛቤ ይዘው ያነባሉ፡፡
- ቅድመ ንባብ የመማር ክሂልን መማሪያም ነው፤ተግባራቱ ተማሪዎቹ ጽሁፍን እንዴት እንደሚያነቡ ወይም እንዴት እንደሚያቀርቡት የሚያመላክቱ በመሆናቸው ለራሳቸው የንባብ ስራ ሃላፊነት እንዳለባቸው ግንዛቤያቸውን ያጐለብትላቸዋል፡፡
- ተማሪዎች ስለሚያነቡት ጽሁፍ አስቀድመው በጋራ እንዲሰሩና የጋራ ግንዛቤያቸውን ይዘው እንዲያነቡ ያደርጋሉ፡፡
- የመገመት ተግባራቱ በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ሲሆኑ ከሚነበበው ጽሁፍ ምን እንደሚጠበቅ በማመላከት ጽሁፉን የማንበብ ፍላጐትን ይጨምራል፡፡
- ተማሪዎች ቀድመው የገመቱትን ወይም የሚጠብቁትን ከሚያነቡት ጋር እያነፃፀሩ እንዲያነቡ ያግዛል፡፡
- ሰዎች አዲስና ያልታወቀ ነገር ይፈትናቸዋል፡፡ ለዚህም ቅድመ ንባብ ተግባራት በሚነበብ ጽሁፍ ውስጥ እንግዳ ነገር ወይም ችግር ሲያጋጥም እንዴት መፍታት እንደሚቻል መንገድ ያመላክታል፡፡

- ቅድመ ንባብ ተግባራት የተማሪዎችን ቋንቋውን በጥልቀት የመማር ፍላጐት ይጨምራሉ ፡፡ ነገሮችን በጥልቀትና በስፋት የማየትና የመረዳት ችሎታን ያሳድጋሉ፡፡

**የንባብ ጊዜ ተግባራት** ፡-በዚህ የንባብ ጊዜ ተግባር ወቅት መምህራን ተማሪዎቻቸውን በንቃት ላይ የተመሰረተ ንባብ እያካሄዱ መሆናቸውን የሚቆጣጠሩበትና ተማሪዎቹ የበለጠ ለንባብ እንዲነሳሱ የሚያግዙ ተግባራትን የሚያከናውኑበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ የንባብ ጊዜ እያነበቡ ያሉ ተማሪዎችን በርካታ ተግባራትን ማሰራት ይቻላል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ተግባራት እንደ የምንባቡ ይዘትና አላማ ይለያያሉ፡፡ ይህንን በተመለከተ Lindsay and Knight (2006፡78) የንባብ ጊዜ ተግባራትን በሶስት መንገድ ገልፀዋል፡፡ እነሱም ፡-

- የተማሪና የመምህር ጥምረት ተግባራት
- የተማሪ ከተማሪ ጥምረት ተግባራት
- የጽሁፍ ተግባራት ናቸው በማለት ገልፀዋል፡፡

**ድህረ ንባብ ተግባራት፡-**ድህረ ንባብ ከንባብ ሂደት በኋላ የሚሰጡ ጥያቄዎች የሚሰሩበት ሂደት ነው፡፡ እንዲሁም በንባብ ማጠናቀቂያ ጊዜ የሚታዩ ሲሆን የንባብ ሂደት የሚከለስበት ነው፡፡ ድህረ ንባብ ተግባራት ተማሪዎች ምንባቡን ሙሉ በሙሉ

መረዳታቸውን ለማረጋገጥ፤ የምንባቡን ተዓማኒነት እንዲገመግሙ ለማበረታታት እና ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያያዙ ለማድረግ የሚጠቅም ነው፡፡

በዚህ ደረጃ ተማሪዎቹ ከተነሱባቸው የቅድመ ንባብና በመቀጠልም በንባብ ጊዜ ከተሳተፉባቸው ጥያቄዎች በተረዱቸው ሃሳቦች መሰረት የሚመልሷቸውን ጥያቄዎች የሚያካትት ተግባራዊ ክንውንን ይይዛል፡፡ በአብዛኛው የግምገማ ስራዎችን የሚይዝ ሲሆን ምንባቡን መነሻ በማድረግ ከክፍል ውጭ ካለው አለም ጋር በማዛመድ ሃሳብ እንዲሚያቀርቡባቸው የሚችሏቸው ጥያቄዎች የሚካተቱበት ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹ ከራሳቸው የህይወት ልምድና እውቀት አኳያ የአስተሳሰብ አድማሳቸውን ተጠቅመው ሃሳብ የሚሰነዝሩበት ነው፡፡ የሚዘጋጁት ጥያቄዎች ለአሳታፊነታቸው እንጂ ለውጤት ተብለው መዘጋጀት የለባቸውም፡፡

## 2.4.3.አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ምንነትና ሲዘጋጁ ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች

አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ከምንባብ ቀጥሎ የሚመጡ በተነበበው ጽሁፍ ላይ መሰረት ያደረጉ እንደሆኑ Nuttal (1988) ገልጸዋል፡፡እንደ Shin (1992:290) ቋንቋን ለማስተማር ዓላማ ባደረገ የንባብ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች የሚቀርቡላቸውን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መመለስ እንዲያስችላቸው መምህራን በቅድመ ንባብ ተግባራት ዳራዊ እውቀታቸውን እንዲፈትሹ ያደርጋሉ፡፡ የሚዘጋጁት የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትም ይህን የተከተሉ ናቸው፡፡

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችም በቅድመ ንባብ ተግባር የተፈተሹ የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት፣ በንባብ ጊዜ የሚያዙ አጫጭር ማስታወሻዎችን ከንባብ በኋላ የሚካሄዱ ውይይቶችን፣የጽሁፍ ተግባራትና ሌሎች ክሂሎችን አጠቃለው የሚይዙ ናቸው፡፡ይህም ተማሪዎች መሰረታዊ የሆኑ በይዘት ላይ ያተኮሩ መልመጃዎችን እንዴት እንደሚሰሩ በመጠቀም ልምድን ያዳብርላቸዋል፡፡

በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አንባቢ የአንድን ጽሁፍ አጠቃላይ መልዕክት ከተለያዩ አተያዮች አንጻር መገንዘብን ለመመርመር የሚዘጋጁና ክሂልን ለማዳበር የሚረዳ መንገድን የሚያሳዩ ጥያቄዎች ናቸው፡፡እነዚህ ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ወቅት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ በርካታ ነጥቦች እንዳሉ የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የአንባቢያንን ችሎታ በመመዘን ላይ ብቻ ያተኮሩ ሳይሆኑ አንባቢያኑ አንድን ጽሁፍ ለመረዳት በራሳቸው የሚፈጥሩትን አዳዲስ ስልት እንዲቀይሱ

የሚገፋፉ መሆን እንደሚኖርባቸው የተለያዩ ምሁራን አብራርተዋል፡፡ Johnson (1982) እንደገለጹት ምንባብን መሰረት ያደረጉ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተከታታይነት ያላቸው የመረዳትን ሁኔታ ማረጋገጫ መልመጃዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መልመጃዎች ደግሞ እንደ ጽሁፉ ባህሪ ተለዋዋጭነት ያላቸው ይሆናሉ፡፡

ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምንረዳው የእያንዳንዱ ምንባብ ባህሪ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በመሆኑም በመልመጃዎቹ ስር የሚካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ጽሁፉን ደጋግመው እንዲያነቡ የሚገፋፉ ሆነው ቢዘጋጁ ተመራጭነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ምክንያቱም ተማሪዎች የራሳቸውን የአነባበብ ስልት ተጠቅመው ምንባቡን የመረዳት፣የመተርጎም ፣የማብራራት፣ የማጠቃለል እና ሌሎች ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት መንገድ የሚያሳይ በመሆኑ ነው፡፡

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ትኩረት ሊደረግባቸው ከሚገቡ በርካታ ነጥቦች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱትን Grellet (1991:6-9) ገልጸዋል፡፡እነሱም፡-ከአጠቃላይ ጭብጥ መጀመር፣የጥያቄዎችን ስብጥር መጠበቅ፣ ከልዩልዩ ክሂሎች ጋር ማቀናጀትና በመልመጃ ጥያቄዎችና በፈተና ጥያቄዎች መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች የይዘት ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል ስለ ጽህፈት ክሂል ምንነትና ስለክሂሎቹ ትስስር እንመለከታለን፡፡

## 2.5.የጽህፈት ክሂል ምንነት

ከቋንቋ ክሂሎች መካከል መጻፍ አንዱ ሲሆን የንግግር ድምጾችን በሚወክሉ ምልክቶች አማካኝነት ሀሳብን በወረቀት ላይ በማስፈር የመግባባት ተግባር ነው፡፡የክሂሉን ምንነት አስመልክተው ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ የሰጡ ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

Byrne (1988) ሲገልጹ በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ የንግግር ድምጾች የየራሳቸው የሆነ ትዕምርታዊ ውክልና ይሰጣቸዋል፤ ትዕምርቶቹ የቋንቋውን ሥርዓት ተከትለው ይዋሀዳሉ፡፡ እነዚህ ድምፆች ትርጉም ሊሰጡ በሚችሉበት መንገድ ተቀናጅተው ይቀርባሉ ይህም ጽህፈት ይባላል በማለት አብራርተዋል፡፡ አክለውም ጽህፈት ድምፅን አቀናጅቶ ቃላት መመስረት ብቻ ሳይሆን እነዚያን ቃላትም በማቀናጀት ትርጉም ያለው ዓ.ነገርን ማዋቀርን፣ዓ.ነገሮችም አንቀጽንም መመሰረትን ወዘተ የሚያካትት ነው ሲሉ ገልጸውታል፡፡

ይህንኑ ሀሳብ ብዙዎቹ የመስኩ ባለሙያዎች ይጋሩታል (Harmer 1991፣ 149 )እና(Nunan 1988:36)።

Byrne (1991) ጽሁፍ በምንጽፍ ጊዜ ምልክቶችን እንጠቀማለን፡፡ እነዚህ ምልክቶች የሚፈጥሯቸው ፊደሎችና የፊደሎች ግንኙነት ሲሆን ከድምጹ ጋር ይገናኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ ንግግር ከድምጽ በላይ እንደሆነ ሁሉ ጽህፈትም በግልጽ የሚታዩ ምልክቶችን ከማፍለቅ በላይ ነው ብለው በይነውታል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ብያኔዎች እንደምንረዳው ጽህፈት የንግግር ድምፆችን የሚወክሉ ትዕምርቶችን በመጠቀም ሀሳብን፣ ስሜትን፣ መረጃን እንዲሁም መልዕክትን ማስተላለፊያና ቀርፆ ማስቀመጫ ክሂል ነው፡፡በሚፃፍበት ወቅትም የቋንቋውን ተናጋሪዎች የቋንቋ አጠቃቀምና ሥርዓት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ጽህፈት እንደ ቃላዊ ክሂሎች በመልመድ ሳይሆን በመማር የሚገኝ ከመሆኑም ባሻገር ከፍተኛ ትጋትንና ጥረትን የሚጠይቅ የቋንቋ መሠረታዊ ክሂል ነው፡፡

መጻፍ የሀሳብ አቀነባበርን፣የሀሳብ ፍሰትን፣የቃላት አመራረጥን እና የአገላለጽ ስልትን የሚጠይቅ የቋንቋ ክሂል ነው፡፡ ስለዚህ ብዙዎች እንደሚስማሙበት መጻፍ የነቃ አዕምሮ ውጤት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን የመጻፍ ክሂል በብዙዎች ዘንድ አስቸጋሪ መሆኑ ይገለጻል፡፡ መጻፍ ለብዙዎች አስቸጋሪ የሚሆንበትን ምክንያት Byrne (1988) ሲያስረዱ ሶስት ምክንያቶችን ይጠቅሳሉ፡፡እነሱም ስነልቦናዊ ችግር፣ሰዋሰዋዊ ችግርና ግንዛቤዊ ችግር ናቸው፡፡ በመቀጠል ስለጽህፈት ክሂል አስፈላጊነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2.6.የጽህፈት ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት

ጽህፈት ሲዘጋጅ ከአንባቢ ጋር ተግባቦትን የሚፈጥር በመሆኑ በጥሩ ሁኔታ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ አስፈላጊነቱን አስመልክተው Raimes(1983፡3) ሰዎች በጊዜና በቦታ ሳይገደቡ በሚታዩ ትዕምርቶች አማካኝነት ከማግባባቱም በላይ ለትምህርት መማሪያ፣ለሀሳብ መለዋወጫና ለመሳሰሉት ነገሮች እንደሚያገለግል ይገልፃሉ፡፡ይህ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቱ ደግሞ በትምህርትነት እንዲሰጥና እንዲያድግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቶለታል፡፡እንዲሁም celce Murcia (1991፡241) በበኩላቸው ተማሪው በተሻለ ሁኔታ በቋንቋው እንዲጠቀምና የተግባቦቱን ሂደትም በጥልቀት እንዲመረምር ያደርገዋል ይላሉ፡፡

ከምሁራን ሀሳብ እንደምንረዳው በጥሩ ሁኔታ እንዲጠቀም ያስችለዋል ሲባል በጽህፈት ክሂል አማካኝነት ሌሎችን የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር ማስቻሉ ነው፡፡ በሌላ በኩል Ur (1996፥168) የጽህፈትን ትምህርት ከግለሰብዓዊና ከማህበራዊ ፋይዳ አንፃር ይመለከቱታል፡፡ግለሰባዊ ፋይዳው አመለካከትን ከመግለፅ፣ የተፃፉ ሰነዶችን ከመመርመርና አዕምሯዊ ተግባራትን ከመመርመር አንፃር ሲመለከቱት ማህበራዊ ፋይዳውን ደግሞ የማህበረሰቡ የሆኑ የተለያዩ ታሪኮችን፣ ባህላዊ መገለጫዎችን፣ሥነጽሁፋዊ ስራዎችንና የመሳሰሉትን ለመሰነድ ካለው ፋይዳ አንፃር ቃኝተውታል፡፡ በመሆኑም ጽሁፍ ለግለሰብም ይሁን ለማህበረሰቡ ያለው ፋይዳ ጉልህ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን እንረዳለን፡፡ከዚህ በመቀጠል በማንብበና በመጻፍ ክሂሎች መካከል ያለውን ትስስር ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

## 2.7. የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ትስስር

በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች መካከል የጠበቀ ትስስር ያላቸው በመሆኑ በቅንጅት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡

መጻፍ አንብቦ የመረዳት ክሂልን ሊያሳድግ ይችላል፤ማንበብ ደግሞ የመጻፍ ክሂልን ሊያዳብር ይችላል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ በሚያነቡበት ጊዜ የአጻጻፍ ስልቱን፣ የታሪክ አወቃቀሩንና የጽሁፉን መልዕክት በመገንዘብ ራሳቸው ለሚጽፉት ጽሁፍ ይጠቀሙበታል፡፡ይህም ሂደት በሁለቱ ክሂሎች መካከል ያለውን ትስስር የሚያመለክት መሆኑን Harp, etal (1996) ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም Ruddel (1997) ሲገልጹ ማንበብና መጻፍ ጥብቅ ትስስር ስላላቸው በውህደት ቢቀርቡ የተማሪዎችን በውህደት የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ሊያሳድጉ ይችላሉ፡፡

የሁለቱ በውህደት መቅረብ የትምህርቱንም ይዘት በተገቢው መንገድ እንዲረዱት ሊያግዛቸው ይችላል፡፡ ክሂሎቹ የቀደመ እውቀትንና ነባር ልምድን የሚጠይቁ ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው በመሆናቸውም እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ May (1990) በተመሳሳይ ተማሪዎቹ ውስብስብ ዐ/ነገሮችን በሚጽፉበት ጊዜ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ሊዳብር ይችላል፡፡ይህም የሚያሳየው በክሂሎቹ መካከል ጥብቅ ትስስር መኖሩን ያመለክታል፡፡አንባቢዎችና ፀሀፊዎች የሚያከናውኗቸው ተግባራት በመስታዎት ውስጥ እንደሚታይ የአንድ ቁስ አካል ምስልና ራሱን የቁስ አካሉን ያህል ትስስር አላቸው፡፡ አንባቢዎችና ፀሀፊዎች ለማንበብና ለመጻፍ በሚዘጋጁበት ጊዜ ሁለቱም

ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ፡፡ይኸውም ለማንበብ ወይም ለመጻፍ የራሳቸውን ዓላማ ይነድፋሉ፤ፍላጎትም ይኖራቸዋል፤የቀደመ እውቀታቸውን ይጠቀማሉ፤አእምሯዊ ምስል ይፈጥራሉ፡፡ የፀሀፊዎች ፍላጎት ሀሳባቸውን ለሌሎች በማካፈል መረጃ መስጠት ወይም ሰዎችን ማዝናናት ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም የሁለቱ የመግባቢያ መንገዳቸው የተዘጋጀው በጽሁፍ ነው፡፡የአንባቢዎች ፍላጎት ደግሞ መረጃ ለማግኘት፣ ሃሳብ ለመጋራት ወይም ለመዝናናት ጽሁፍ ማግኘት ነው፡፡ በመሆኑም ሁለቱም ባለጉዳዮች ማለትም ፀሀፊውና አንባቢው በተዘጋጀው ጽሁፍ ይገናኛሉ በማለት አስረድተዋል፡፡

የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትስስር ቀደም ሲል ለማየት ተሞክሯል፡፡የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትስስር መሰረት በማድረግ የክሂሎቹ በቅንጅት መቅረብ ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ጠቀሜታ በሚመለከት ተመራማሪዎች የተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦችን ገልጸዋል፡፡ለአብነት ያህል የሚከተሉትን እንመለከታለን፡፡

## 2.7.1. አንብቦ መረዳትንና የመጻፍን ክሂልን በቅንጅት የማቅረብ አስፈላጊት

አንብቦ መረዳት የተለያዩ ክሂሎች የተዋሀዱበት ሂደት እንደሆነ Ellis and Brain (1980 140:143)ይገልጻሉ፡፡እንደ Grellet (1991፡4-5)ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ መንገዶችን በማመቻቸት የተለያዩ አይነት ጥያቄዎችን ማውጣት ይቻላል፡፡ጥያቄዎችም ከምንባቡ አጠቃላይ አደረጃጀት ጀምሮ እስከ ዝርዝርና ግልጽ የተቀመጡ ይዘቶች ላይ ያተኩሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡የጥያቄዎቹ አይነትና ተግባርም የተወሰነ ክሂል ከማዳበር ጋር የተቆራኘ መሆን ይኖርበታል፡፡ይህም አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ለተማሪዎች በሚወጡ ጥያቄዎች አማካኝነት ሊረጋገጥ ይችላል፡፡ጥያቄዎቹ የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ብቻ ሳይሆን ሌሎችን የቋንቋ ክሂሎችንም ማዳበር ይጠበቅባቸዋል፡፡

ንባብና ፅሁፍ፡-በንባብ ትምህርት ወቅት ተማሪዎች አብረው ሊያዳብሩት ከሚጠበቅባቸው ክሂሎች ውስጥ አንዱ ጽሁፍ ነው፡፡የመጻፍ ክሂል በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አማካኝነት እንዲዳብር ተማሪዎች ሊያከናውኗቸው የሚችሉ ተግባራትን መስጠት ያስፈልጋል፡፡ለምሳሌ ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፣ሀሳባቸውን ባጭር ባጭሩ በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታቸው በተወሰነ መልኩ እንዲያቀርቡ እና አጫጭር ሃሳቦችን አብራርተው በዝርዝር እንዲጽፉ የሚያደርጉ መልመጃዎች የመጻፍ ክሂልን ከንባብ ጋር በተቀናጀ መልኩ እንዲዳብር የሚያግዙ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ከምሁራኑ ሃሳብ እንደምንረዳው አንብቦ መረዳት ከሌሎች ክሂሎች ተነጥሎ ሊታይ የማይችል መሆኑን ነው፡፡በመሆኑም በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አማካኝነት ሌሎች ክሂሎች ተዋህደው እንዲዳብሩ ማድረግ እንደሚቻል እንረዳለን፡፡

Conley (1997) የማንበብና የመጻፍ ክንዋኔዎችን በውህደት ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ ጠቃሚ ዘዴ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡በተጨማሪም ማንበብና መጻፍ በእለት ተእለት የመማር ክንዋኔዎች ላይ ትርጉምን መገንባት የሚያስችሉ የቋንቋ ሂደቶች እንደሆኑም አስገንዝበዋል፡፡በመሆኑም አንዱ ክሂል ሌላውን ለማዳበር መሰረታዊ ጠቀሜታ ያለውና እርስ በርሳቸውም የሚደጋገፉ በመሆናቸውም ነው፡፡

የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትስስር መሰረት በማድረግ የክሂሎቹ በቅንጅት መቅረብ ያለውን ጠቀሜታ በሚመለከት ቀደም ሲል ለማየት ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ክሂሎቹን በቅንጅት ለማዳበር የሚጠቅሙ ብልሃቶችን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## 2.7.2.አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ብልሃቶች

አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በውህደት ለማስተማርና ለማለማመድ የተለያዩ ዘዴዎች እንዳሉ የመስኩ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ፡፡ለአብነት ያህል ጥቂቶችን ለማየት እንሞክራለን፡፡

Block (1997) ሲገልጹ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን ለማጎልበት ከፍተኛ ድርሻ ያለው በመሆኑ የወቅቱ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ አብይ ጉዳይ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡አክለውም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት አንብቦ መረዳትና ጽሁፍ ማቀናበርን ሊያጎለብቱ የሚችሉ በርካታ ብልሃቶች እንዳሉም ገልጸዋል፡፡በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሁሉንም ዓይነት ጽሁፍ አንብቦ ለመረዳት ማንኛውንም ታሪክ ያለምንም ብዥታ አቀናብሮ ለመጻፍ ከሚያስችሉ ብልሃቶች ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ፣ማብራራትና መተርጎም፣ማጠቃለል፣መተንበይና መገመት በጥልቀት ማሰብ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዳቸውን በተናጠል እንመለከታለን፡፡

ጥያቄ መጠየቅ፡- በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ጥያቄ መጠየቅ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ለማሳደግ ጠቀሜታ እንዳለው የተለያዩ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ Block (1997) ሲገልጹ ጥያቄ መጠየቅ ተማሪዎች አዳዲስ ሀሳቦችን ቀደም ብለው ከሚያውቁት

ጋር አጣምረው እንዲያደራጁ ይረዳቸዋል፡፡ ጥያቄ የመጠየቅ ተግባር በራሱ እውቀትን የማዳበር ክንውን ነው ሲሉ Airasian(1997) በበኩላቸው በቋንቋ መማር ማስተማር ወቅት ተማሪዎች ጥያቄ የሚያቀርቡ ከሆነ ሀሳባቸውን በቃላት ጽፈው እንዲገልጹ፣በጥልቀት እንዲያነቡና ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ ስለሚያደርግ ጠቀሜታው ከፍተኛ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Gary(1995) ተማሪዎች እያነበቡ ወይም እየጻፉ እያሉ ምን አውቃለሁ? ለማወቅ የምፈልገው ምንድነው? ያወቅኩት ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ሲያነሱ ግንዛቤያቸውን ያሳድግላቸዋል በማለት አስረድተዋል፡፡

ከዚህም በመነሳት አጥኝዋ ተማሪዎች ሲያነቡና ሲጽፉ በርካታ ጥያቄዎችን በጠየቁ ቁጥር ትምህርቱን የመረዳት ችሎታቸው እየጎለበተ ሊሄድ እንደሚችል ታምናለች፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ጥሩ ጥያቄ አቅራቢዎች እንዲሆኑ ሊለማመዱ እንደሚገባም ታስገነዝባለች፡፡

መተንበይና መገመት (Inferring and predicting)፡- ይህን የማስተማሪያ ብልሃት በተመለከተ Block (1997) መገመት የሚባለው አንባቢው እያነበበ እያለ ቀጥሎ የሚመጣውን ሁነት ድርጊት ወይም ሀሳብ የሚጠቁምበት ልዩ የመገመቻ ስልት ነው፡፡ መተንበይ ግን ከጽሁፍ አንብቦ የሚገኝን መረጃ ከቀደመ እውቀቱና ገጠመኙ ጋር አዛምዶ የተለየ ትርጉም የሚሰጥበት ወይም ስለሚነበበው ሀሳብ ምክንያታዊ ግምገማ ወይም ዳኝነት የሚሰጥበት አማራጮችን የሚጠቁምበት ልዩ ስልት ነው:: እንዲሁም Barrs (2000) መተንበይን በሚመለከት የሰጡት ማብራሪያ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አንድን ጽሁፍ በማንበብ ላይ እያሉ የገጸባህሪያትን ማንነት፣ድርጊት፣ሴራ በመረዳት ንባባቸውን ሳይጨርሱ ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን በመተንበይ መደምደሚያ ላይ ይደርሳሉ፡፡ይህም የሚያመለክተው ተማሪዎቹ ጽሁፉን በአግባቡ መረዳታቸውን በመጻፍ የሚገልጹበት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡እንዲሁም አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ከሚያገለግሉት ብልሃቶች መካከል ማብራራትና መተርጎም ተጠቃሾች እንደሆኑ Block (1997) ያስረዳሉ፡፡በእነዚህ ብልሃቶች አማካኝነት ተማሪዎች ያነበቡትን ነገር በመጻፍ እንዲያብራሩና ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድረግ የመረዳት ችሎታቸውን ለመገንዘብ ጥረት የሚደረግባቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡ተማሪዎች እነዚህን ብልሃቶች ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ስለአነበቡት ጽሁፍ ዝርዝር ማብራሪያ፣ትርጉምና ትንተና በጽሁፍ መስጠት የሚያችሉበት እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡

ከዚህም ሌላ Gary (1995) እንደገለጹት ተማሪዎች ከመጀመሪያው ንባብ በኋላ በሚዘጋጁት የውይይት ክንዋኔዎች ሃሳባቸውን እንዲለዋወጡ የሚገፋፉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ከእነዚህ

ክንዋኔዎች በኋላ ተማሪዎቹ ስለጽሁፉ ያላቸውን ግንዛቤ ይተነብያሉ፣ ትርጉም ይሰጣሉ፣ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችን ይመረምራሉ፡፡እንዲሁም ተማሪዎች ስላነበቡት ወይም ስለጻፉት ነገር ማጠቃለያ መስጠት ከቻሉ ላነበቡት ወይም ለጻፉት ይዘት በቂ መረጃ ያላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡ይህ ዘዴ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታን ለማጎልበት ጠቃሚ ብልሃት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ማጠቃለል (Summarizing)፡- ማጠቃለልን በሚመለከት Block and Mangeri (1995) እንደገለጹት ተማሪዎች ከሚያነቡት ጽሁፍ በአእምሯቸው የታሰባቸውን በጽሁፍ የሚያጠቃልሉ ከሆነ የማስታወስ ወይም እውቀትን ይዞ የመቆየት ችሎታቸው 16% ያህል እንደሚጨምር ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ማጠቃለል ንባብን በዕለት ተዕለት ህይወት ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በሚያነቡበት ወቅት በየደረጃው በጽሁፍ ማጠቃለያ እየሰጡ መሄድ የሚያስችላቸውን ብልሃቶች መማር ይኖርባቸዋል፡፡

ምሰላ (Imaging):- አንባቢው በሚያነበው ጽሁፍ ውስጥ ባሉት ገጸ ባህሪያት፣ድርጊትና ሁነቶች በአእምሮ ምስል የሚቀረጽበት ስልት ምሰላ ይባላል፡፡ይህንንም ለአንባቢዎችና ለጸሀፊዎች ማስተማር አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት እያነበቡ ወይም እየጻፉ እያሉ በንቃት እንዲያነቡ ስለሚያስችላቸው ነው፡፡ይህም ብልሃት በህይወት ውስጥ ስሜታዊ ገጠመኞችን ከአመለካከትና ከተጠየቃዊ ገጠመኞች ጋር ለማቀናጀትም ይጠቅማል፡፡በቋንቋው ሂደት ውስጥ በራሱ ሳይሆን የቋንቋው ሂደት በሚፈጥረው ገጠመኝ ውስጥ ጠልቆ ለመግባት ያስችላል፡፡ምስል ከሳች ጽሁፎችን እንዲያነቡ በማድረግ እያበቡ እያሉ በአእምሯቸው የመጣውን ምስል እንዲናገሩ በማድረግ እያነበቡ እያሉም ምስላቸው እንዴት እየተለወጠ እንደሄደ በመጠየቅም ማለማመድ እንደሚቻል Block (1997) አስረድተዋል፡፡

የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ለማስተማር ከንባብ በፊት፣በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ የመጻፍ ክንዋኔዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎቹ ሃሳባቸውን እንዲያደራጁ በማድረግ የሚገፉፉ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ክንዋኔውም ቀላልና የተወሰነ ማስታወሻ መያዝ ሊሆን ይችላል፡፡ለምሳሌ ተማሪዎቹ በሚያነቡበት ጊዜ የቃላትን ትርጉም ከአገባባቸው መረዳት ሊሆን ይችላል፡፡በመጨረሻም መምህራኑ የተማሪዎችን ስራ ለመገምገም ዝርዝር መልሶች የሚያስፈልጋቸው ይዘት ተኮር ጥያቄዎችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ጥያቄዎችም ከንባብ በፊት፣በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ የሚቀርቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ሁሉም ክንዋኔዎች ከንባብ ጋር የተቆራኙ የመጻፍ ተግባሮች በመጻፍ ለማንበብ ምላሽ መስጠት የሚያስችሉና ማንበብና መጻፍን በቅንጅት የሚያለማምዱ ሊሆኑ ይገባቸዋል Gary (1995)::

በአጠቃላይ በክለሳ ድርሳናቱ የቀረቡት ጥናታዊ ግኝቶች አንብቦ የመረዳትና የመጻፍን ክሂሎች በቅንጅት ማስተማር የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ የሚያዳብር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡እንዲሁም የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች የማይነጣጠሉ፣የሚደጋገፉና ትስስር ያላቸው መሆኑንም አመልክተዋል፡፡በመሆኑም ክሂሎቹን በቅንጅት ተከታታይ በሆነ መልኩ ማቅረብ ከተቻለ የተማሪዎችን በራስ የመተማመንን ሁኔታ እንደሚፈጥርላቸው፣የተማሪዎችን ግንዛቤ እንደሚያሳድግላቸውና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እንደሚያግዛቸውም ገልጸዋል፡፡

ከዚህ በመነሳት አጥኚዋ የመስኩ ተመራማሪዎች ክሂሎቹን በቅንጅት ለማስተማር ያቀረቧቸውን ብልሃቶች በመማሪያ መጽሀፉ መካተት አለመካተታቸውንና ከተካተቱ የክፍል ውስጥ አተገባበሩ ምን እንደሚመስል ለመመርመር ይህንን ጥናት ለማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ከዚህ በመቀጠል ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን ቀደምት ስራዎችን ቅኝት እንመለከታለን፡፡

## 2.8.የቀደምት ስራዎች ቅኝት

የዚህ ጥናት አቅራቢ በመረጠችው ርዕስ ላይ ጥናት ለማካሄድ ከመጀመሯ በፊት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ አካሂዳለች፡፡ይሁን እንጅ የዚህ ጥናት ትኩረት በ2007ዓ.ም በተዘጋጀው የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ በተካተቱ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ትንተና ላይ በመሆኑ ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ጥናቶች ማግኘት አልተቻለም፡፡ነገር ግን ተቀራራቢነት ካላቸው ቀደምት ስራዎች ውስጥ ጥቂቶቹን ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት እንደሚከተለው ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

1ኛ.ትዝታ ደሳለኝ (2003) "የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛ ቋንቋን የማስተማር አተገባበርና የተማሪዎች አቀባበል ፍተሻ" በሚል ርዕስ በአዲስአበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበችው ጥናት ነበር፡፡የጥናቱ ዋና ዓላማ የነበረውም የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቋንቋ ክሂሎችን ቅንጅታዊ አቀራረብና የተማሪዎችን አቀባበል መፈተሽ ነው፡፡

ይህንን ፍተሻ ለማካሄድም አጥኝዋ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሶስቱን በናሙናነት መርጣለች፡፡ የተተኳሪዎች አመራረጥም የአላማና የነሲብ ናሙና አመራረጥ ዘዴን የተከተለ ሲሆን አጥኝዋ ለአላማ መፈተሻነትም የክፍል ውስጥ ምልከታ ቅጽ፣የጽሁፍና የቃለመጠይቆችን ተጠቅማለች፡፡በዘጠኝ ተተኳሪ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ክፍል ውስጥ በመገኘት በእያንዳንዱ መምህር የሶስት ተከታታይ ክፍለ ጊዜያት ምልከታን በማድረግ፣ተተኳሪ ተማሪዎችን የጽሁፍ መጠይቅ በማስሞላት ለዘጠኙም መምህራን ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃዎችን ሰብስባለች፤በተገኘው ውጤትም ክሂሎችን አቀናጅተው የሚያቀርቡ ጥቂት መምህራንና ክሂሎችን አቀናጅቶ የማያቀርቡ በርካታ መምህራን እንዳሉ የታወቀ ሲሆን የተማሪዎቹም የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀባበል ጥሩና መጥፎ መሆን እንደ መምህራኑ የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ጥሩና መጥፎ መሆን የተወሰነ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

በመሆኑም የተመራማሪዋ ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብና የተማሪዎችን አቀባበል መፈተሽ ላይ የሚያተኩር ሲሆን ይህ ጥናት አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና እና የክፍል ውስጥ አቀራረብ ላይ ስለሆነ፤እንዲሁም በክፍል ደረጃና በጊዜ ስለማይገናኝ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡

2ኛ.አታክልቲ መኮንን (1998) "የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛን የማስተማር ስነ-ዘዴ አተገባበር ፍተሻ" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት ነበር፡፡ የጥናቱ ዓላማም የቋንቋ ክሂሎችን እንዴት እንዳቀረቧቸው የሚቃኝ ነው፡፡የጥናቱ ወሰንም አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኙ ሶስት ትምህርት ቤቶች ላይ ሲሆን ከሶስቱ ትምህርት ቤቶች ሁለት ሁለት መምህራንን በመውሰድ ምልከታ በማድረግ፣ቃለመጠይቅ በማቅረብ መረጃውን ሰብስቧል፡፡ያገኘው ውጤትም መምህራኑ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅተው እንደማያቀርቧቸው የሚያሳይ ነው፡፡

በመሆኑም የአታክልቲ ጥናት የሚያተኩረው የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛን የማስተማር ስነ-ዘዴ አተገባበር ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ግን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና እና የክፍል ውስጥ አቀራረብ ላይ

ስለሆነ፤እንዲሁም በክፍል ደረጃና በጊዜ ስለማይገናኝ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡

3ኛ.ሞገስ አመራ (1999) "የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና" ለማረጋገጥ ጥናት አድርገዋል፡፡ በጥናታቸው ውጤትም በሀገራችን ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት እርከን የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች በውህደት የሚቀርቡበት ሁኔታ ትኩረት ያላገኘ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ይህ ጥናት በአንጻሩ ክሂሎች በተናጠል ከሚቀርቡ ይልቅ በቅንጅት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ አመላክቷል፡፡

የሞገስ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች ውህደት ላይ በማተኮሩ ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ጥናት ከተመራማሪው ጥናት የሚለየው የተማራማሪው ጥናት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ ሙከራዊ ጥናት ላይ ስለሚያተኩርና የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና እና የክፍል ውስጥ አቀራረብ ላይ ስለሆነ እንዲሁም በክፍል ደረጃ፣በጊዜና በቦታ ልዩነት ስላለው ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡

4ኛ. እሸቴ መብራት (2003) "የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረው ሚና"በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት ነበር፡፡የጥናቱ ዋና አላማ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ በማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ በወረታ በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሙከራዊ ጥናት አድርገዋል፡፡የጥናቱ ውጤትም የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ካላቸው ትስስርና ዝምድና አንጻር በተናጠል ከማቅረብ ይልቅ በውህደት ቢቀርቡ ለክሂሎቹ መጎልበት የላቀ ሚና እንዳለው አሳይቷል፡፡

የእሸቴ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች ውህደት ላይ በማተኮሩ ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ጥናት ከተመራማሪው ጥናት የሚለየው የተማራማሪው ጥናት በአስረኛ ክፍል የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ ሙከራዊ ጥናት ላይ ስለሚያተኩርና የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል

ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና እና የክፍል ውስጥ አቀራረብ ላይ ስለሆነ  እንዲሁም በክፍል ደረጃ፣በጊዜና በቦታ ልዩነት ስላለው ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ጥናቶች ቀደም ብዬ በዝርዝር ከእያንዳንዱ ጥናት ጋር በጠቀስኩት መልኩ የአታክልቲ(1998) እና የትዝታ (2003) ጥናቶች በስያሜም ይሁን በይዘት ከዚህ ጥናት ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም፡፡ነገር ግን የእሸቴ (2003)እና የሞገስ (1999) ጥናት በስያሜ የሚመሳሰል ሲሆን በአጠናን ዘዴውና በጥናቱ ትኩረት ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከላይ ከቀረቡት ጥናቶች በርዕስ፣ በተጠኝዎች የትምህርት ደረጃ ፣የጊዜ ርዝመትና የርዕስ አመራረጥ ከተጠቀሱት ጥናቶች በብዙ መልኩ እንዲለይ ያደርገዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት፣የአጠናን ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በጥናቱ ተተኳሪ የሚሆኑትን የመረጃ ምንጮች አመራረጥ፣የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አይነት፣የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ፣የጥናቱ አጠናን ስልት በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ትኩረት በ2007 ዓ.ም ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች መማሪያነት የተዘጋጀውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ መገምገምና የክፍል ውስጥ አተገባበርን መፈተሽ ነው፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ የተደረገው የአጠናን ዘዴ ቅይጥ የምርምር ዘዴ ሲሆን በዋናነት አይነታዊ ምርምር እና በደጋፊነት መጠናዊ ምርምር አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡በዚህ ጥናት ቅይጥ የምርምር ዘዴ መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት ምርምሩ የሚተነተነው በገለጻ እና በቁጥር መረጃ ትንተና ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት የጥናቱ አቀራረብ ገላጭ ስልትን የተከተለ በመሆኑ ነው፡፡ አጥኝዋ በተጠቀሰው መጽሀፍ ላይ እንዲሁም የክፍል ውስጥ አተገባበሩ ላይ ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት ለግምገማው በሚዘጋጁት መስፈርቶች አማካኝነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በአይነት በአይነት በማድረግ መተንተን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡መጠናዊ ምርምር በቁጥር የመረጃ ትንተና ላይ የተመሰረተ የምርምር አይነት በመሆኑ አጥኝዋም በቁጥር ለምትገልጸው የመረጃ ትንተና አመቺ ሆኖ ስላገኘችው ልትመርጠው ችላለች፡: በመሆኑም በጥናቱ ቅይጥ የምርምር ዘዴን የሚከተለውን Cress well,(2009) እና የያለው (2001) የምርምር መጻህፍት ለጥናቱ መነሻ በግብዓትነት አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡

## 3.2 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች

የጥናቱ የመረጃ ምንጮች የሰነድ ፍተሻ፣በመምህራን የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ ከመጽሐፉ አዘጋጆች የሚገኝ ቃለ መጠይቅና ከምልከታ የሚገኙ የመረጃ ግብዓቶች ናቸው:: እንዲሁም የንድፈ ሀሳባዊ መሰረቶች ላይ በመመስረት ነው፡፡በመሆኑም የሚፈለጉት መረጃዎች ከሰነድ ፍተሻ፣ከጽሁፍ መጠይቅ፣ከቃለመጠይቅና ከምልከታ ከተሰበሰቡ በኋላ በአስፈላጊው ቅደም ተከተል ተዘርዝረው በገላጭ ስልት ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## 3.3.የጥናቱ ናሙና አመራረጥ

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ለጥናቱ ተገቢውን መረጃ ሊሰጡ ወይም ሊያስገኙ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸው ምንጮች በተለያዩ የናሙና አመራረጥ ስልቶች ተመርጠዋል፡፡ የእያንዳንዱ የናሙና አመራረጥ ሂደትም ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

### 3.3.1.የጥናቱ ክልል አመራረጥ

አጥኝዋ በአዲስ አበባ ከተማ በቦሌ ክፍለ ከተማ ረዘም ላለ ጊዜ በመምህርነት ሙያ የሰራች በመሆኑ ከመምህራን አገኛቸዋለሁ ብላ ላሰበቻቸው መረጃዎች ከሌሎች ክፍለ ከተሞች በተሻለ መልኩ መረጃዎችን ማግኘት እንደምትችል በመገመቷ በቦሌ ክፍለ ከተማ የጥናቱ ክልል እንዲሆን በአመቺ የናሙና ዘዴ (Convienece sampling method) ተመርጦ የጥናቱ ቦታ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

### 3.3.2. የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ስር ከሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ውስጥ አራት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ተመርጠዋል፡፡እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተመረጡት አመች የናሙና ስልትን (Convienece sampling method) መሰረት በማድረግ ነው፡፡አራቱም ትምህርት ቤቶች ከአጥኝዋ መኖሪያ ጋር ቅርበት ያላቸው በመሆናቸው መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቀላል ይሆናል ብላ በመገመቷ ነው፡፡የተመረጡት ትምህርት ቤቶች በቦሌ ክፍለ ከተማ የሚገኙ

ሲሆኑ ህዳሴ፣ጎሮ ፣ቦሌ ለሚ እና ምስራቅ በር ቁጥር ሁለት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡

### 3.3.3. የክፍል ደረጃ አመራረጥ

አጥኚዋ በመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክልትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ለስድስት ዓመታት ያህል ስታገለግል መቆየቷ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ በዚህ ምክንያት ከዚህ በፊት በአገልግሎት ላይ ውሎ የነበረውን የ"7ኛ"ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ በቅርበት ታውቀዋለች፡፡

በመሆኑም በመጽሐፉ ውስጥ ተካተው የነበሩ የአንብቦ መረዳት ይዘቶች አቀራረብ ችግሮች አዲስ በተዘጋጀው መመሪያ መጽሐፍ ውስጥ ምን ያህል መሻሻል እንዳሳዩ ሳይንሳዊ መርሆዎችን በመከተል መመርመር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም  የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ  ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጧል፡፡

### 3.3.4. የመምህራን አመራረጥ

በ2010 ዓ.ም በህዳሴ፣በጎሮ፣በምስራቅ በር ቁጥር ሁለትና በቦሌ ለሚ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ"7ኛ" ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስድስቱም በጠቅላይ የናሙና ስልት በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል፡፡

### 3.3.5. የመጽሀፉ አዘጋጆች አመራረጥ

በ2007ዓ.ም የተዘጋጀውን የ"7ኛ" ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ አስማምቶ የማዘጋጀት ስራውን ያከናወኑት አንዲት መምህርትና አንድ የስርዓተ ትምህርት ባለሙያ ሲሆኑ ከአዘጋጆች ቁጥር አነስተኛነት አንጻር በጠቅላይ የናሙና ስልት ሁሉንም በመውሰድ ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸዋል፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ አራት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በስራ ላይ ውለዋል፡፡ እነሱም የሰነድ ፍተሻ፣ የጽሁፍ መጠይቅ ቃለ መጠይቅና ምልከታ ናቸው፡፡ከእነዚህም መካከል የሰነድ ፍተሻው በዋናነት ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በአጋዥነት አገልግለዋል፡፡ ተከታዩ ክፍልም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በዝርዝር ያሳያል፡፡

### 3.4.1. የሰነድ ፍተሻ

የሰነድ ፍተሻ ለዚህ ጥናት ዓላማ ከግብ መድረስ ዋናውን ድርሻ የያዘ ነው፡፡ይህም የሚያተኩረው በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብን በተለያዩ መረጃዎች አስደግፎ በመተንተን ላይ ይሆናል፡፡ለዚህም እንዲያግዝ የክሂሎቹ ይዘቶች አቀራረብ በተለያዩ ንድፈ ሃሳቦች አማካኝነት ተቃኝተዋል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ንድፈ ሀሳቦቹን መሰረት ያደረጉ የመገምገሚያ መስፈርቶች ተዘጋጅተው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ይኸውም የይዘት ተገቢነት፣ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ ዝግጅት ለአንብቦ መረዳትና ለመጻፍ ክሂል የይዘት ቅንጅታዊ አቀራረብ የሰጡት ትኩረት ፣የመልመጃዎቹ አቀራረብ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀት ያላቸው እገዛ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀት ያላቸው እገዛ የሚሉት ዋና ዎቹ ናቸው፡፡

### 3.4.2. የጽሁፍ መጠይቅ

ለመምህራን የቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ በምዕራፍ ሁለት ውስጥ የተነሱትን ጽንሰ ሀሳቦች መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡መጠይቁ ከሰነድ ፍተሻው የተገኘውን መረጃ የበለጠ ለማረጋገጥ፣ ለማጠናከርና ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት ታስቦ ተግባራዊ የሆነ ነው፡፡በመሆኑም ለዚህም አላማ የሚውሉ የጽሁፍ መጠይቆች 12 በዝግ ወይም ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎችና 2 ደግሞ በልቅ ወይም በነጻ የአቀራረብ ስልት ተዘጋጅተው ለጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ቀርበው ምላሽ እንዲሰጥባቸው ተደርጓል፡፡ እነዚህን የአጠያየቅ ስልቶች መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት ዝግ የአጠያየቅ ስልት በቀላሉ ለመተንተን አመቺ በመሆኑ ሲሆን ልቅ የአጠያየቅ ስልትን መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት ደግሞ መላሾቹ

ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ ስለሚያችል በተነሳው ርዕስ ዙሪያ አስፈላጊና ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት ስለሚረዳ ነው፡፡

### 3.4.3 ምልከታ

ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ከመማር ማስተማሩ ሂደት ለመሰብሰብ ምልከታ በዋናነት የሚመረጥ ዘዴ ነው፡፡ምልከታው በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሲሆን ሁሉም የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተካተዋል፡፡ለምልከታው የሚያገለግል ቅጽም የተዘጋጀው ከCelece-muricia(1991) ሃሳብ በመውሰድ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን አቀናጅቶ ለማስተማር የሚረዱ ብልሃቶችን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ለምልከታ የወጣውን የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በማድረግ እያንዳንዱ ተጠኚ መምህር በሚያስተምርበት ክፍል ለሶስት ለሶስት ጊዜያት ምልከታው ተከናውኗል፡፡የምልከታው አላማም የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በንባብ ክፍለ ጊዜ በሚያስተምሩበት ወቅት አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር ሆን ተብሎ እና ታቅዶበት ቅንጅታዊ አቀራረብ መኖር አለመኖሩን ለመረዳት ነው፡፡(የምልከታ ቅጹን በአባሪ አምስት ይመልከቱ)፡፡

### 3.4.4 ቃለ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት በመዛግብት ፍተሻ የተገኙ መረጃዎችን ለማገዝ ከጽሁፍ መጠይቅ በተጨማሪ ቃለ መጠይቅም የዚህ ጥናት አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን አገልግሏል፡፡ አጥኚዋ ቃለመጠይቅ ያደረገችው ለመማሪያ መጽሀፉ አስማምቶ አዘጋጆች ሲሆን የቃለ መጠይቁ ዋና ዓላማ በመማሪያ መፅሐፉ ዝግጅት ወቅት አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር ከማቀናጀት አንጻር በማዘጋጀት ሂደት ላይ አስማምቶ አዘጋጆቹ ምን ትኩረት እንደሰጡና የጥያቄዎቹን የአቀራረብ ስልት በተመለከተ የተከተሏቸውን የአሰራር ዘዴዎች መኖር አለመኖራውቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡ጥያቄዎቹ ዘጠኝ ሲሆኑ የቃለ መጠይቁ አይነትም በከፊል የተደራጀ ነው፡፡ ይህም የተመረጠበት ምክንያት እንደ seligar and Shohamy (1989) በዚህ የቃለ መጠይቅ አይነት ለመነሻነት በሚያገለግሉ ጥያቄዎች አማካኝነት የመላሾችን ማብራሪያ በመመርኮዝ ሌሎች ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን

ለማንሳትና ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸውን ነጥቦች በቃለ መጠይቁ ወቅት በደንብ ተገንዝቦ ለማለፍ እንዲያስችል ነው፡፡

የቃለ መጠይቁን አቀራረብ ሂደት በተመለከተ ጥያቄዎቹ በጥናቱ አቅራቢ አማካኝነት አንድ በአንድ እየቀረቡ ተጠያቂዎቹ ማብራሪያ የሰጡባቸው ሲሆን ምላሻቸውም በመቅረጸ ድምጽ ከተቀረጸ በኋላ ወደ ጽሁፍ ተመልሶ ለትንተና ቀርቧል፡፡ ቃለ መጠይቁም እንደ ምልከታና የጽሁፍ መጠይቁ ለጥናቱ እንዲስማማ ሆኖ ከተዘጋጀ በኋላ በአማካሪዎቹ ተገምግሞና ማሻሻያ ተደርጎበት በግልጋሎት ላይ ውሏል፡፡(አባሪ 6ን ይመልከቱ)

## 3.5.የመረጃ አተናተን ዘዴ

### 3.5.1. የመረጃ አለያየት እና ለትንተና ዝግጁ ማድረግ

የዚህ ጥናት ዋና የመረጃ ምንጭ" መጽሀፍ ግምገማ" መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡የሰነድ ፍተሻው ዋና አላማም ለጥናቱ በተመረጠው የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካቱት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብን በጥልቀት መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ በመዛግብት ፍተሻ የተገኙት መረጃዎች በዓይነት በዓይነት ተደራጅተው እንዲቀርቡ ሆኗል፡፡በመጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችና ይዘቶች አቀራረብ Grellet (1991)፣Masdon(1983) እና Celece-Muricia(1991)ጸሀፍት ባስቀመጧቸው መስፈርቶች አማካኝነት የይዘቶችንና የመልመጃዎችን አቀራረብ መሰረት በማድረግ ተደራጅተው ተተንትነዋል፡፡

### 3.5.2. የመተንተኛ ስልት

የጥናቱን መረጃዎች ለመተንተን ገላጭ የመረጃ መተንተኛ ስልት በተግባር ላይ ውሏል፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ በመዛግብት ፍተሻ የተገኙት መረጃዎች ከአጥኝዋ እይታ አንጻር በገላጭ የአተናተን ስልት ከተተነተኑ በኋላ የጽሁፍ መጠይቁን ከሞሉት መምህራን እይታ አንጻር የተገኙት መረጃዎች የቁጥር መለኪያ ተሰጥቷቸው በመቶኛ ተገልጸዋል፡፡እንዲሁም በመጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንደ አስፈላጊነቱ በትንታኔው ጣልቃ መግባት በሚገባቸው ቦታ እየተተነተኑ የቀረቡ ሲሆን በቃለ መጠይቅና በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎችም የመዛግብት ፍተሻውን በሚያጠናክር መንገድ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ የክፍል ውስጥ አቀራረብን በተመለከተ ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ

የተገኙት መረጃዎች በገላጭ የአተናተን ስልት የቀረቡ ሲሆን በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኙት መረጃዎች ከአጥኝዋ እይታ አንጻር የቁጥር መለኪያ ተሰጥቷቸው በመቶኛ ከተተነተኑ በኋላ በገላጭ የአተናተን ስልት ተገልጸዋል፡፡

### 3.5.3. የትንተናው ትኩረት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ላይ በመሆኑ የትንተናው ትኩረት በአንብቦ መረዳት መልመጃዎች እና የይዘቶች አቀራረብ ላይ ነው፡፡ይኸውም ትኩረት ያደረገው ይዘቶቹ ለተማሪዎቹ ደረጃ ተስማሚ ናቸው? አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል የይዘት ቅንጅታዊ አቀራረብ አላቸው? የመልመጃዎቹ አዘገጃጀት የተለያዩ የማስተማሪያ ብልሃቶችን አካተዋል? የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን አቀናጅቶ ለማቅረብ አጋዥ ናቸው? የሚሉት ነገሮች በዋናነት ትኩረት የተደረገባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ እንዲሁም የመምህራን የክፍል ውስጥ አቀራረብ ላይ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን አቀናጅቶ ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ላይ ትንተናው ትኩረት አድርጓል፡፡

# ምዕራፍ አራት፤የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1. የመረጃ ትንተና

ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ2007 ዓ.ም በተዘጋጀው የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ መገምገም ነው፡፡

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በምዕራፍ ሶስት ላይ እንደተገለጸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ በዋናነት ሰነድ ፍተሻ ሲሆን አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያዎቹ ደግሞ የፅሁፍ

መጠይቅ፣ ቃለመጠይቅና ምልከታ ናቸው፡፡አጥኝዋ የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍን ፣የመምህሩን መምሪያና መርሃ ትምህርቱን የሰነድ ፍተሻ በማድረግ፣የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደትን በመመልከት ለመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ በማቅረብና ለመማሪያ መጽሀፉ አዘጋጆች ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃዎችን ሰብስባለች፡፡

የዚህ ክፍል አላማም የተሰበሰቡትን መረጃዎች መተንተን ነው፡፡በዚህ ክፍል ውስጥ ለመምህራንና ለመጽሀፉ አዘጋጆች የቀረቡ መጠይቆች በሰነድ ፍተሻው ወቅትም አገልግሎት ላይ የዋሉ ሲሆን መምህራንን በሚመለከት በዋናነት ከምልከታ የተገኘው መረጃና እንዳስፈላጊነቱ ከመምህራኑ  የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎችም አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ በመጽሀፉ ውስጥ የተካተቱትን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረባቸውን አስመልክቶ የተገኙ መረጃዎች ከመተንተናቸው በፊት ስለ መማሪያ መጽሐፉ ጥቂት መረጃዎችን እንመለከታለን፡፡

## 4.1.1.የመማሪያ መጽሐፉ አጠቃላይ ዳራ

የሰባተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በመውሰድ በአዲስ አበባ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ለከተማ አውድ ተስማምቶ የቀረበ ሲሆን አገልግሎት መስጠት የጀመረው በ2008 ዓ.ም ነው፡፡መጽሀፉ ወደ ዋናው የትምህርት ክፍሎች ከመግባቱ በፊት በመግቢያው ላይ የስርዓተ ትምህርቱን መሰረታዊ መርሆዎች፣ከትምህርት ቤት ውጭ የተማሪዎችንና የወላጆችን ትምህርታዊ ተግባራት እንዲሁም የመጽሐፉን የይዘት አደረጃጀት በማስተዋወቅ ይጀምራል፡፡ ዋናውን የመጽሐፉን ትምህርታዊ አቀራረብ ስንቃኝ ደግሞ አስር ምዕራፎች ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ምዕራፍ በሶስት ሳምንት፣ አንዱ ሳምንት ደግሞ በሶስት ቀናት ተከፋፍሎ  እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ መጽሐፉ በአመት ውስጥ በሰላሳ ሳምንት ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን የመጽሀፉ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲታይ ሰባት ዋና ዋና የቋንቋ ይዘቶች አካቶ ይዟል፡፡እነሱም፡- የቃላት ጥናት፣አንብቦ መረዳት፣የቃላት እውቀት፣ መጻፍ፣ አቀላጥፎ ማንበብ፣ቃላዊ ክሂሎች (መናገርና ማዳመጥ) እና ሰዋስው ናቸው፡፡ሌላው መጽሀፉ በመጨረሻ ገጾች ላይ የተለያዩ የቃላትን ፍች የሚያሳዩ ሙዳዬ ቃላትና ዋቢ መጻህፍትን ይዟል፡፡በአጠቃላይ መጽሀፉ 237 ገጾች አሉት፡፡

## 4.1.2.የተተኳሪ መምህራን ዳራዊ መረጃ

ሰንጠረዥ ፡- 1. የጽሁፍ መጠይቅ የሞሉ መምህራን አጠቃላይ መረጃ

| ፆታ | እድሜ | በዋናነት የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ | የአገልግሎት ዘመን በዓመታት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | በሰተፍኬት | በዲፕሎማ | በዲግሪ |
| ሴ | 57 | አማርኛ | 22 | 6 | 7 |
| ሴ | 48 | አማርኛ | | 20 | 10 |
| ሴ | 53 | አማርኛ | | 24 | 10 |
| ሴ | 43 | አማርኛ | | 20 | 5 |
| ሴ | 48 | አማርኛ | | 10 | 5 |
| ሴ | 35 | አማርኛ | | 10 | 4 |

ከሰንጠረዥ አንድ እንደምንረዳው ተተኳሪ መምህራኑ በዋናነት የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ነው፡፡ የትምህርት ደረጃቸውን በተመለከተም ስድስቱም የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው እንደሆነ ታውቋል፡፡የመምህራኑ የአገልግሎት ዘመንም ከ14 እስከ 35 አመታት ባለው ውስጥ ያገለገሉ ናቸው፡፡በመሆኑም ቋንቋን በማስተማር ከፍተኛ ልምድ ያካበቱ በመሆናቸው የሚሰጡት መረጃ ለጥናቱ ተገቢና ተዓማኒ እንዲሆን ይረዳል ተብሎ ይገመታል፡፡

## 4.1.3. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የንባብ ክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ

በ2007ዓ.ም የተዘጋጀው የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በአስር ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው፤በውስጡም ሰላሳ ምንባቦችን አካቶ ይዟል፡፡በሁሉም

ምዕራፎች ስር የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ለዚህ የመረጃ ትንተና እንዲያመች አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አቀራረብ ትንተና በሚል ንዑስ ርዕስ ለይቶ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

## 4.1.4. አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አቀራረብ ትንተና

የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ቅድመ ንባብ፣የንባብ ጊዜና ድህረንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተ የትምህርት አቀራረብ እንዲሆን የመስኩ ምሁራን የሚገልጹ ሲሆን በእነዚህ አቀራረብ ማስተማር ደግሞ የተሻለ ውጤታማ መሆኑን Lindsay and Knight (2006)ገልጸዋል፡፡

የዚህ መጽሀፍ አቀራረብም ሲታይ ከጠቅላላው ሰላሳዎቹ ምንባቦች ውስጥ ሁሉም ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች አላቸው፡፡በቅድመ ንባብ ጊዜ መካሄድ ያለባቸው ክንዋኔዎች በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነቃቃት፣ቀደምት እውቀታቸውን በመጠቀም የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ እንዲገምቱ ማስቻል ነው፡፡በመሆኑም በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከሁሉም ምንባቦች በፊት መቅረባቸው ብቻ ሳይሆን የማንበብ ፍላጎት በማነቃቃት የምንባቦቹን ፍሬ ሀሳቦች እንዲገምቱ የሚያስችሉ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች አቀራረብ ማሳያ እንዲሆኑ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

*ምዕራፍ ስድስት ገጽ 109 "ከሞት ጋር ድርድር" በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል? እንዲሁም ገጽ 121 ፊደል ተራ ሀ.በአካባቢያችሁ በሰዎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሄ የሚያገኙት እንዴት ነው?" ፊደል ተራ ለ.በስዕሉና "በላ ልበልሃ" በሚለው ርዕስ መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት ያለ ይመስላችኋል?"*እነዚህና ሌሎች መሰል ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ባህርይ የተማሪዎችን ቀደምት ልምድ የሚመለከቱ ቀጥሎ ወደሚማሩት ትምህርት የሚያመላክቱ የተማሪዎችን የመማር ሂደት በቅድሚያ የሚያመቻቹ ናቸው፡፡

እነዚህ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች የተማሪዎችን ቀደምት እውቀት ከጽሁፎች ይዘቶች ጋር በማያያዝና በማነቃቃት የምንባቦቹን ፍሬ ሀሳቦች እንዲገምቱ የሚያስችሉ መሆናቸውን

መገንዘብ ይቻላል፡፡ጥያቄዎቹም ምንባቦቹ የሚመልሷቸው በመሆናቸው ተማሪዎች ቀደምት እውቀታቸውን ከምንባቡ ሀሳብ ጋር እንዲያዛምዱ ጽሁፉን እንዲገምቱ የሚረዱ ናቸው፡፡

ከዚህ በመቀጠል በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የንባብ ጊዜ ተግባራት እንመለከታለን፡፡የንባብ ጊዜ ተግባራት መምህራን ተማሪዎቻቸውን በንቃት ላይ የተመሰረተ ንባብ እያካሄዱ መሆናቸውን የሚቆጣጠሩበትና ተማሪዎቹ የበለጠ ለንባብ እንዲነሳሱ የሚያግዙ ተግባራትን የሚያከናውኑበት ጊዜ ነው፡፡ስለዚህ በሰባተኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የንባብ ጊዜ ተግባራት አቀራረብን አስመልክቶ ምሳሌዎችን እንመልከት፡፡

*"መስህቦቻችን" በሚል ርዕስ የቀረበውን ገላጭ ጽሁፍ ለዋና ዋና ሀሳቦች ትኩረት በመስጠት ድምጽ ሳታሰሙ በየግላችሁ አንብቡ፡፡(ገጽ 2)"ጉዞ ወደ ሀዋሳ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በእያንዳንዱ የጉዞ መዳረሻ ሊታዩ የሚችሉ ነገሮችን ቀድማችሁ በመተንበይ ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡(ገጽ 9)"የአፈር እንክብካቤ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምጽ ሳታሰሙ በማንበብ በየአንቀጹ ያሉ ዋና ዋና ሀሳቦችን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡ የሚሉና ሌሎችንም ትዕዛዛት የያዙ ክንውኖች ቀርበዋል፡፡*

እነዚህ የንባብ ጊዜ ተግባራት አቀራረብ ተማሪዎቹ እያነበቡ እያሉ ወደፊት የሚሆነውን በመተንበይ እንዲያነቡና በየአንቀጹ ያሉ ዋና ዋና ሀሳቦችን እንዲጽፉ የሚያደርጉ ናቸው፡፡እነዚህም አቀራረቦች ተማሪዎቹ የበለጠ ለምንባቡ እንዲነሳሱ እገዛ ያደርጋሉ፡፡

ድህረ ንባብ ተግባራት በአብዛኛው የግምገማ ስራዎችን የሚይዝ ሲሆን የተነበበውን ምንባብ መነሻ በማድረግ ከክፍል ውጭ ካለው አለም ጋር በማዛመድ ሃሳብ እንዲያቀርቡባቸው የሚያችሏቸው ጥያቄዎች የሚካተቱበት ነው፡፡አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች የምንባቡን ዓላማ የጸሀፊውን አመለካከት የአንባቢውን አረዳድና ሌሎችንም ነጥቦች የሚዳስሱ በመሆናቸው በተለያየ መንገድ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ይኸውም በክፍት ጥያቄዎች፣በምርጫ ሰጪ፣በእውነት /ሀሰት፣ በአዛምድ እና በሌሎችም የአቀራረብ ስልት እንደምንባቡ ባህሪ ጥያቄዎቹ ተለዋዋጭነት ሊኖራቸው ይችላል፡፡በመሆኑም በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የጥያቄዎቹ አቀራረብ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል ፡፡

ሰንጠረዥ ፡-2. በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ባህርይ

| ምዕራፍና ርዕስ | የመልመጃ ጥያቄ አይነቶች | | | | በየምዕራፉ ያሉ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | ክፍት ጥያቄዎች | ዝግ ጥያቄዎች | | | |
| | | እውነት/ሀሰት | አዛምድ | ምርጫ | |
| ምዕራፍ አንድ ተፈጥሮን ማድነቅ | 21 | 3 | - | - | 24 |
| ምዕራፍ ሁለት የቤተሰብ ምጣኔ | 15 | 4 | - | 3 | 22 |
| ምዕራፍ ሶስት ኤች.አይ.ቢ./ኤድስና ማህበራዊ ቀውሶች | 19 | - | - | - | 19 |
| ምዕራፍ አራት ታዋቂ የኪነጥበብ ሰዎች | 20 | - | - | - | 20 |
| ምዕራፍ አምስት ውኃና ጥቅሙ | 11 | 4 | 6 | 4 | 25 |
| ምዕራፍ ስድስት ማህበራዊ ግንኙነት | 21 | | | | 21 |
| ምዕራፍ ሰባት ሱስ | 29 | - | - | - | 29 |
| ምዕራፍ ስምንት አርበኝነት | 31 | | | | 31 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ምዕራፍ ዘጠኝ ተላላፊ በሽታዎች | 18 | | | 13 | 31 |
| ምዕራፍ አስር ቃላዊ ግጥም | 16 | - | - | - | 16 |
| ድምር | 201 | 11 | 6 | 20 | 238 |
| በፐርሰንት | 84.5% | 4.6% | 2.5% | 8.4% | 100% |

ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አስር ምዕራፎች ቀርበዋል፡፡በእነዚህ ምዕራፎች በተካተቱ ምንባቦች ውስጥ 238 አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡እነዚህ ጥያቄዎችም በክፍት 201(84.5%) ዝግ 37(15.5%) ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በዝግ የቀረቡት ጥያቄዎች በእውነት ሀሰት፣በአዛምድና በምርጫ የቀረቡ ናቸው፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ከፍተኛው የአንብቦ መረዳት ጥያቄ በክፍት መልክ መቅረቡን የሰነድ ፍተሻው ያመለክታል፡፡

ይህም አቀራረብ Madoson (1983) እንደገለጹት ክፍት ጥያቄዎች መላሹ ነጻ ሆኖ ያለ ገደብ የራሱን ሀሳብ በተረዳው መንገድ የሚገልጽባቸው የጥያቄ አይነቶች በመሆናቸው የአንባቢውን የመተንበይ፣የመገመት፣የማብራራትና የማጠቃለል ችሎታዎችን ለማዳበር ከዝግ ጥያቄዎች የተሻሉ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡በመሆኑም በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎችም ሀሳባቸውን በነጻ ለመግለጽ አመችነታቸው ከፍ ያለ መሆኑን የሰነድ ፍተሻው ያመለክታል፡፡ ከዚህ በመቀጠል አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች አቀራረብን ማሳያ እንዲሆኑ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ ስድስት ገጽ 115 "ከሞት ጋር ድርድር" በሚል ርዕስ የቀረበውን የምንባብ ጭብጥ በራሳችሁ አገላለጽ በአንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡ገጽ 137 ፊደል ተራ ለ."ጫት መቃምና መዘዙ" ከሚለው ምንባብ ካወጣችኋቸው ዋና ዋና ሀሳቦች ውስጥ አንዱን ወስዳችሁ በምክንያትና ውጤት ስልት በራሳችሁ አገላለጽ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡" እነዚህና መሰል ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

የእነዚህ ጥያቄዎች አቀራረብ የምንባቡን ዋና ሀሳብ ወይም ጭብጥ መሰረት በማድረግ በራስ አገላለጽ እንዲጽፉ የሚረዳ ነው፡፡ይህም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማዳበር ያግዛል፡፡

*ምዕራፍ ስድስት ገጽ 125 ተግባር 2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች "በላ ልበላሃ" በሚለው ምንባብ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡*

*1. ከሳሽ፣"መጣሁ እንደ ውሃ ስፈስ፣*

*እንደጋግ ስነፍስ፣"ሲል ከሳሹ ስለራሱ ምን መግለጹ ነው?*

*2. "እንዴት ለቀበሮ የላት ገላ፣*

*ትገባለች አርባ ክንድ ምሳ"ብሎ ተከሳሽ ሲመልስ ምን ማለቱ ነው?*

*3.ተከሳሽ "ፍየል መንታ ትወልዳለች፣*

*አንዱን ለመጣፍ አንዱን ለወናፍ፣*

*መጣፉ እኔ ወናፉ አንተ"ሲል ከሳሹን ምን እያለው ነው?*

*ይህ የጥያቄ አቀራረብ መተርጎምና ማብራራትን መሰረት በማድረግ የቀረበ ነው፡*እነዚህ ብልሀቶች ተማሪዎች ስላነበቡት ጽሁፍ ዝርዝር ማብራሪያ፣ትርጉምና ትንተና በጽሁፍ መስጠት የሚያስችሉ በመሆናቸው አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ችሎታን ለማዳበር ያግዛሉ፡፡

*ምዕራፍ ስምንት ገጽ 168 ተግባር 2 ለሚከተሉት ጥያቄዎች የተብራራ መልስ ጻፉ፡፡ ፊደል ተራ ሀ. የሀገር ፍቅር ስሜትን ለመግለጽ ከአርበኝነት ተግባርና ከበጎ አድራጎት ተግባር የትኛው የተሻለ ይመስላችኋል?ለምን? ፊደል ተራ ለ. በዓለም የውድድር አደባባዮች ተሰልፈው ድል ማድረግ የተሳናቸውን አትሌቶች የሀገር ፍቅር ስሜት የላቸውም ማለት ይቻላል? ለምን? የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡ (አባሪ 3ን ይመልከቱ፡፡)*

እነዚህ ጥያቄች ከምንባቡ የወጡ ሆነው ምላሻቸውም መመራመር የሚያስፈልጋቸውና የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ሲሆኑ በራስ አገላለጽ ሀሳብን በጽሁፍ ለመግለጽ የሚያግዙ ናቸው፡፡ይህም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያግዛሉ፡፡

ቀጥሎ ደግሞ ለመምህራን የቀረበውን መረጃ መሰረት በማድረግ ትንታኔ ይሰጣል፡፡ለመምህራን የተዘጋጁት ጥያቄዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሰንጠረዥ፡-3. ለአንብቦ መረዳትና ለመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ እንዲሆኑ የተዘጋጁት መልመጃዎች የትምህርቱን አላማ የማሳካት ብቃታቸው

| ተ.ቁ | ጥያቄዎቹ | ድግግሞሽ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3 | ለአንብቦ መረዳትና ለመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ እንዲሆኑ የተዘጋጁት መልመጃዎች የትምህርቱን ዓላማ የማሳካት ብቃታቸው | 1(16.7%) | 3(50%) | 1(16.7%) | 1(16.7%) | - |
| 4 | የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ተማሪዎቹ ቋንቋውን በሚገባ እንዲካኑ ለማድረግ ያላቸው አቅም | 2(33.3%) | 2(33.3%) | - | 2(33.3%) | - |
| 5 | መጽሐፉ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያስችሉ በቂ ይዘቶችን አሟልቶ የመያዝ ሁኔታ | 3(50%) | 1(16.7%) | 1(16.7%) | 1(16.7%) | - |
| 9 | በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ | 2(33.3%) | 2(33.3%) | 2(33.3%) | - | - |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ተገቢነት | | | | | |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በተራ ቁጥር 3 "ለአንብቦ መረዳትና ለመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ እንዲሆኑ የተዘጋጁት መልመጃዎች የትምህርቱን አላማ የማሳካት ብቃታ አላቸው ወይ" ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ በጣም ከፍተኛ 1(16.7%)፣ከፍተኛ 3(50%) እና መካከለኛ 1(16.7%) ሲሆኑ ዝቅተኛ በማለት ምላሻቸውን የሰጡት ደግሞ 1(16.7%) ናቸው፡፡በመሆኑም ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለው 4 መምህራን (66.7%) በአመዛኙ ከፍተኛ የሚል ነው፡፡ እንዲሁም በተራ ቁጥር 4 ላይ የሰጡት ምላሽ በጣም ከፍተኛ ያሉት 2(33.3%) ከፍተኛ በማለት የመለሱት 2(33.3%) ሲሆኑ ዝቅተኛ በማለት ምላሻቸውን ያሰፈሩት ደግሞ 2(33.3%) ናቸው፡፡በመሆኑም ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለው 4 መምህራን (66.7%) በአመዛኙ ከፍተኛ የሚል ነው፡፡እንዲሁም በተራ ቁጥር 5 ላይ በሰጡት ምላሽ በጣም ከፍተኛ ያሉት 3(50%)፣ከፍተኛ በማለት ምላሻቸውን የሰጡት 1(16.7%) መካከለኛ ሲሉ ምላሻቸውን የሰጡት 1(16.7%) ሲሆኑ ዝቅተኛ በማለት ምላሻቸውን የሰጡት ደግሞ 1(16.7%) ናቸው፡፡ በመሆኑም ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለው 4 መምህራን (66.7%) በአመዛኙ ከፍተኛ የሚል ነው፡፡

በተራ ቁጥር 9 በሰጡት ምላሽ በጣም ከፍተኛ ያሉት 2(33.3%) ፣ከፍተኛ በማለት የመለሱት 2(33.3%) ሲሆኑ መካከለኛ በማለት ምላሻቸውን የሰጡት ደግሞ በተመሳሳይ 2(33.3%) ናቸው፡፡ ስለሆነም ከመምህራን ምላሽ መረዳት የሚቻለው 4 መምህራን (66.7%) በአመዛኙ ከፍተኛ የሚል ሆኗል፡፡ ከዚህ ትንታኔ የምንረዳው እንደ መረጃ ሰጭዎቹ እምነት የመልመጃዎች አቀራረብ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው መሆናቸውን ነው፡፡

ይህንን ይበልጥ ለማረጋገጥ ለመማሪያ መጽሀፉ አዘጋጆች በጥያቄ ተራ ቁጥር 2 በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱትን አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂል የአቀራረብ ስልት በተመለከተ ምን አይነት አዘገጃጀት ተጠቀሙ? ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ መጽሀፉ የተዘጋጀው "EGRA" ባጠናው ጥናት መሰረት ተማሪዎቹ አንብቦ መረዳታቸውና የመጻፍ ክሂላቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ሁለቱን ክሂሎች በማስተሳሰር አንብበው የተረዱትን በጽሁፍ እንዲገልጹ የሚያስችል የአዘገጃጀት ስልትን እንደተጠቀሙ

ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ይህም በመዛግብት ፍተሻና ከመምህራን የተገኘውን መረጃ የሚያጠናክር ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ ከሰነድ ፍተሻው፣ከጽሁፍ መጠይቁና ከቃለመጠይቁ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በመጽሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ አቀራረብ ከምንባቡ በፊት ስለምንባቦቹ ይዘት የመገመት የቅድመ ንባብ ተግባራት፣በምንባቡ ላይ የተመሰረቱ

የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በማካተት ከምንባቡ ይዘት በመነሳት እንዲጽፉ የሚያግዙ ተግባራት ቀርበዋል፡፡እነዚህም የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት በመቀስቀስ እንዲገምቱ የሚያደርጉ እንዲሁም ምንባቡን መሰረት በማድረግ በራሳቸው አገላለጽ እንዲያብራሩና የምንባቡን ጭብጥ አሳጥረው እንዲጽፉ የሚያግዙ ናቸው፡፡ይህም አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማሳደግ እንዲተገበሩ የቀረቡት የመልመጃ ጥያቄዎች ክሂሎቹን ለማዳበር በሚያስችል መልኩ የቀረቡ መሆናቸውን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

የቋንቋ ትምህርት ይዘት ለልምምድ በሚቀርብበት ጊዜ በቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው የትምህርቱ ዓላማ ነው፡፡ የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ የመለማመጃ ጥያቄዎቹ ግልጽ በሆኑ መመሪያዎች መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ከዚህ አንጻር በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች መመሪያ አቀራረብ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ፡-4. በመጽሀፉ ውስጥ የሚገኙ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች መመሪያ አቀራረብ

| ተ.ቁ | የመልመጃ ጥያቄዎቹ የሚመለሱበት መንገድ | ጠቅላላ ብዛት በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | በቃል እንዲመለሱ የቀረቡ | 9 | 16.7% |
| 2 | በጽሁፍ እንዲመለሱ የቀረቡ | 36 | 66.6% |
| 3 | በምን ሁኔታ እንደሚመለሱ ያልተገለጹ | 9 | 16.7% |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4 | ጠቅላላ ድምር | 54 | 100% |

በሰንጠረዥ 4 ላይ እንደምንረዳው በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ውስጥ 9(16.7%) በቃል እንዲመለሱ፣ 36(66.6%) በጽሁፍ እንዲመለሱ፣ 9(16.7%) ደግሞ በቃል ይሁን በጽሁፍ በግልጽ ትዕዛዝ የሌላቸው መልስ እንዲሰጥባቸው ብቻ የቀረቡ ናቸው፡፡በመሆኑም በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች መመሪያ አቀራረብ አብዛኛዎቹ በጥንካሬያቸው የሚገለጹ ናቸው፡፡

በአንጻሩ ደግሞ ለልምምድ እንዲሆኑ ከቀረቡት መመሪያዎች መካከል ግልጽነት የሌላቸውና ተማሪዎቹ በምን መልኩ እንደሚተገብሩት ግልጽ ያልሆኑ መመሪያዎች እንዳሉ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡የእነዚህ መመሪያዎች ችግርም ተማሪዎች ተግባራቱን በምን መልኩ እንደሚተገብሯቸው ግልጽነት የሌላቸው ናቸው፡፡ይህም ሲባል አተገባበራቸው በቃል ይሁን በጽሁፍ፣ በተናጠል ይሁን በጥንድ፣ በግል ይሁን በቡድን እንዴት መተግበር እንዳለባቸው ግልጽ በሆነ መልኩ አለመገለጻቸው ነው፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ የመመሪያዎችን አቀራረብ በተመለከተ በተራ ቁጥር 11 ላይ ለመምህራን ለቀረበላቸው ጥያቄ ለክሂል መልመጃዎቹ ተገቢ የሆኑ መመሪያዎች ተሰጥተዋል ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ በጣም ከፍተኛ ያሉት 1(16.7%) ፣ ከፍተኛ በማለት የመለሱት 3(50%)፣መካከለኛ ሲሉ ምላሻቸውን የሰጡት 1(16.7%) ሲሆኑ ዝቅተኛ በማለት ምላሻቸውን ያሰፈሩት ደግሞ 1(16.7%) ናቸው፡፡ በመሆኑም ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለው 4 መምህራን (66.7%) በአመዛኙ ከፍተኛ የሚል ነው፡፡

በአጠቃላይ በመጽሀፉ ውስጥ ለክሂል መልመጃዎቹ የቀረቡትን መመሪያዎች በመመርመር የተገኙት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ጥሩ የሚባሉ መመሪያዎች መኖራቸውን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ግልጽነት የሌላቸው ከተማሪዎች የሚጠበቀው ተግባር እንዴት እንደሚያከናውኑት በትክክል የማይገልጹ መመሪያዎችም እንዳሉ የመረጃ ትንተናው ያመለክታል፡፡ ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኙ መረጃዎችም ይህንኑ የሚያረጋግጡ መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡

### 4.1.5.የአንብቦ መረዳት ትምህርት የይዘቶች አቀራረብ ትንተና

ለአንድ የክፍል ደረጃ የሚቀርብ የትምህርት ይዘት የተማሪዎችን ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ችሎታ፣ ፍላጎትና ዳራዊ ጉዳዮችን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡አለበለዚያ በመማር ማስተማሩ ሂደት አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ በመሆኑም የመማሪያ መጽሀፉ ይዘቶች አቀራረብ ለአብነት ያህል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

*"ምዕራፍ ሁለት "የቤተሰብ ምጣኔ" ገጽ 30 ፊደል ተራ ሀ."አንዳንድ ወላጆች ሁለቱንም ፆታ ለማግኘት ሲሉ የቤተሰብ ምጣኔ አይደግፉም" ከሚለው አገላለጽ ምን ተገነዘባችሁ? ለ.ስለቤተሰብ ምጣኔ በአሉታዊነት ከተዘረዘሩት አመለካከቶች መካከል ምናልባት እናንተ በአዎንታ የምትመለከቱት ካለ ግለጹ፡፡ምዕራፍ ስድስት ገጽ 131 የአካባቢያችሁን ማህበራዊ ግንኙነት መሰረት በማድረግ የሚከተለውን የቢጋር ሰንጠረዥ በትክክል አሟሉ፡፡*

*ምዕራፍ ስምንት "አርበኝነት" ገጽ 167 ተግባር 1"የሀገር ፍቅር መገለጫዎች "የሚለውን ሀሳብ መነሻ በማድረግ በዙሪያው ያሉትን የቢጋር ሰንጠረዦች በምንባቡ መሰረት አሟሉ፡፡ ምዕራፍ አስር "የተጻፈና ያልተጻፈ ግጥም" ገጽ 220 አንብቦ መረዳት ተግባር 1.ለ.በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውንና በግጥም የሚቀርቡ የልጆች ጨዋታዎችን ስማቸውን ተናገሩ፡፡"* እነዚህና መሰል ይዘቶች በመጽሀፉ ውስጥ ይገኛሉ፡፡

እነዚህ ይዘቶችም በአብዛኛው ከላይ ለተዘረዘሩት መሰረታዊ ነገሮች ትኩረት ተሰጥቷቸው የተዘጋጁ እንደሆኑ ያሳያል፡፡ ምክንያቱም በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ አንብቦ የመረዳት ይዘቶች በደረጃው ለሚገኙ ተማሪዎች የተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ ከግምት ውስጥ ያስገቡ፣አብዛኛዎቹ ከተማሪዎች አካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር የሚዛመዱ ይዘቶችና መልመጃዎች የተካተቱ መሆናቸው ነው፡፡ለዚህም ማሳያው በአስሩም ምዕራፎች ስር የቀረቡት ምንባቦች ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሳትፉ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ያተኩሩ በመሆናቸውና የአንብቦ መረዳት ተግባራትም ምንባቦቹን መሰረት አድርገው በመዘጋጀታቸው ነው፡፡ ይህንኑ ለማረጋገጥ ለመምህራን ለቀረበላቸው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሰንጠረዥ ፡-5. አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂሎች በቅንጅት ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶች የተማሪዎችን ሁኔታዎች ትኩረት ያደረጉ ስለመሆናቸው

| ተ.ቁ | ጥያቄዎቹ | ድግግሞሽ |
|---|---|---|

| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል የይዘት ቅንጅታዊ አቀራረብ ትምህርት ለደረጃው ተስማሚነታቸው | 2(33.3%) | 2(33.3%) | - | 2(33.3%) | - |
| 8 | አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርቡት ይዘቶች ከተማሪዎች ህይወት ጋር ያላቸው ግንኙነት | 2 (33.3%) | 2(33.3%) | 2(33.3%) | - | - |
| 1<br>2 | የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ተግባራት ዳራዊ እውቀትን ከግንዛቤ ውስጥ የማስገባታቸው ሁኔታ | 1(16.7%) | 3(50%) | - | 2(33.3%) | - |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በተራ ቁጥር 6 ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ 2 መምህራን (33.3%) በጣም ከፍተኛ፣2 መምህራን (33.3%) ከፍተኛ እና 2 መምህራን (33.3%)ዝቅተኛ የሚል ነው፡፡በመሆኑም 4 መምህራን (66.7%) በአመዛኙ ከፍተኛ የሚል ነው፡፡በተራ ቁጥር 8 ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ 2 መምህራን (33.3%) በጣም ከፍተኛ፣ 2 መምህራን (33.3%) ከፍተኛ እና 2 መምህራን (33.3%) መካከለኛ የሚል ነው፡፡ስለሆነም ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለው 4 መምህራን (66.7%) በአመዛኙ ከፍተኛ የሚል ነው፡፡እንዲሁም በተራ ቁጥር 12 ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ 1(16.7%) በጣም ከፍተኛ፣3መምህራን (50%) ከፍተኛ እና 2 መምህራን (33.3%)ዝቅተኛ የሚል ነው፡፡በመሆኑም ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለው 4 መምህራን(66.7%) በአመዛኙ ከፍተኛ የሚል ነው፡፡

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው ይዘቶቹ ለደረጃው ተስማሚ፣ከተማሪዎች ህይወት ጋር ግንኙነት ያላቸውና ዳራዊ እውቀትን ከግንዛቤ ያስገቡ መሆናቸውን ነው፡፡ይህንኑ ይበልጥ ለማረጋገጥ ለመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች በጥያቄ ቁጥር ሰባት የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በተመለከተ የቀረቡትን ይዘቶች ከተማሪዎች ፍላጎት፣ዳራ፣ችሎታ ጋር የተዛመዱ ናቸው ብለው ያምናሉ? ከሆነ እንዴት? ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ

የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡የመጽሐፉ ዝግጅት የተማሪዎችን አካባቢያዊ ሁኔታ፣ዳራዊ እውቀታቸውን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ እንደተዘጋጀ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት የአንብቦ መረዳት ይዘቶችና መልመጃዎች ፍተሻ ፣በመምህራን የተሞሉ የጽሁፍ መጠይቆችና ከመጻህፉ አዘጋጆች ቃለ መጠይቅ የተገኙት ምላሾች እንደሚያመለክቱት አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የቀረቡት ይዘቶችና ተግባራት የተማሪዎችን ፍላጎት፣ደረጃና ዳራዊ እውቀትን መሰረት በማድረግ እንደቀረቡ የትንተናው ውጤት ያመለክታል፡፡

## 4.1.6. በመጽሐፉ ውስጥ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው አላማዎች ውስጥ "የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን ማዳበር" የሚል ይጠቀሳል፡፡

ማንበብና መጻፍ ጥብቅ ትስስር ስላላቸው በውህደት ቢቀርቡ ተማሪዎች የትምህርቱን ይዘት በተገቢው መንገድ እንዲረዱት ሊያግዛቸው ይችላል፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም ክሂሎች የቀደመ እውቀትን የሚጠይቁ በመሆናቸው ሲሉ (Ruddel 1997) አስረድተዋል፡፡

የትምህርት ይዘቶች ለሚፈለገው የትምህርት ደረጃ የታለመውን ግብ እንዲመቱ ለተማሪዎች ግልጽና ተስማሚ ሆነው በበቂ ሁኔታ በመልመጃዎች ተጠናክረው ከቀረቡ የታሰበውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሚናቸው ጉልህ ነው፡፡በመሆኑም በሰባተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ቅንጅታዊ አቀራረብ አንጻር ትኩረት የተሰጠው ለየትኛው ክሂል እንደሆነ ከሚከተለው ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

ሰንጠረዥ ፡-6. በመጽሀፉ ውስጥ የሚገኙ ጠቅላላ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች

| ተ.ቁ | የመልመጃ ጥያቄዎቹ የሚመለሱበት መንገድ | ጠቅላላ ብዛት በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | በቃል እንዲመለሱ የቀረቡ | 9 | 16.7% |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2 | በጽሁፍ እንዲመለሱ የቀረቡ | 36 | 66.6% |
| 3 | በምን ሁኔታ እንደሚመለሱ ያልተገለጹ | 9 | 16.7% |
| 4 | ጠቅላላ ድምር | 54 | 100% |

በሰንጠረዥ 6 ላይ እንደምንረዳው በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ውስጥ 9(16.7%) በቃል እንዲመለሱ፣36(66.6%) በጽሁፍ እንዲመለሱ፣9(16.7%) ደግሞ በቃል ይሁን በጽሁፍ በግልጽ ትዕዛዝ የሌላቸው መልስ እንዲሰጥባቸው ብቻ የቀረቡ ናቸው፡፡በመሆኑም በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ከሌሎች ክሂሎች ይልቅ የንባብ ክሂልን ከጽህፈት ክሂል ጋር በማቀናጀት የሚያዳብሩ ናቸው፡፡

በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በአስሩ ምዕራፎች በሰላሳዎቹ ምንባባት ስር የተካተቱት መልመጃዎች አቀራረብም አብዛኛዎቹ ተማሪዎቹ ካነበቡት ምንባብ በመነሳት በጽሁፍ የሚመልሷቸው ናቸው፡፡ጥያቄዎቹ የተለያዩ ይዘቶች ቢኖራቸውም መሰረታቸው የቀረበው ምንባብ ስለሆነ ምንባቡን አንብበው በተለያየ መልኩ እንዲጽፉ የሚያግዙ ናቸው፡፡ከዚህ በመቀጠል በመጽሀፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብን ለአብነት ያህል ከተወሰኑ ማሳያዎች ጋር ጥቂቶችን እንመለከታለን፡፡

ምዕራፍ አንድ ተግባር ሁለት ገጽ 12 "ጉዞ ወደ ሀዋሳ "የሚለውን ምንባብ በአንድ አንቀጽ አሳጥራችሁ ጻፉ፡፡ምዕራፍ ስድስት ገጽ 115 ተግባር 2"ከሞት ጋር ድርድር" በሚል ርዕስ የቀረበውን የምንባብ ጭብጥ በራሳችሁ አገላለጽ በአንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

ይህ የመልመጃ አቀራረብ የምንባቡን ዋና ሀሳብ ወይም ጭብጥ መሰረት በማድረግ በራስ አገላለጽ አንቀጽ እንዲጽፉ የሚረዳ ነው፡፡ ይህም አንብበው የተረዱትን በጽሁፍ እንዲያጠቃልሉ የሚያግዝ በመሆኑ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማዳበር ያግዛሉ፡፡

ምዕራፍ ሁለት ገጽ18 ፊደል ተራ ሀ.አፈር ህይወትን ለማስቀጠል የሚያስችል የተፈጥሮ ሀብት የተባለው ለምንድነው? አብራርታችሁ ጻፉ፡፡ፊደል ተራ ለ.የአፈር ለምነትን ከምንጠብቅባቸው ዘዴዎች መካከል ሁለቱን መርጣችሁ በራሳችሁ አገላለጽ ማብራሪያ ስጡ፡፡የሚሉና መሰል ጥያቄዎችም ይገኙበታል፡፡

እነዚህ ጥያቄዎች ከምንባቡ የወጡ ሆነው መተርጎምንና ማብራራትን መሰረት በማድረግ የቀረቡ ናቸው፡፡እነዚህ ብልሃቶች ተግባራዊ በሚሆኑመበት ጊዜ ተማሪዎች ላነበቡት ጽሁፍ ዝርዝር ማብራሪያ ትርጉምና ትንተና በጽሁፍ መስጠት የሚችሉበትን እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ይህም አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን ለማቀናጀት እገዛ ያደርጋሉ፡፡

ምዕራፍ ሁለት ገጽ 30 ተግባር 2"የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡ፊደል ተራ ሀ."አንዳንድ ወላጆች ሁለቱንም ጾታ ለማግኘት ሲሉ የቤተሰብ ምጣኔ አይደግፉም" ከሚለው አገላለጽ ምን ተገነዘባችሁ? ፊደል ተራ ለ.ስለቤተሰብ ምጣኔ በአሉታዊነት ከተዘረዘሩት አመለካከቶች መካከል ምናልባት እናንተ በአዎንታ የምትመለከቱት ካለ ግለጹ፡፡"እና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡

እነዚህ ጥያቄዎች ከምንባቡ የወጡ ሆነው የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ምላሻቸው በጽሁፍ እንዲሰጥ የሚያዙ በመሆናቸው ሀሳብን በነጻነት ለመግለጽ አመቺ ናቸው፡፡ በመሆኑም አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት ለማዳበር ይረዳሉ፡፡

ምዕራፍ አራት ገጽ 73 ተግባር 1 በምንባቡ መሰረት የሚከተለውን የትረካ ቅደም ተከተል ቢጋር በማሟላት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡



**የሃሳብ ልዩነቱ የመጨረሻ ውጤት**



ይህ አቀራረብ ቀጥተኛ ማገናዘብንና ማዋቀርን የሚፈልግ በመሆኑ ተማሪዎች ምንባቡን በጥልቀት በማንበብ በጽሁፍ እንዲገልጹ የሚጋብዙ ናቸው፡፡በመሆኑም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ለማዳበር ይረዳሉ፡፡

ምዕራፍ አምስት ተግባር 2 ገጽ 99 ምንባብን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ሀሳቦች በምክንያት አስደግፋችሁ በጽሁፍ ግለጿቸው፡፡



ይህ አቀራረብ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብና የራስ የማብራራት ችሎታቸውን ተጠቅመው ሀሳባቸውን በጽሁፍ እንዲገልጹ የሚያስችል የአቀራረብ ብልሃት ነው፡፡በመሆኑም አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር ያግዛል፡፡

ምዕራፍ ሰባት ገጽ 137 ተግባር 2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች "ጫት መቃምና መዘዙ " በሚለው ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡ፊደል ተራ ሀ."ጫት መቃምና መዘዙ" ከሚለው ምንባብ ከእያንዳንዱ አንቀጽ ውስጥ ዋና ሀሳቡን የያዘ አንድ ዓረፍተነገር ለይታችሁ በማውጣት ጻፉ፡፡ለ."ጫት መቃምና መዘዙ"ከሚለው ምንባብ ካወጣችኋቸው ዋና ዋና ሀሳቦች ውስጥ አንዱን ወስዳችሁ በምክንያትና ውጤት ስልት በራሳችሁ አገላለጽ አንቀጽ ጻፉ:: የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡(አባሪ 3ን ይመልከቱ)፡፡

እነዚህ አቀራረቦችም ከምንባቡ ውስጥ ከሚገኙ አንቀጾች ውስጥ ዋና ሀሳቡን የያዙ ዐ/ነገሮችን በመለየት እንዲጽፉ የሚያደርጉና ከለዩዋቸው ዋና ሀሳቦች ውስጥ አንዱን በመምረጥ በምክንያትና ውጤት ስልት በራሳቸው አገላለጽ አንቀጽ እንዲጽፉ በሚረዳ መልኩ ቀርበዋል፡፡ይህም አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማዳበር ያግዛሉ፡፡

ይህ አቀራረብም Block (1997) እና Beerdgew (2003) እንደገለጹት ተማሪዎች እያነበቡ በመገመት ሲጽፉና ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ እየሰጡ እንዲማሩ ሲደረግ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር እገዛ እንደሚያደርግ ይገልጻሉ፡፡

በመሆኑም በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሃምሳ አራት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የተካተቱ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ሰላሳ ስድስቱ ተግባራት የንባብ ክሂልን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ለማስተማር የሚያግዙ ናቸው፡፡እነዚህ ጥያቄዎችም ከምንባቡ የወጡ ሆነው ምላሻቸው በጽሁፍ የሚገለጽ በመሆናቸው ይህም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ለማዳበር ያግዛሉ፡፡

ከመምህራን በተገኘ የመጠይቅ ምላሽ መሰረት ደግሞ አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር መቀናጀት አለመቀናጀቱን በተመለከተ መረጃ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ፡-7. መልመጃዎቹ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ያላቸው እገዛ

| ተ.ቁ | ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎች | ድግግሞሽ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 1 | በተማሪው መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያላቸው እገዛ | 3(50%) | 1(16.7%) | 1(16.7%) | 1(16.7%) | - |
| 2 | ይዘቶቹ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ያላቸው አመችነት | 3(50%) | 1(16.7%) | - | 2(33.3% | - |
| 11 | ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች አኳያ ሲታይ መጽሀፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳትና ለመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ የተሰጠው ቦታ | 1(16.7%) | 3(50%) | 1(16.7%) | 1(16.7%) | - |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በተራ ቁጥር 1 ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ 3 (50%) በጣም ከፍተኛ፣ 1(16.7%) ከፍተኛ 1(16.7%) መካከለኛ እና 1(16.7%) ዝቅተኛ የሚል ነው፡፡በመሆኑም ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለው 4 መምህራን (66.7%) በተማሪው መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያላቸው እገዛ በአመዛኙ ከፍተኛ የሚል ነው፡፡በተራ ቁጥር 2 ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ 3 (50%) በጣም ከፍተኛ፣ 1(16.7%) ከፍተኛ እና 2 መምህራን (33.3%) በጣም ዝቅተኛ የሚል ነው፡፡ ስለሆነም ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለው 4 መምህራን

(66.7%) ይዘቶቹ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ያላቸው አመችነት በአመዛኙ ከፍተኛ የሚል ነው፡፡

በተራ ቁጥር 11 ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ 1(16.7%) በጣም ከፍተኛ፣3 (50%) ከፍተኛ ፣1(33.3%) መካከለኛ እና 1(33.3%) ዝቅተኛ የሚል ነው፡፡ስለሆነም ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለው 4 መምህራን (66.7%) ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች አኳያ ሲታይ መጽሀፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳትና ለመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራብ የተሰጠው ትኩረት በአመዛኙ ከፍተኛ የሚል ነው፡፡ ይህ የመረጃ ትንተና እንደሚያመለክተው አንብቦ የመረዳት መልመጃዎቹ አቀራረብ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂላቸውን በቅንጅት ለማዳበር በሚያስችል መልኩ መቅረባቸውን ነው፡፡

ይህን ጉዳይ በተመለከተ "ከሌሎች ክሂሎች አንጻር ሲታይ በመጽሀፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳትና ለመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ የተሰጠው ቦታ ምን ይመስላል? ቢገልጹልኝ" በማለት ለመማሪያ መጽሀፉ አዘጋጆች ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ በ"EGRA" ጥናት ውጤት መሰረት ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂላቸው ዝቅተኛ በመሆኑ በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ወቅት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷል በማለት ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም "አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን አቀናጅቶ ማቅረብ ምን ዓይነት ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለው ያስባሉ?" ተብለው ለቀረቡላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ  ማንበብና መጻፍ ጥብቅ የሆነ ትስስር አላቸው ፣አንብበው ከተረዱት ነገር ተነስተው እንዲጽፉ ይደረጋል፡፡ ይህም አቀራረብ ተማሪዎች ተነሳሽነት እንዲኖራቸው፣አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውንና የመጻፍ ክሂላቸውን ለማሳደግ ይረዳል እንዲሁም ሌሎች የትምህርት አይነቶችን በጥልቀት እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል መጽሀፉም የተዘጋጀው ይህን መሰረት አድርጎ ነው በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ "የአንብቦ መረዳት ተግባራት ከመጻፍ ክሂል ጋር የይዘት ቅንጅት አላቸው ብለው ያምናሉ? ከሆነስ በምን መልኩ?" ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁለቱም አዘጋጆች "አዎ፣ ምክንያቱም በመጀመሪያ ምንባቡን እንዲያነቡ ይደረጋል፡፡ ከዚያም አንብበው የተረዱትን እንዲጽፉ ይደረጋል"ሲሉ ገልጸዋል::ይህም በመዛግብት ፍተሻ የተገኘውን 66.6% ያህሉ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከመጻፍ ክሂል ጋር የተቀናጁ ናቸው የሚለውን ሀሳብ የሚያጠናክር ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ ከመማሪያ መጽሀፉ ሰነድ ፍተሻ፣ከመምህራንና ከአዘጋጆች መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በተማሪው መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱት አንብቦ የመረዳት

ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ አብዛኞዎቹ ከመጻፍ ክሂል ጋር ተቀናጅተው መቅረባቸውን ነው፡፡

## 4.1.7. አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት ለማስተማሪያ የተዘጋጁት መልመጃዎች ግምገማ

አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በውህደት ለማስተማርና ለማለማመድ የሚዘጋጁ ተግባራት የማስተማሪያ ብልሃቶችን መሰረት ያደረጉ መሆን እንዳለባቸው በርካታ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ይህም በምዕራፍ ሁለት ላይ  በዝርዝር የተገለጸ ሲሆን ጥያቄ መጠየቅ፣መተንበይና መገመት፣ማብራራትና መተርጎም፣ማጠቃለልና ምሰላ የሚሉት ይገኙበታል፡፡በመጽሀፉ ውስጥ የንባብ ክሂልንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ታስበው የቀረቡት መልመጃዎች የቀረቡበትን ስልት ለማሳየት የተወሰኑትን ምሳሌዎች መጥቀስ ተገቢ ነው፡፡

የንባብን ክሂል ማስተማሪያ ከሆኑ ብልሃቶች መካከል አንዱ"ጥያቄ መጠየቅ" ሲሆን ይህ ብልሃት በመጽሀፉ ውስጥ በብዛት መካተቱን ማስተዋል ተችሏል፡፡ እነዚህን አቀራረቦች ለምሳሌ ያህል ጥቂቶቹን እንመለከታለን፡፡ገጽ 2 ቅድመ ንባብ ጥያቄ ፊደል ተራ ሀ "ጉዞ ወደ ሀዋሳ" የሚለውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት ስዕሉን አስተውሉና ከስዕሉ የተረዳችሁትን በቃላችሁ ግለጹ፡፡ገጽ 15 ፊደል ተራ ሀ."የአፈር እንክብካቤ" ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል? ፊደል ተራ ለ.ከስዕሉ የተገነዘባችሁት ሀሳብ ምንድነው?የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡

ሁለተኛው የንባብ ማስተማሪያ ብልሃት መተንበይና መገመት ሲሆኑ እነዚህን የማስተማሪያ ስልቶች በሚመለከት በመጽሐፉ ውስጥ በተካተቱ አብዛኞዎቹ ምንባቦች በማንበብ ሂደት መመሪያዎች ላይ ተማሪዎቹ በሚያነቡት ጽሁፍ ውስጥ ቀጥሎ ሊከሰት ስለሚችለው ጉዳይ ቀድመው በመተንበይ እንዲያነቡ መመሪያዎች ተሰጥተዋል፡፡ ይህ አቀራረብ በከፍተኛ ሁኔታ ተስተውሏል፡፡ለምሳሌ ያህል ጥቂቶቹን እንመለከታለን፡፡

ገጽ 9 "ጉዞ ወደ ሐዋሳ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በእያንዳንዱ የጉዞ መዳረሻ ሊታዩ የሚችሉ ነገሮችን ቀድማችሁ በመተንበይ ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡ምዕራፍ አምስት ገጽ 88  "ተዋበችና የውኃ አጠቃቀሟ" የሚለውን ምንባብ ስታነቡ ባለታሪኳ ለሚያጋጥሟት ችግሮች

ቀድማችሁ መፍትሄውን በመገመት ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡ገጽ 96 ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ፣ምክንያቶቹ ሊያስከትሏቸው የሚችሉ ውጤቶችን በመገመት ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡ምዕራፍ ስድስት ገጽ 110 "ከሞት ጋር ድርድር" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የአንዱን ገጸባህርይ ንግግር ካነበባችሁ በኋላ የሌላው ምላሽ ምን ሊሆን እንደሚችል በመገመት ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡ የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡(አባሪ 1እና 2ን ይመልከቱ፡፡)

ሶስተኛው የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ብልሃት "ማጠቃለል" የሚለው ሲሆን ይህም የምንባብን ዋና ሀሳብ ጨምቆ የማውጣት ሂደት ነው፡፡ይህ ማስተማሪያ ብልሃት በመጽሀፉ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ተግባራዊ መሆኑን መመልከት ተችሏል፡፡ ይኸውም ምዕራፍ አንድ ገጽ 12 ተግባር 2 "ጉዞ ወደ ሀዋሳ" የሚለውን ምንባብ በአንድ አንቀጽ አሳጥራችሁ ጻፉ፡፡ ምዕራፍ ሁለት ገጽ 24 የምንባቡን ዋና ሀሳብ በሶስት አረፍተነገሮች ግለጹ፡፡ ምዕራፍ ስድስት ገጽ 115 አንብቦ መረዳት ተግባር 2 "ከሞት ጋር ድርድር" በሚል ርዕስ የቀረበውን የምንባብ ጭብጥ በራሳችሁ አገላለጽ በአንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡የሚሉና ሌሎችም ይገኛሉ፡፡(አባሪ 3ን ይመልከቱ፡፡)

አራተኛው አንብቦ መረዳትንና ጽሁፍ ማቀናበርን በውህደት ለማስተማር ከሚያገለግሉት ብልሃቶች መካከል ማብራራትና መተርጎም ተጠቃሾች እንደሆኑ Block (1997) ያስረዳሉ፡፡ በእነዚህ ብልሃቶች ተማሪዎች ያነበቡትን ነገር በመጻፍ እንዲያብራሩና ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድረግ የመረዳት ችሎታቸውን ለመገንዘብ የሚሞከርባቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡ተማሪዎች እነዚህን ብልሃቶች ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ስለአነበቡት ጽሁፍ ዝርዝር ማብራሪያ፣ትርጉምና ትንተና በጽሁፍ መስጠት የሚችሉበት እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ይህ የማስተማሪያ ብልሃት በመጽሀፉ ውስጥ በብዙ ምዕራፎች ተግባራዊ መሆኑን የሰነድ ፍተሻው ያመለክታል፡፡ለምሳሌ ያህል ጥቂቶቹን እንመልከታለን፡፡

*ምዕራፍ አንድ ገጽ 18 ፊደል ተራ ሊ.የአፈር ለምነትን ከምንጠብቅባቸው ዘዴዎች መካከል ሁለቱን መርጣችሁ በራሳችሁ አገላለጽ ማብራሪያ ስጡ፡፡ ምዕራፍ ስምንት ገጽ 168 ፊደል ተራ ሀ.የሀገር ፍቅር ስሜትን ለመግለጽ ከአርበኝነት ተግባርና ከበጎ አድራጎት ተግባር የትኛው የተሻለ ይመስላችኋል? ለምን? ለ.በዓለም የውድድር አደባባዮች ተሰልፈው ድል ማድረግ የተሳናቸውን አትሌቶች የሀገር ፍቅር ስሜት የላቸውም ማለት ይቻላል? ለምን?የሚሉና ሌሎችም ተካትተው ይገኛሉ፡፡(አባሪ 3ን ይመልከቱ፡፡)*

ሌላው የማስተማሪያ ብልሃት ምሰላ ሲሆን ይህ ብልሃት በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ተስተውሏል፡፡ይኸውም ምዕራፍ ስድስት ገጽ 110 ላይ "በላ ልበልሃ"በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በከሳሽና በተከሳሽ መካከል የሚፈጠረውን ስሜትና የአካል እንቅስቃሴ በአዕምሯችሁ ምስል እየፈጠራችሁ ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ በማለት ቀርቧል፡፡(አባሪ 2ን ይመልከቱ፡፡)

በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ብልሃቶች በጥሩ ሁኔታ ተካተው ቀርበዋል፡፡እነዚህ አቀራረቦችም ተማሪዎች የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት ሲለማመዱ ስለጽሁፉ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲተነብዩ፣ትርጉም እንዲሰጡ፣ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችን እንዲመረምሩም ያግዛቸዋል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ያነበቡትን ወይም የጻፉትን ነገር ማጠቃለያ መስጠት እንዲችሉ በሚረዳ መልኩ ከተዘጋጁ እውቀትን ይዞ የመቆየት ችሎታቸውን ያዳብርላቸዋል፡፡ ይህም በቋንቋ ትምህርት ውስጥ እንደ መሰረታዊ አንብቦ የመረዳትና የጽሁፍ ማቀነባበር ችሎታ ማዳበሪያ ብልሃት ተደርጎ እንደሚወሰድ ጽንሰ ሀሳባቸውን ካራመዱት Block(1997) እና Beerdgew(2003) ሀሳብ ጋር የጥናቱ ውጤት የሚደጋገፍ እንደሆነ የሰነድ ፍተሻው ያመለክታል፡፡

ይህንን አቀራረብ አስመልክቶ በተራ ቁጥር 7 የንባብ ክሂል መልመጃዎች ለክሂሉ ማስተማሪያ የሚሆኑ ብልሃቶችን መሰረት ያደረጉ ናቸው? (ለምሳሌ፡-ጥያቄ መጠየቅ፣ማብራራትና መተርጎም፣አንድምታና ትንበያ) ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ በጣም ከፍተኛ 2(33.3%) ከፍተኛ 2(33.3%) መካከለኛ 2(33.3%) የሚል ነው፡፡በመሆኑም ከዚህ መረዳት የሚቻለው 4 መምህራን (66.7%) በአመዛኙ ከፍተኛ የሚል ነው፡፡

ይህ የመረጃ ትንተና የሚያመለክተው የንባብ ክሂል ማስተማርያ ብልሃቶች በጥሩ ሁኔታ መካተታቸውን ነው፡፡ ይህንን ይበልጥ ለማረጋገጥ "በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚረዱ ብልሃቶች ምን ያህል ተካተዋል ብለው ያምናሉ?"ተብለው ለቀረቡላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ከንባብ በፊት እንዲገምቱ፣በንባብ ጊዜ ግምታቸውን እንዲያረጋግጡና ከንባብ በኋላ የተረዱትን በጽሁፍ እንዲያብራሩ በሚያስችል መልኩ ቀርቧል በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡እንዲሁም

"ስለአንብቦ መረዳትና ስለመጻፍ ክሂል ተግባራት የይዘት ቅንጅት የሚሉት ነገር ካለ? ቢገልጹልኝ፡፡"ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሻቸውን ሲሰጡ መጽሐፉ የተዘጀው አንብቦ

መረዳትንና የመጻፍ ክሂላቸውን ለማዳበር ሁለቱን ክሂሎች ባቀናጀ መልኩ አንብበው የተረዱትን እንዲጽፉ በሚረዳ ሁኔታ እንደተዘጋጀ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይህም ከሰነድ ፍተሻ ከተገኘውን መረጃ የሚያጠናክር ነው፡፡

በአጠቃላይ በመጽሐፉ ላይ በተደረገው ሰነድ ፍተሻ፣ ከመምህራንና ከመማሪያ መጻህፉ አዘጋጆች ከተገኙት መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ የማስተማሪያ ብልሃቶች በአብዛኛው ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ እነሱም ጥያቄ መጠየቅ፣ መገመት፣ ትንበያ፣ ማጠቃለል፣ ማብራራትና መተርጎም የሚባሉት የማስተማሪያ ብልሃቶች መሆናቸውን የመረጃው ትንተና ያብራራል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ "ምሰላ" የተባለው የማስተማሪያ ብልሃት በመጽሀፉ ውስጥ አንድ ቦታ ላይ ብቻ መካተቱን የመረጃ ትንተናው ያሳያል፡፡

## 4.1.8. የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ለአንብቦ መረዳትና ለመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው እገዛ

የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ተቀናጅተው ቢቀርቡ የሚያስገኙትን ጠቀሜታ በምዕራፍ ሁለት ቅኝት ላይ ተገልጿል፡፡ የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ሲዘጋጁ ተማሪዎች የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት እንዲለማመዱ የሚያስችሉ መሆን እንዳለባቸው ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ይኸውም ስለጽሁፉ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲተነብዩ፣ ትርጉም እንዲሰጡ፣ ላነበቡት ወይም ለጻፉት ነገር ማጠቃለያ መስጠት የሚያስችሉ ሆነው መዘጋጀት እንዳለባቸው Block(1997) እና Beerdgew(2003) ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በመቀጠል በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱትን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች አቀራረባቸውን አስመልክቶ የተገኙ መረጃዎች ከመተንተናቸው በፊት ስለ መርሃ ትምህርቱ ጥቂት መረጃዎችን እንመለከታለን፡፡

### 4.1.8.1.የመርሀ ትምህርቱ አጭር መግለጫ

የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት የተዘጋጀው በ2007 ዓ.ም ሲሆን በክፍል ደረጃው በተዘጋጀው የመምህሩ መምሪያ የመጨረሻዎቹ ገጾች ላይ ይገኛል፡፡ በውስጡም አስር ምዕራፎች አሉት፡፡ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ስር ርዕስ፣ዝርዝር ዓላማዎች የማስተማር ክንውኖች፣ የምዘና ስልቶችና ይዘቶች በተከታታይ ቀርበዋል፡፡በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት የቋንቋ ክሂሎች ያላቸው ዝርዝር አላማዎችም ተገልጸዋል፡፡

ዓለም (1995) እንደገለጹት መርሀ ትምህርት በሚቀረጽበት ጊዜ ትኩረት ከሚገባቸው ነገሮች መካከል አንዱ ክሂሎቹ ተቀናጅተው መቅረባቸውን ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ ምሁራኑ ይገልጻሉ፡፡በመሆኑም የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ስለሆነ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች አቀራረብ ምን እንደሚመስል ለአብነት ያህል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| አንብቦ መረዳት | ማንበብ | መጻፍ | ናሙና የመማር ማስተማር ስልቶች | ናሙና የምዘና ስልቶች | ይዘቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| አንብቦ የመረዳት ብልሃት ማጎልበት | ተማሪዎች | ተማሪዎች | | | |
| | -2.5ገጽ ያለውን ጽሁፍ አንብበው ያሳጥራሉ፡፡<br>-2.5ገጽ ያለውን ጽሁፍ አንብበው ይገመግማሉ፡፡ | -ስዕላዊ የሀሳብ አደረጃጀትን ስልት በመጠቀም በጽሁፍ የቀረበን ሀሳብ ያደራጃሉ፡፡<br>-በጽሁፍ የቀረቡትን ሀሳቦች | ለማንበብ የዘወትር አጋጣሚዎችን መጠቀም፤ለተለያዩ ዘውጎችዳራዊ እውቀት በመገንባት በተዘዋዋሪ መጻፍን ያሻሽላሉ::<br>-ምናባዊ ምሰላ፤ተማሪዎች በአእምሯቸው ስዕል እንዲስሉና | -መመሪያ መር ክለሳ፤ተማሪዎች ለጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ያለፈውን ትምህርት ጥያቄዎችን የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ወረቀቶች /ካርዶች በማሳየት ይመልሳሉ(ለምሳሌ፣እስማማለሁ/አልስማማም፣እውነት/ሀሰት)<br>-ኢ-መደበኛ ክትትል፤የትኞቹ ህጻናት እንደገባቸውና የትኞቹ የበለጠ እርዳታ እንደሚፈልጉ ለማወቅ መምህራን በክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩ ይከታተላሉ፡፡ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | -ከክፍሉ ደረጃ ለቀረበው ጽሁፍ ከቀደመ እውቀትና ልምድ እንዲሁም ከሌላ ጽሁፍ ጋር ያዛምዳሉ፡ ፡-ለጽሁፉ የሚስማማ የመረዳት ስልትና የንባብ ዘዴ መርጠው በስራ ላይ ማዋል ይችላሉ፡፡<br><br>-ለክፍሉ ደረጃ የተመደበውን ጽሁፍ መረዳታቸውን ለመመዘን ራስን የመገምገም ስልት ያበለጽጋሉ፡፡ | ማስተካከል፣መቀየርና መግለጽ ይችላሉ፡፡<br><br>-ድምጽ በማሰማት የተነበበውን ወይም የተደመጠን ጽሁፍ ሀሳቦች አሳጥረው ይጽፋሉ፡፡ | የተማሩትንና ያነበቡትን እንዲያስታውሱና እንዲረዱ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ ማብራራት፤ተማሪዎች ከተማሩት ውስጥ ግራ ያጋባቸው ላይ ማብራሪያ እንዲፈልጉ ያበረታታቸዋል፡፡<br><br>-የመጠይቅና ምላሽ ግንኙነት፤ድህረ ንባብ ጥያቄዎች የሚከተሉትን ይይዛሉ፤<br><br>-መልሱ እዚያው (መልሱ በአንድ አረፍተነገር ውስጥ ይገኛል)<br><br>-ማንበብና መመርመር (መልሱ ምንባቡ ውስጥ አለ፤ግን መረጃው ከአንድ ዓረፍተ ነገር በላይ ማየትን ይጠይቃል)<br><br>-ጽሁፍና እኔ(ጥያቄውን ለመመለስ የጽሁፉን መረጃ ከአካባቢው ዳራ ማዛመድን ይጠይቃል)<br><br>-መጠየቅ፤ስለነበቡት ነገር ጥያቄ እንዲያዘጋጁና የክፍል | -ማቅረብ/አቅርቦት፤ተማሪዎች የተረዱትን ለመምህር ወይም ለክፍሉ ለማሳየት አጋጣሚ ያገኛሉ፡፡ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጓደኞቻቸውን እንዲጠይቁ ጊዜ ይሰጣል፡፡<br><br>-ማጠቃለል፤የጽሁፍ መረጃን እንዲ ያጠቃልሉና እንዲያዋህዱ ያለማምዳል፡፡ | | |

ከዚህ በላይ ከቀረበው መርሃ ትምህርት እንደምንረዳው አንብበው የተረዱትን አሳጥረው እንዲጽፉ ፣አንብበው የተረዱትን በጽሁፍ ማጠቃለያ እንዲሰጡ በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህ አቀራረብም አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ ያለው እገዛ ጉልህ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ሌላው የማስተማርያ መሳሪያ የመምህሩ መምሪያ ሲሆን መምህሩ የተማሪውን የመማሪያ መጽሀፍ እንዴት ማስተማር እንዳለበት አቅጣጫ የሚያመለክት ነው፡፡በመሆኑም የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመምህር መምሪያውም የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አቀራረብ ምን እንደሚመስል ጥቂቶችን ለአብነት ያህል እንመለከታለን፡፡

ምዕራፍ አንድ ገጽ 11 የማንበብ ሂደት አቀራረብን ስንመለከት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ *"ለቅድመ ንባብ ጥያቄዎች የሰጣችኋቸውን መልሶች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ "የአፈር እንክብካቤ" የሚለውን ምንባብ ድምጽ ሳታሰሙ በማንበብ ዋና ሃሳቦችን ቆም እያላችሁ በመለየት በደብተራችሁ ጻፉ፡፡ዋና ሃሳቦችን ለመለየት እያንዳንዱን አንቀጽ በማጠቃለል ወደ ቀጣዩ አንቀጽ መተላለፍ አለባችሁ፡፡(ዋና ሃሳቦችን እያወጡ መሆናቸውን እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፡፡)"*

"በ2ኛው ሳምንት ፣4ኛ ቀን የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞች ለራሳችሁ በሚሰማ ድምጽ በማንበብ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ተረዱ፡፡መልዕክቱን ለመረዳት በየሀረጋቱና በስንኞቹ ያሉትን ለየት ያሉ አገላለጾች በሚገባ በመመርመር፤አዲስና የተለያየ ፍቺ ያላቸውን ቃላት ስታገኙ ከዓውዳቸው አንጻር ፍቻቸውን በመረዳት አንብቡ፡፡ከአራት እስከ ስድስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት ካነበባችኋቸው ቃላዊ ግጥሞች የምታስታውሷቸውን ሀረጋት ወይም ስንኞች ጻፉ፡፡(አንዱን ወረቀት ተራ በተራ እያዟዟሩ የሚያስታውሱትን እንዲጽፉ

ይንገሯቸው) ከጻፏቸው ሀረጋትና ስንኞች የተረዳችሁትን መልዕክት ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡እነዚህንና ሌሎች መሰል አተገባበሮች ተካተዋል፡፡

እነዚህ አቀራረቦች ተማሪዎቹ እያነበቡ እያሉ የተረዱትን ማስታወሻ እንዲይዙ፣ሁለቱንም ክሂሎች በተቀናጀ ሁኔታ እንዲተገብሩት በሚረዳ መልኩ የቀረቡ ሲሆን ይህም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከጽሁፍ ጋር አቀናጅቶ ለማዳበር ያግዛሉ፡፡ከዚህ በመቀጠል ከምንባብ በኋላ የቀረቡት መልመጃዎች አቀራረብ ጥቂቶችን ለምሳሌ ያህል እንመለከታለን፡፡

*መምህር "የመጀመሪያዋ ጋዜጠኛና ደራሲ ወይዘሮ ሮማነወርቅ ካሳሁን" የሚለውን ምንባብ አንብባችኋል፡፡ ቀጥሎ በመማሪያ መጽሐፋችሁ በቀረበው የቢጋር ሰንጠረዥ መሰረት በደብተራችሁ ላይ ዋናዋና ሀሳቦቹን ጻፉ፡፡(10 ደቂቃ ይስጧቸው ገጽ 42) በተግባር 2 ስር የ"ለ"ን ከክፍል ውጪ በሰራችሁት መሰረት አቅርቡ፡፡ በመጀመሪያ የአንቀጽ አንድ ዋና ሀሳብ መነሻ አድርጋችሁ በራሳችሁ አገላለጽ በምክንያትና ውጤት ስልት የጻፉችሁትን አንብቡ፡፡(5ደቂቃ ይስጧቸው ገጽ 86 )"* እነዚህና ሌሎችም አቀራረቦች ይገኛሉ፡፡

እነዚህ አቀራረቦች ደግሞ ምንባቡን ካነበቡ በኋላ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ እንዲገልጹ የሚያደርጉና የጻፉትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው የሚጋብዙ ናቸው፡፡በመሆኑም እነዚህ አቀራረቦች የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች በተቀናጀ ሁኔታ የቀረቡ ሲሆኑ ይህም የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች እርስበርስ አቀናጅቶ ለማስተማር እገዛ ያደርጋል፡፡ ከመምህራን በተገኘ የመጠይቅ ምላሽ መሰረት ደግሞ የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ለአንብቦ መረዳትና ለመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸውን እገዛ በተመለከተ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ይህንንም በተመከለተ በተራ ቁጥር 13 ላይ ለመምህራን የመማሪያ መጽሐፉ፣የመምህሩ መመሪያና መርሃ ትምህርቱ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎቹ እርስ በርስ ተያይዘው እንዲቀርቡ እገዛ በማድረግ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለመምራት ምን ያህል አጋዥ ናቸው?ተብለው ለቀረቡላቸው ጥያቄ (መ/ርት 3፣መ/ርት 4፣መ/ርት 5 እና መ/ርት 6) የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ

በጥሩ ሁኔታ አጋዥ እንደሆኑ ምላሻቸውን የገለጹ ሲሆን (መ/ርት 1 እና መ/ርት ግን በመጠኑ አጋዥ መሆናቸውን ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ መረጃ ትንተና መረዳት የሚቻለው የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ መማር ማስተማር ሂደቱን ለመምራት ከፍተኛ የሆነ እገዛ እንዳደረጉላቸው የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ይህን ጉዳይ በተመለከተ "የንባብ ክሂልን ለማስተማር ሲታሰብ ሌሎች ክሂሎች ይከተላሉ?ይህ የቋንቋ ክሂሎችን ለማቀናጀት በቂ ነው ይላሉ?ለምን?" በማለት ለመማሪያ መጽሐፉ አዘጋጆች ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሻቸውን ሲሰጡ አራቱም የቋንቋ ክሂሎች የሚነጣጠሉ አይደሉም፡፡ ተግባራቱን በሚያከናውኑበት ጊዜ አንብበው የተረዱትን ይጽፋሉ፣ይናገራሉ፡፡

በመሆኑም የማይነጣጡሉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ክሂሎችን ለማሳደግ ታስቦበት መተግበር ያስፈልጋል፡፡በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ይህም በምዕራፍ ሁለት ላይ ከተገለጸው የምሁራን ሀሳብ ጋር የሚስማማ ነው፡፡ ከመጠይቁ የተገኘው ምላሽም ከሰነድ ፍተሻ ከተገኘውን መረጃ የሚያጠናክር ነው፡፡

በአጠቃላይ ከሰነድ ፍተሻው፣ ከጽሁፍ መጠይቁና ከቃለ መጠይቁ መረዳት እንደሚቻለው መማሪያ መጽሀፉ፣የመምህሩ መምሪያና መርሃ ትምህርቱ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን እርስ በርሳቸው ተቀናጅተው እንዲቀርቡ እገዛ በማድረግ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለመምራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ የተገኘው መረጃ ያብራራል፡፡ይሁን እንጅ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን አቀናጅቶ ለመተግበር የሚያስችሉ ቢሆኑም በንባብ ክሂል ክፍለ ጊዜ የቀረቡት ተግባራትና የተሰጠው ጊዜ ግን ተግባራቱን ለመተግበርና ክሂሎቹን ለማዳበር የሚያስችል አይደለም፡፡ Lindsay and Knight (2006) ሲያስረዱ የንባብን ክሂል ለማዳበር የምንመርጠው የጽሁፍ መጠን ክፍል ውስጥ ካለን ጊዜ አንፃር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ጽሁፍን ለማንበብ የሚወስድብን ጊዜ እና ከንባብን በኋላ ለሚሰሩ ተግባራት የምንሰጠው ጊዜ ከአለን አጠቃላይ ጊዜ ጋር ካልተጣጣመ ልናዳብረው የፈለግነውን የንባብ ክሂል ውጤታማ ልናደርገው አንችልም በማለት ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ የመጽሀፉ አዘገጃጀት ከምሁራኑ ሀሳብ ጋር እንደሚቃረን

የሰነድ ፍተሻው ያመለክታል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የመምህራን የቋንቋ ክሂሎች አቀራረብን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 4.1.9. መምህራን ስለማንበብና መጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤ

የተተኳሪ መምህራንን የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ከማየታችን በፊት የክፍለ ጊዜያቱ ይዘቶች አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀት ያላቸውን እገዛ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት በስድስቱም መምህራን በተደረገው የሶስት ሶስት ተከታታይ የክፍል ምልከታዎች የክፍለ ጊዜው ይዘት አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀት ያለውን እገዛ ለማወቅ የምልከታ ነጥቡና የተገኘው መረጃ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ ፡-8 የክፍለ ጊዜያቱ ይዘቶች አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀት ያላቸውን እገዛ ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ዝርዝር የመከታተያ ነጥብ | ድግግሞሽ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 1 | የክፍለ ጊዜው ይዘት አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ያለው እገዛ | - | 18(100%) | - | - | - |
| 2 | የክፍለ ጊዜው ይዘት አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ | | 18(100%) | - | - | - |
| 3 | አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የቀረበው ይዘት ከተማሪዎች | - | 18(100%) | - | - | - |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ህይወት ጋር ያለው ግንኙነት | | | | | |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በስድስቱም የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን በተከታታይ በሶስቱ ክፍለ ጊዜያት የነበረው ይዘት አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ለማቅረብ ያለው እገዛ ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡ከዚህም በተጨማሪ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች ከተማሪዎች ህይወት ጋር ግንኙነት ያላቸው መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ መምህራን የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ ግንዛቤው ከሌላቸው ይዘቶቹ አመቺ ስለሆኑ ብቻ የቋንቋ ክሂሎች ተቀናጅተው ይቀርባሉ ማለት አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

## 4.1.9.1.የመምህራኑ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች አቀራረብ

መምህራኑ ስለቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ እውቀት እንዳላቸው ለማወቅ መጀመሪያ ክሂሎችን እንዴት እንዳቀረቧቸው መፈተሽ አስፈላጊ ነው፡፡በመሆኑም ከምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

ሰንጠረዥ፡-9. የመምህራንን የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | መከታተያ ነጥብ | ድግግሞሽ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 4 | መ/ሩ(ሯ) ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ የማድረግ ሁኔታቸው | 5(27.8%) | 7(38.9%) | 4(22.2%) | 2(11.1%) | - |
| 6 | መ/ሩ (ሯ) አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር ትኩረት ሰጥተው የማቀናጀት | - | 3(16.7%) | 5(27.8%) | 4(22.2%) | 6(33.3%) |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሁኔታ | | | | | |
| 11 | መ/ሩ (ሯ) በክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ የማድረግ ሁኔታቸው | - | 4(22.2%) | 6(33.3%) | 4(22.2%) | 4(22.2%) |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በተራ ቁጥር 4 መከታተያ ቅጽ መሰረት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው 5(27.8%) በጣም ከፍተኛ 7(38.9%) ከፍተኛ 4(22.2%) መካከለኛ 2(11.1%) ዝቅተኛ የሆነ አተገባበር እንዳለ መመልከት ተችሏል፡፡

ይህም የሚያሳየው አብዛኞዎቹ መምህራን ተማሪዎቹ ምንባቡን እንዲያነቡ የሚያደርጉት ክትትልና ድጋፍ በጣም ጥሩ የሚባል ሲሆን ጥቂቶቹ ደግሞ ምንባቡ ተነቧል እንዲባል ያህል አንብቡ በማለት እንዴት ማንበብ ወይም ተግባራትን እንዴት ማከናወን እንዳለባቸው ሚናቸውን የመወጣት ሁኔታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡

ሰንጠረዥ 8 ላይ እንደምንረዳው በአስራ ስምንት ተከታታይ ምልከታዎች የነበረው ይዘት አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ለማቅረብ ከፍተኛ ቢሆኑም ከአስራ ስምንት ተከታታይ ምልከታዎች የነበረው አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ የማቀናጀት ሁኔታ 3(16.7%) ክፍለ ጊዜያት ከፍተኛ 5(27.8%) ክፍለ ጊዜያት በመካከለኛ የሆነ የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ መኖሩን ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ 4(22.2%) ክፍለ ጊዜያት ዝቅተኛ እና 6(33.3%) ክፍለ ጊዜያት ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ቅንጅታዊ አቀራረብ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ይህም የንባብ ክሂልን ከመጻፍ ክሂል ጋር ትኩረት ሰጥተው የሚያቀርቡ መምህራን በቁጥር ዝቅተኛ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከሰንጠረዡ በተራ ቁጥር 11 ላይ እንደምንረዳው አንብቦ መረዳት ተግባራትን መምህራን በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ የማድረጋቸውን ሁኔታ ስንመለከት 4(22.2%)ከፍተኛ 6(33.3%) መካከለኛ የሆነ አተገባበር ያላቸው መምህራን እንዳሉ ሁሉ 4(22.2%) ዝቅተኛ እና 4(22.2%) በጣም ዝቅተኛ የሆነ አተገባበር ያላቸው መምህራን እንዳሉም መረዳት ተችሏል፡፡

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ "አንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ተቀናጅተው ቢቀርቡ በተማሪዎች ችሎታ ላይ ለውጥ ያመጣል ብለው ያስባሉ? ከሆነ እንዴት?" ተብለው ለመምህራን ለቀረበላቸው ጥያቄ (መ/ርት 1 ፣ መ/ርት 2፣መ/ርት 3፣መ/ርት 5 እና መ/ርት 6 ) የሰጡት ምላሽ አዎ ምክንያቱ ሁለቱ ክሂሎች ትስስር ስላላቸው ሁለቱንም አዋህዶ ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታ ውጤታማ ማድረግ ይቻላል፡፡ይኸውም አንብበው የተረዱትን በጽሁፍ እንዲገልጹ በማድረግ ሁለቱም ክሂሎች እንዲዳብሩ ማድረግ ይቻላል ሲሉ መ/ርት 4 ግን የተማሪዎች ቁጥር ከፍተኛ በሆነበት ክፍል አንብበው የተረዱትን እንዲናገሩ ማድረግ ስለማይቻል አንብበው የተረዱትን በጽሁፍ እንዲገልጹ በማድረግ በተሻለ ሁኔታ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታቸውን ማሳደግ ይቻላል በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል::

ከመጠይቁ ከተገኘው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራን ማንበብና መጻፍ ጥብቅ የሆነ ትስስር ስላላቸው አንብበው ከተረዱት ነገር ተነስተው እንዲጽፉ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ጠቀሜታውም አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውንና የመጻፍ ክሂላቸውን ለማሳደግ እንደሚረዳቸው ነው፡፡ይህም የሚያሳየን አብዛኛዎቹ መምህራን ስለቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ግንዛቤው ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ መምህራን ስለቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ግንዛቤው ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ይሁን እንጂ ከምልከታ የተገኘው መረጃ የሚያሳየው ትኩረት ሰጥተው አቀናጅተው እንደማያስተምሩ የትንተናው ውጤት ያሳያል፡፡

## 4.1.10. መምህራን አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶችና ስልቶች

ምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለጸው መምህራን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን አቀናጅተው ለማቅረብ የተለያዩ ብልሃቶችንና ስልቶችን መጠቀም እንደሚችሉ በዝርዝር ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡በመሆኑም መምህራኑ የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶችና ስልቶችን ለማወቅ ከምልከታው የተገኙ መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

የ"7ኛ" ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመማር ማስተማር ሂደት አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን እንዴት እንደሚያቀርቧቸው ለማየት ተከታታይ ምልከታዎች

ተካሂደዋል፡፡በተለይም ደግሞ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶችና ስልቶችን ለማወቅ የምልከታ ነጥቦችና የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ፡-10. መምህራን የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶችና ስልቶችን ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | መከታተያ ነጥብ | ድግግሞሽ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 7 | ተማሪዎች አንድን ምንባብ ካነበቡ በኋላ በራሳቸው አባባል እንዲጽፉ የማድረግ ሁኔታቸው | - | 3(16.7%) | - | 3(16.7%) | 12(66.7%) |
| 8 | ተማሪዎች ሃሳባቸውን በጽሁፍ እንዲገልጹ በቂ ጊዜ የመስጠት ሁኔታ | - | 2(11.1%) | 1(5.6%) | 3(16.7%) | 12(66.7%) |
| 9 | ተማሪዎች የሚጽፏቸውን ጽሁፎች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው የማድረግ ሁኔታ | - | 2(11.1%) | 1(5.6%) | - | 15(83.3%) |
| 10 | መ/ሩ (ሯ) ከተማሪ መጽሀፍ ውጪ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ፍላጎት የሚያነሳሳ ይዘት የማካተት ሁኔታቸው | | - | - | - | - |

በተራ ቁጥር 7 ከቀረበው መከታተያ ነጥብ የተገኘው መረጃ 3(16.7%) ከፍተኛ፣3(16.7%) መካከለኛ እና 12(66.7%) በጣም ዝቅተኛ የሚል ነው፡፡በመሆኑም ከዚህ መረዳት

የሚቻለው መምህራን ተማሪዎችን አንድን ምንባብ ካነበቡ በኋላ በራሳቸው አባባል እንዲጽፉ የማድረግ ሁኔታቸው በአመዛኙ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡

በተራ ቁጥር 8 ከቀረበው መከታተያ ነጥብ የተገኘው መረጃ 2(11.1%) ከፍተኛ፣1(5.6%) መካከለኛ፣3(16.7%) ዝቅተኛ እና 12(66.7%) በጣም ዝቅተኛ የሚል ነው፡፡ከዚህ መረዳት የሚቻለው መምህራን ለተማሪዎቻቸው ሀሳባቸውን በጽሁፍ እንዲገልጹ በቂ ጊዜ የመስጠት ሁኔታቸው በአመዛኙ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን የመረጃ ትንተናው ያመለክታል፡፡

በተራ ቁጥር 9 ከቀረበው መከታተያ ነጥብ የተገኘው መረጃ 2(11.1%) ከፍተኛ፣1(5.6%) መካከለኛ እና 15(83.3%) በጣም ዝቅተኛ የሚል ነው፡፡ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለው መምህራን ተማሪዎች የሚጽፏቸውን ጽሁፎች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ የማድረጋቸው ሁኔታ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡እንዲሁም በተራ ቁጥር 10 ከቀረበው መከታተያ ነጥብ የተገኘው መረጃ ሁሉም መምህራን ከተማሪው መጽሀፍ ውጪ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ፍላጎት የሚያነሳሳ ይዘት ሲተገብሩ አልተስተዋለም፡፡

በአጠቃላይ ከሰንጠረዡ ከተገኙት መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው መምህራን አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር ትኩረት ሰጥተው የማቀናጀት ሁኔታቸው ዝቅተኛ መሆኑን የመረጃ ትንተናው ያመለክታል፡፡

መምህራኑ የቋንቋ ክሂሎችን ምን ያህል ትኩረት ሰጥተው እንደሚያቀናጁዋቸው በምልከታው መከታተያ ቅጽ በጥያቄ በተራ ቁጥር 14 ላይ የሚከተለው ጥያቄ ቀርቦ ነበር፡፡መምህሩ(ሯ) አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀት ይሞክራሉ? ከሞከሩስ በምን በምን ስልት? ለ14ኛ ጥያቄ ከመረጃው የተገኘው መልስ እንደሚያመለክተው ከስድስቱ መምህራን አብዛኞቹ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን መምህራን እየጠየቁ ተማሪዎቹ ደግሞ በቃላቸው እንዲመልሱ ሲደረግ ለመመልከት ተችሏል፡፡የተወሰኑት ደግሞ የክፍልና የቤትስራዎችን መስጠትና ተማሪዎቹ የሰሩትን መልስ አብዛኛውን ጊዜ በቃል አንዳንድ ጊዜም በንባብ እንዲያቀርቡ የሚያደርጉበት ሁኔታ እንዳለ ለመመልከት ተችሏል፡፡እንዲሁም በምልከታው መከታተያ ቅጽ በጥያቄ ተራ ቁጥር 15 ላይ መምህሩ (ሯ) ከመማሪያ መጽሀፉ ላይ ካለው በተጨማሪ የቋንቋ ክሂሎችን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎችና ብልሃቶች ምንድናቸው?ለዚህ ጥያቄ ከመረጃው የተገኘው

መልስ እንደሚያመለክተው ሁሉም መምህራን ከመማሪያ መጽሀፉ በተጨማሪ የቋንቋ ክሂሎችን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎችና ብልሀቶች አለመኖራቸውን መመልከት ተችሏል፡፡

በተራ ቁጥር 16 ላይ በጠቅላላ በመማር ማስተማር ሂደቱ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ አጠር ያለ ግላዊ አስተያየት የሚል መከታተያ ነጥብ ቀርቦ የተገኘ አጠቃላይ መረጃ ሲታይ ከስድስቱ መምህራን በሁለቱ ላይ የነበረው አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ የማቅረብ ሂደት ጥሩ ሊባል የሚችል ሲሆን በሁለቱ መምህራን ላይ ደግሞ መካከለኛ የሆነ ቅንጅታዊ አቀራረብ ነበራቸው፡፡ በሌሎቹ በሁለቱ መምህራን ላይ ግን ዝቅተኛ የሆነ ቅንጅታዊ አቀራረብ መኖሩን መመልከት ተችሏል፡፡በተናጠል ሲታይም መ4 እና መ6 ጥሩ መ2 እናመ3 መካከለኛ ሲሆኑ መ1 እና መ5 ላይ ደግሞ የነበረው የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ በአጠቃላይ ደካማ ነው፡፡

በአጠቃላይ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ይዘት ተኮርና ተግባር ተኮር በመጠኑ የተስተዋሉ ሲሆን ስነጽሁፍን መሰረት በማድረግ ማቅረብ ግን ፈጽሞ አልነበረም፡፡እነዚህን ዘዴዎችና ብልሃቶች በተወሰነ መልኩም ቢሆን የሚተገብሩ መምህራን ቢኖሩም አብዛኛዎቹ ግን እንደማይተገብሯቸው ከምልከታው ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

በምዕራፍ  አንድ ላይ እንደተገለጸው ይህ ጥናት የተካሄደው ለአምስት ጥያቄዎች መልስ በመስጠት የጥናቱን አላማዎች ለማሳካት ነው፡፡በተደረገው ጥናትም ጥያቄዎቹ መልስ ስላገኙ አላማዎቹ ተሳክተዋል፡፡የጥያቄዎቹ መልስ የተገኘው ከሰነድ ፍተሻ፣ከጽሁፍ መጠይቅ፣ ከምልከታና ከቃለ መጠይቅ ውጤት ትንተና ሲሆን ትንተናውን መሰረት ያደረገው የውጤት ማብራሪያ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ጥያቄዎች ጥናቱ ሊመልሳቸው የሚገባቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች ሲሆኑ ጥያቄዎቹም  በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት  አንብቦ የመረዳት ይዘቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ ቀርበዋል ወይ? በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ ምን ይመስላል? የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን እንዴት እንዳቀረቧቸውና መምህራን ክሂሎችን አቀናጅተው እንዲያቀርቡ እገዛ ያደርጉላቸዋል? ወይስ አያደርጉላቸውም? መምህራን ስለማንበብና መጻፍ ክሂሎች ታስቦበትና ታቅዶበት ለሚከናወን ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል? የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅተው ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ምን ምን ናቸው? የሚሉት ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘትም በዋናነት አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብን መሰረት ያደረገ የሰነድ ፍተሻ ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም በጽሁፍ መጠይቅ፣በምልከታና በቃለ መጠይቅ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያግዙ የጽሁፍ መጠይቅ ፣የምልከታ ቅጽና መነሻ የሚሆኑ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል፡፡በሰነድ ፍተሻ፣በጽሁፍ መጠይቅ፣በምልከታና በቃለ መጠይቅ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ቅይጥ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ትንተናው ተከናውኗል፡፡የውጤት ትንተናውም አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ዙሪያ የተለያዩ ውጤቶች መገኘታቸውን ያመለክታል፡፡

በመጀመሪያ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱትን አንብቦ የመረዳት ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ ስንመለከት ከሰነድ ፍተሻ፣ ከጽሁፍ መጠይቅና ከቃለመጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት አብዛኛዎቹ በመጽሀፉ ውስጥ የሚገኙ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች በደረጃው የሚገኙ ተማሪዎችን  የእውቀት  ደረጃ  ከግምት ውስጥ ያስገቡ፣አብዛኛዎቹ ከተማሪዎች አካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር የሚዛመዱ ይዘቶችና መልመጃዎች የተካተቱ መሆናቸውን የትንተናው ውጤት ያመለክታል፡፡ መማሪያ መጻህፍት ሲዘጋጁ ማሟላት ካለባቸው ባህሪያት መካከል የይዘት ተገቢነት ሲሆን በደረጃው የሚገኙ ተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ ከግምት ውስጥ ያስገቡ፣አካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር የሚዛመዱ ይዘቶችና መልመጃዎች መሆን እንዳለባቸው 2.1 ላይ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ውጤት ከምሁራኑ ሀሳብ ጋር የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሁለተኛው የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄ በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ ምን ይመስላል? የሚለው

ሲሆን ተማሪዎች የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት ሲለማመዱ ስለጽሁፉ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲተነብዩ፣ትርጉም እንዲሰጡ፣ ላነበቡት ወይም ለጻፉት ነገር ማጠቃለያ እንዲሰጡ ሆነው ሲዘጋጁ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ እንደ መሰረታዊ አንብቦ መረዳትና የጽሁፍ ማቀናበር ችሎታ ማጎልበቻ ብልሃት ተደርጎ ይወሰዳል Gray (1995) እና Beerdgew (2003)፡፡ እንዲሁም ማንበብና መጻፍ ጥብቅ ትስስር ስላላቸው በውህደት ቢቀርቡ ተማሪዎች የትምህርቱን ይዘት በተገቢው መንገድ እንዲረዱት ሊያግዛቸው ይችላል፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም ክሂሎች የቀደመ እውቀትን የሚጠይቁ በመሆናቸው Ruddel (1997)፡፡ በመሆኑም የሰባተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አቀራረብን በተመለከተ ከሰነድ ፍተሻ፣ከጽሁፍ መጠይቅና ከቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት አንብቦ የመረዳት ተግባራት ከመጻፍ ክሂል ጋር ትኩረት ተሰጥቷቸው በቅንጅት እንደቀረቡ የተገኘው መረጃ ትንታኔ ያመለክታል፡፡በመሆኑም የጥናቱ ውጤት ንድፈ ሀሳቡን ካቀረቡት ከምሁራኑ ሀሳብ ጋር በአብዛኛው የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሶስተኛው የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄ የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን እንዴት እንዳቀረቧቸውና መምህራን ክሂሎችን አቀናጅተው እንዲያቀርቡ እገዛ ያደርጉላቸዋል? ወይስ አያደርጉላቸውም? የሚለው ሲሆን እነዚህ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅተው እንዳቀረቧቸውና መምህራን ክሂሎችን ትኩረት ሰጥተው አቀናጅተው እንዲያቀርቡ እገዛ የሚያደርጉ መሆናቸውን ከሰነድ ፍተሻና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ውጤት ዓለም (1995) ካቀረቡት ንድፈ ሀሳብ ጋር በአብዛኛው የሚደጋገፍ ነው፡፡

የንባብን ክሂል ለማዳበር የምንመርጠው የጽሁፍ መጠን ክፍል ውስጥ ካለን ጊዜ አንፃር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ጽሁፍን ለማንበብ የሚወስድብን ጊዜ እና ከንባብ በኋላ ለሚሰሩ ተግባራት የምንሰጠው ጊዜ ከአለን አጠቃላይ ጊዜ ጋር ካልተጣጣመ ልናዳብረው የፈለግነውን የንባብ ክሂል ውጤታማ ልናደርገው አንችልም Lindsay and Knight (2006)፡፡ ይሁን እንጂ በንባብ ክሂል ክፍለ ጊዜ የቀረቡት ተግባራትና የተሰጠው ጊዜ ተመጣጣኝ አለመሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ውጤት ከምሁራኑ ሀሳብ ጋር በከፊል ተቃርኖ አለው፡፡

በመጨረሻም በዚህ ጥናት ውስጥ ምላሽ ከሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች መካከል መምህራን ስለማንበብና መጻፍ ክሂሎች ታስቦበትና ታቅዶበት ለሚከናወን ቅንጅታዊ አቀራረብ

ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል ? የሚለው ሲሆን አብዛኛዎቹ  መምህራን ስለ ቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ግንዛቤው እንዳላቸው በሰጡት ምላሽ ማረጋገጥ ቢቻልም አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂሎች የክፍል ውስጥ አቀራረብ በ4.1.10 ላይ በቀረበው የመረጃ ትንተና በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ላይ የምልከታ ቅጽ በማዘጋጀትና በመቅረጸ ትዕይንት ታግዞ የተደረገው ምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ ትንተና ተደርጓል፡፡ከምልከታ የተገኙት መረጃዎች በምዕራፍ ሁለት ስር ከቀረቡት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ንድፈ ሀሳቦችን መሰረት አድርገው ተተንትነዋል፡፡ ከክፍል ውስጥ ክንውን ምልከታው የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በትግበራው ወቅት ትኩረት ሰጥተው አቀናጅተው የሚያቀርቡት በተወሰነ መልኩም ቢሆን ጥቂቶቹ መምህራን ሲሆኑ አብዛኛዎቹ ግን ትኩረት ሰጥተው አቀናጅተው አለማቅረባቸውን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በመሆኑም  ምሁራኑ ካቀረቡት ንድፈ ሃሳብ ጋር የጥናቱ ውጤት በአብዛኛው የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡ይሁን እንጂ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን ለማሳደግ የሁለቱም ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ጠቃሚ በመሆኑ መምህራን በመጽሀፉ የቀረቡትን ይዘቶች  የማስተማሪያ መሳሪያዎችን አቀራረብ መሰረት በማድረግ ምሳሌዎችን በመስጠት፣ ተማሪዎቹ የሚቀርቡላቸውን ምንባቦች በጥሞና እንዲያነቡ፣ባነበቡት ሀሳብ ላይ በመመስረት በየግላቸው አስፋፍተው እንዲጽፉና ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ በማበረታታትና ንቁ የሆነ ክትትል በማድረግ በተሰጠው ክፍለ ጊዜ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂል በተቀናጀ መልኩ ማቅረብ ቢችሉ የተሻለ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ የውጤት ትንተና ማብራሪያው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የአንብቦ መረዳት ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረባቸው ምን እንደመሚመስልና በአቀራረባቸው ውስጥ ያለውን ጥንካሬና ክፍተት በመተንተን ይዘቶቹ ማሟላት ያለባቸውን ነገሮች እንዲሁም የክፍል ውስጥ አቀራረባቸው ምን እንደሚመስል በመተንተን ተብራርተዋል፡፡ የውጤት ማብራሪያውም በምዕራፍ ሁለት የተገለጹትን የምሁራን ንድፈ ሃሳቦች መሰረት በማድረግ የታዩትን ጥንካሬዎችና ክፍተቶች አስቀምጧል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፣ማጠቃለያና አስተያየት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2007ዓ.ም በተዘጋጀው የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብን በመገምገም ድክመታቸውንና ጥንካሬያቸውን በመለየት ማሳየት ነው፡፡ጥናቱ ያነሳቸውን መሰረታዊ ጥያቄዎች በአግባቡ ለመመለስ ለጥናቱ አላማ ግብ መምታት አስፈላጊ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተግባር ላይ ውለዋል፡፡እነዚህም የመዛግብት ምርመራ፣የጽሁፍ መጠይቅ፣ቃለመጠይቅና የክፍል ውስጥ ምልከታ ናቸው፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው የሚከተሉት የማጠቃለያ ሀሳቦች ላይ ተደርሷል፡፡

## 5.1. ማጠቃለያ

ከዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማዎች መካከል የመጀመሪያው በ2007 ዓ.ም ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ይዘቶቹ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ መቅረባቸውን ወይም አለመቅረባቸውን መመርመር ሲሆን በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ የተማሪዎችን ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ችሎታና ዳራዊ እውቀታቸውን ከግንዛቤ ባስገባ ሁኔታ የተዘጋጁ ናቸው፡፡በመሆኑም ይዘቶቹ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ መቅረባቸውን የትንተናው ውጤት ያመለክታል፡፡

ሁለተኛው የዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማ በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምን እንደሚመስል መመርመር ሲሆን በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት ሃምሳ አራት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ውስጥ ሰላሳ ስድስቱ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ከመጻፍ ክሂል ጋር የተቀናጁ ሲሆን ዘጠኙ ደግሞ ከመናገር ክሂል ተቀናጅተው ቀርበዋል፡፡በመሆኑም አንብቦ የመረዳት ተግባራት ከመጻፍ ክሂል ጋር ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው በቅንጅት እንደቀረቡ ከመጽሐፍ ግምገማው የተገኘው መረጃ ትንታኔ ይጠቁማል፡፡ይሁን እንጅ ለክሂል መልመጃዎች ከቀረቡት መመሪያዎች መካከል የመለማመጃ ጥያቄዎቹ በምን መልኩ እንደሚተገበሩ የተሟላ መረጃ የሚሰጡ የተካተቱ ቢሆንም የተወሰኑት ደግሞ ስለመልመጃዎቹ አሰራር ሙሉ መረጃ የማይሰጡ መመሪያዎች በመጽሀፉ ውስጥ እንደሚገኙ የትንተናው ውጤት ያሳያል፡፡

ሶስተኛው የዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማ የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን እንዴት እንዳቀረቧቸውና መምህራን ክሂሎችን አቀናጅተው እንዲያቀርቡ ድጋፍ ማድረግ አለማድረጋቸውን መመርመር የሚለው ሲሆን እነዚህ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅተው እንዳቀረቧቸውና መምህራን ክሂሎችን ትኩረት ሰጥተው አቀናጅተው እንዲያቀርቡ እገዛ የሚያደርጉ መሆናቸውን ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃ ትንታኔ ያመለክታል፡፡ይሁን እንጂ በንባብ ክሂል ክፍለ ጊዜ የቀረቡት ተግባራትና የተሰጠው ጊዜ ተመጣጣኝ አለመሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

አራተኛው የዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማ መምህራን ስለማንበብና መጻፍ ክሂሎች ታስቦበትና ታቅዶበት ለሚከናወን ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸውን ግንዛቤ ነቅሶ ማውጣት የሚለው ሲሆን አብዛኛዎቹ መምህራን ስለ ቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ግንዛቤው እንዳላቸው በሰጡት ምላሽ ማረጋገጥ ቢቻልም ከክፍል ውስጥ ክንውን ምልከታው የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በትግበራው ወቅት ትኩረት ሰጥተው አቀናጅተው የሚያቀርቡት በተወሰነ መልኩም ቢሆን ጥቂቶቹ መምህራን ሲሆኑ አብዛኛዎቹ ግን ትኩረት ሰጥተው አቀናጅተው አለማቅረባቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

የመጨረሻው የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅተው ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ምን እንደሚመስሉ መመርመር የሚለው ነው፡፡በመሆኑም የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተተኳሪ መምህራን አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች መምህራን አንብበው የተረዱትን እንዲጽፉና የጻፉትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ የሚያደርጉ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ግን አንብበው የተረዱትን ሀሳብ በቃል እንዲያቀርቡ የሚያደርጉ መሆኑን የትንተናው ውጤት ያሳያል፡፡

## 5.2 አስተያየት

በዚህ ጥናት የተገኙትን ውጤቶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡

***ሀ. ለመምህራን***፡-የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተተኳሪ መምህራን አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ጥቂቶቹ አንብበው የተረዱትን እንዲጽፉና የጻፉትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ የሚያደርጉ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ግን አንብበው የተረዱትን ሀሳብ በቃል እንዲያቀርቡ የሚያደርጉ መሆኑን የትንተናው ውጤት

ያሳያል፡፡ይሁን እንጂ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂሎችን ለማሳደግ የሁለቱም ክሂሎች ቅንጅታዊ አተገባበር ጠቃሚ በመሆኑ መምህራን በመጽሀፉ የቀረቡትን ይዘቶች ለመጨረስ ከሚጣደፉ ይልቅ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን አቀራረብ መሰረት በማድረግ ምሳሌዎችን በመስጠት፣ ተማሪዎቹ የሚቀርቡላቸውን ምንባቦች በጥሞና እንዲያነቡ፣ባነበቡት ሀሳብ ላይ በመመስረት በየግላቸው አስፋፍተው እንዲጽፉና ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ በማበረታታትና ንቁ የሆነ ክትትል በማድረግ በተሰጠው ክፍለ ጊዜ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂል በተቀናጀ መልኩ ማቅረብ ቢችሉ የተሻለ ይሆናል፡፡

**ለ. ለመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች**፡-በመጽሐፉ ውስጥ ለክሂል መልመጃዎች ከቀረቡት መመሪያዎች መካከል የመለማመጃ ጥያቄዎቹ በምን መልኩ እንደሚተገበሩ የተሟላ መረጃ የሚሰጡ የተካተቱ ቢሆንም የተወሰኑት ደግሞ ስለመልመጃዎቹ አሰራር ሙሉ መረጃ የማይሰጡ"የሚከተሉትን አሟሉ፡፡" የሚሉ ትዕዛዛትን ያዘሉ ሲሆኑ ምላሻቸውም በጽሁፍ ይሁን በቃል ያልታወቁ መመሪያዎች በመጽሀፉ ውስጥ እንደሚገኙ የትንተናው ውጤት ያብራራል፡፡በመሆኑም በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ሁሉም አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ምላሽ ስለሚሰጥባቸው በተሟላ ሁኔታ መመሪያዎች እንዲኖራቸው ቢደረግ የተሻለ ነው፡፡እንዲሁም በንባብ ክሂል ክፍለ ጊዜ የቀረቡት ተግባራትና የተሰጠው ጊዜ ተመጣጣኝ አለመሆኑን የትንተናው ውጤት ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የመማሪያ መጽሀፍ አዘጋጆች የሚያዘጋጁትን የይዘት ስፋት ከጊዜው ጋር የተመጣጠነ ቢያደርጉ የተሻለ ይሆናል፡፡

**ሐ.ለጥናት አድራጊዎች**፡- ተመራማሪዎች በዚህ ርዕስ ላይ በስፋት ቢያጠኑ ለአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች፣ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲሁም ለቋንቋው እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ እና የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ እንደሚያስችሉ አጥኝዋ ታምናለች፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሞገስ አመራ ::( 1999)፡፡ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን

በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና፡፡ ለድህረምረቃ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ ባህር ዳር

ዩኒቨርስቲ ፣(ያልታተመ)፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡ (1981)፡፡ስነልሳንና ቋንቋን ማስተማር፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣(ያልታተመ)፡፡

ትዝታ ደሳለኝ፡፡ (2003) ፡፡"የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛ ቋንቋን የማስተማር

አተገባበርና የተማሪዎች አቀባበል ፍተሻ"፡፡ለድህረምረቃ የቀረበ ጥናታዊ

ጽሁፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፣(ያልታተመ)፡፡

አለም እሸቱ ::( 1995)::"በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ

የክሂሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች አወቃቀር፡፡"ከጥቅምት

25-29/1995 ዓ.ም ለአማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጁ የ7ኛ እና

የ8ኛ ክፍሎች መርሀ ትምህርቶችን ለማሻሻል ለተዘጋጀው አውደ ጥናት የቀረበ

(ከ/ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ኢንስቲትዩት) አዲስ አበባ፣(ያልታተመ)፡፡

አታክልቲ መኮንን ፡፡ (1998) ፡፡"የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛን የማስተማር ዘዴ

አተገባበር ፍተሻ"፡፡ለድህረምረቃ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣(ያልታተመ)፡፡

እሸቴ መብራት ፡፡ (2003)፡፡"የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ የተደረገ ሙከራዊ ጥናት"፡፡ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣(ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2001)፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡(ሁለተኛ ዕትም)* አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

Atkin S, J.etal.(1996).*Skills development methodology part two* Addis Ababa: Addis Ababa Universty press.

Barrs, Myra. (2000).The Reader in the Writer.Reading (united kingdom Reading Association), July, 54-60.

Block, CathyColling. (1997).*Teaching the Language arts.Expanding thinking Student Centered instraction*. Bastone: Allyn and Bacon.

Block, Cand Mangieri,J.(1995).*Reason to Read Thinking Strategies for life Through Literature,* Volumes 1-3 Menlo Park, CA: Addion.

Byrne, D. (1981). *Integration Skill in Johnson and Marrow*.HongKong: Long man Group Ltd.

Celce-Murcia,M.(eds.)(1991).*Teaching English as a Second or Foreign*

*Language*.(2nd ed.).Boston: Heinl & Heinle publishers.Ltd.

Conley, Mark W. (1997).*Reading and Writing: teaching for the connection*. (2nd ed.)Less har court Brache and company.

Creswell,J. W.(2009).Research Design,Qualitative,Quantitative & Mixed Method Approaches.(3rd ed.). University of Nebraska -Lincoln.

Cunnings worth, A.(1984).*Evaluating and selecting EFL Teaching Materials*. London: Heinemann Educational Books.

____________________.(1995).*Choosing your Course book.Oxford*: Heinemann.

Dawson ,A.etal.(1963).*Fundamentals of Basic Reading Instractions*. New York: D.Mackay, co.

Durkin, D. (1997). Teaching themtoread.(5th edition)Boston:Allyn and BaconInc.

Gary, cobine. (1995).Writing as aresponse to reading. (http:// www.vatide.com./pnp/ERIC/ write- read.htm.)

Gilbert,J.(1982).Clear Speech:Pronunciation and Listening Comprehension in English.TesolQuarterly.Vol 25 No.1(spring,1991) PP.51-75.

Grant, N.(1987).*Making The most of your text book*. Newyork: Longman Ink.

Grellet,F.(1981).*Developing reading skills*.Cambridge:Cambridge unverstiy Press.

Hadge, T.(1988).*Writing Resource Book for Teachers*. In Alan Maley (ed.): Oxford Universty Press Hong Kong.

Harmer,J.(1991).*Teaching the practices ofEnglish Language*.London Long man.

Harp, Bill and Brewry, John.(1996).*Reading and writing Teaching for the connection*.(2nd ed.)S.A: Har court brace and campany.

Johnson,P.(1982)."Effects on Reading comprehension of Building Back ground Knowledge." TESOL Quarterly 16:4,503-516.

Lindsay and knight.(2006).*Learning and teaching English:A course for teachers*.Oxford: oxford university press.

Littile wood, W.(1981*).Communcative language teaching*.Cambridge:Cambridg Unverstiy press.

McDonough, Jand Shaw C.(1992).*Integrated Skills in ELTA Teachers Guide*.Oxford: Black well.

___________________.(1993).*Materials and Methods in ELT*. Cambridge: Black well publisher Ltd.

May, Frank B.(1990).*Reading as communication*.New york:Macmilan Publishing company.

Nuttall,C.(1982). Teaching Reading Skills in aForeign *Language*. London.Heinemann Educational books.

Nunan D.(1988). *Syllabus Design*. Oxford: Oxford university press.

Oxford, R. (2001).Integrated Skills in the ELS/EFL Class room.
ERTV. Maio:eric@Cas.org.

Raimes, A. (1983). *Techniques in teaching writing*. Oxford: Oxford University press Inc.

Richards, J.C. (1990).*The language teaching matrix*. Cambridge: Cambridge University press.

__________.(2001*).Curriculum development in teaching*.Cambridge: Cambridge Universit Press.

Rivers, W. (1981).*Teaching Foreign Langage Skills*.Chicago:Cicago University Press.

Ruddel,MarthaRapp (1997).Teaching content Reading and Writing. (2nd.ed.). U.A.S: Allyn and Bacon.

Seligar,H.W and Shohamy,J.(1989).Second Languge Research Methods.oxford: University press.

Stern, H.H.(1992).*Issues and Options in Language Teaching*.Oxford University Press.

Ur.P.(2006).*A course in language Teaching Practice and Theory* .13th Printing Cambridge: Cambridge University.

Widdowson, H. G.(1978).*Teaching Language as Communication*.Oford:oup

Williams,(ed.)(1984).*Reading in the Language Class room .London: Macmillan Publishers Ltd.*

__________.*(1990).Reading in the Class room. London:Macmillan Publishers Ltd.*

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

### ምዕራፍ አንድ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያይታችሁ መልሶቻችን በቃላችሁ ግለጹ፡፡

ሀ.መስህብ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ.መስህቦቻችን ከሚለው ርዕስ በታች ከቀረበው ምስል ምን ተረዳችሁ? ምክንያት መስጠት ትችላላችሁ?

ጉዞ ወደ ሀዋሳ የሚለውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት ስዕሉን አስተውሉና ከስዕሉ የተረዳችሁትን በቃላችሁ ግለጹ፡፡

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡

ሀ."የአፈር እንክብካቤ"ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ.ከስዕሉ የተገነዘባችሁት ሀሳብ ምንድነው?

## ምዕራፍ ሁለት

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ.የቤተሰብ ምጣኔ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ.በምንባቡ ከቀረቡት ስዕሎች ምን እንደተገነዘባችሁ በቃላችሁ ግለጹ፡፡

ከዚህ በታች በቀረቡት አባባሎች ላይ ተወያዩ፡፡

ሀ.ልጅ ሀብት ነው፡፡

ለ.ልጅ በዕድሉ ያድጋል፡፡

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በያዙት ሀሳብ ላይ ተወያዩ፡፡

ሀ. የህጻናት እንክብካቤ　　　　መ. ሥነልቦና

ለ. ዓለማቀፋዊ ስምምነቶች　　　　ሠ. መብት

ሐ. ሰውሠራሽ አደጋዎች

### ምዕራፍ ሶስት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ስለ ኤች.አይ.ቪ.የምታውቁትን ተናገሩ፡፡

ለ."ኤች.አይ.ቪ."በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ስዕሎች ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ተናገሩ፡፡

ለተለያዩ ሱሶች ተገዢ መሆን ምን ምን ጉዳቶችን ያመጣሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?

መልሶቻችሁን በቃላችሁ አቅርቡ፡፡

የሚከተለውን ቢጋር አሟሉ፡፡






## ምዕራፍ አራት

የሚከተሉትን ጥያቄዎችን ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ.የህይወት ታሪክ ማለት ምን ማለት ነው?

ለ.በጣም ታዋቂ የሚባሉትን ሴት የኪነ-ጥበብ ሰዎች ስም ጥቀሱ?

ለሚከተለው ጥያቄ የቀደመ እውቀታችሁን በመጠቀም በቃላችሁ መልሱ፡፡

በጣም ተወዳጅ ከሆኑት አንጋፋ ኢትዮጵያዊ ድምፃውያን መካከል ምንን ታውቃላችሁ?ለምን ተወዳጅ የሆኑ ይመስላችኋል?

ሀ.ስዕሉን በትክክል አስተውላችሁ የተረዳችሁትን ተናገሩ፡፡

ለ.ከዚህ በታች በስዕሉ የምታዩአቸውን ሰው ዕውቅና ያገኙባቸው ስራዎች ምን ምን ይመስችኋል?

## ምዕራፍ አምስት

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡

ሀ.ሰዎች በተስቦ፣በአንጀት ቁስለትና በጃርዲያ በሽታዎች የሚያዙት በምን ምክንያት ይመስሏችኋል?

ለ.በውኃ አማካኝነት የሚመጡ ተላላፊ በሽታዎችን እንዴት መከላከል ይቻላል?

ውኃ ለምን ለምን እንደሚጠቅም በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ተወያዩና በቃላችሁ ግለጹ፡፡

የሚከተለውን የቅድመንባብ ጥያቄ የቀደመ እውቀታችሁነ በመጠቀም በቃላችሁ መልሱ?

ውኃ ለመጠጥ አገልግሎት ከመዋሉ በፊት በምን ዘዴ ሊጣራ ይችላል?

## ምዕራፍ ስድስት

"ከሞት ጋር ድርድር" በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች የቀደመ እውቀታችሁን መሰረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ.በአካባቢያችሁ በሰዎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሄ የሚያገኙት እንዴት ነው?

ለ.በስዕሉና "በላ ልበልሃ" በሚለው ርዕስ መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት ያለ ይመስላኋል?

የሚከተሉትን ጥያቄዎች የቀደመ እውቀታችሁን መሰረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ.በሰዎች መካከል የሚደረገው የእርስበርስ መረዳዳት ምን ጠቀሜታ የሚያስገኝ

ይመስላችኋል?

ለ.ከጓደኞቻችሁጋር እንዴት ትረዳዳላችሁ?

## ምዕራፍ ሰባት

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች የቀደመ እውቀታችሁን መሰረት በማድረግ በቃላችሁ

መልሱ፡፡

ሀ.ሰዎች ጫት የሚቅሙት በምን ምክንያት ይመስላችኋል?

ለ.ጫት መቃም ጉዳት የሚያስከትል ይመስላችኋል?እንዴት?

የሚከተሉትን ጥያቄዎች የቀደመ እውቀታችሁን መሰረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ."የሱሰኝነት ተጽዕኖ" የሚለው ርዕስ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ለ.ሱሰኛ መሆን ምን ምን ችግሮችን የሚያስከትል ይመስላችኋል?

የሚከተሉትን ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ.ለሱስ ተገዥ መሆን ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ.ሱሰኞችን ከሱሳቸው ማላቀቅ ይቻላል?እንዴት?

## ምዕራፍ ስምንት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች የቀደመ እውቀታችሁን በመጠቀም በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ.በፎቶግራፉና በምንባቡ መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት ያለ ይመስላችኋል?

ለ.ስለእቴጌ ጣይቱ ብጡል የምታዉቁትን ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

የሚከተለውን ጥያቄ የቅድመንባብ እውቀታችሁን በመጠቀም በቃላችሁ መልሱ፡፡

የሀገር ፍቅር ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?በምንስ ይገለጻል?

በቢጋር ሠንጠረዡ ውስጥ ባለው መነሻ ሀሳብ መሰረት በዙሪያው ያሉትን ክቦች አሟሉ፡፡




## ምዕራፍ ዘጠኝ

"ተላላፊ በሽታዎች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት ከቀደመ እውቀታችሁ በመነሳት የቢጋር ሠንጠረዡን አሟሉ፡፡




ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት ምክንያት እያቀረባችሁ በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ.የቲቢ. በሽታ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ እንጅ በሌሎች ሀገሮች ጠፍቷል፡፡

ለ."ቲቢ."የሚለው አህጽሮተቃል "ቱበርክሎሲስ"ማለት ነው፡፡

ሐ. ቲቢ. ሳንባን እንጂ ሌሎች የአካል ክፍሎችን አያጠቃም፡፡

መ. የቲቢ. በሽታ በህክምና ይድናል፡፡

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. በአካባቢያችሁ በስፋት የሚታወቁ ተላላፊ በሽታዎች ምን ምን ናቸው?

ለ.ከመጸዳጃ መልስ ወይም ከምግብ በፊትና በኋላ እጃችንን በሳሙናና በውኃ እንድታጠብ

የሚመከረው ለምንድነው?

## ምዕራፍ አስር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ."የተጻፈና ያልተጻፈ ግጥም" የሚለው ርዕስ ስለምን እንደሚገልጽ ገምታችሁ ተናገሩ?

ለ.በተጻፉና ባልተጻፉ ግጥሞች መካከል ምን ዓይነት አንድነትና ልዩነት ያለ ይመስላችኋል?

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. የምታውቋቸውን የቃላዊ ግጥም ዓይነቶች ዘርዝሩ፡፡

ለ. የምታውቋቸው ቃላዊ ግጥሞች የሚከናወኑባቸውን አጋጣሚዎች ተናገሩ፡፡

በ2ኛው ሳምንት በ4ኛ ቀን ካነበባችኋቸው ቃላዊ ግጥሞች የምታስታውሷቸውን በቃላችሁ

ተናገሩ፡፡

# አባሪ ሁለት

## ምዕራፍ አንድ

### የማንበብ ሂደት

"መስህቦቻችን" በሚል ርዕስ የቀረበውን ገላጭ ጽሁፍ ለዋና ዋና ሀሳቦች ትኩረት በመስጠት ድምጽ ሳታሰሙ በየግላችሁ አንብቡ፡፡

"ጉዞ ወደ ሐዋሳ" የሚለውን ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በእያንዳንዱ የጉዞ መዳረሻ ሊታዩ የሚችሉ ነገሮችን ቀድማችሁ በመተንበይ ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

"የአፈር እንክብካቤ" በሚል ርዕስየቀረበውን ምንባብ ድምጽ ሳታሰሙ በማንበብ በየአንቀጹ ያሉ ዋና ዋናሃሳቦችን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

"የቤተሰብ ም ጣ ኔ ም ንነት " በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በዋናና ዝርዝር ሃሳቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በማስተዋል ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

ቀጥሎ"ስለቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ አመለካከቶች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምጽ ሳታሰሙ በማንበብ ተናጋሪው ማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት ተገንዘቡ፡፡

"ህጻናት እንክብካቤ" የሚለውን ምንባብ ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

"ኤች.አይ.ቪ."በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የነገሮችን ምክንያትና ውጤት በመመርመር ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

"ወይ አለማወቅ?" የሚለውን ምንባብ ምክንያት ውጤት ለመለየት ድምጻችሁን ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

"የኤች አይ.ቢ./ኤድስ ተጽዕኖ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምጻችሁን ሳታሰሙ የምክንያትና ውጤትን ትስስር እየለያችሁ አንብቡ፡፡

## ምዕራፍ አራት

" ሮማነወርቅ ካሳሁን" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የታሪኩን ቅደም ተከተል በመገንዘብ ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ድምጽ ሳታሰሙ በማንበብ የምንባቡን መልዕክት በድርጊት ቅደም ተከተል ለመረዳት ሞክሩ፡፡

"እጅግ የተከበሩ፣የዓለም ሎሬት፣ ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ" የሚለውን ተራኪ ምንባብ በጊዜ ቅደም ተከተል የተከናወኑ ድርጊቶችን በመለየት ድምጻችሁን ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

## ምዕራፍ አምስት

"ተዋበችና የውኃ አጠቃቀሟ " የሚለውን ምንባብ ስታነቡ ባለታሪኳ ለሚያጋጥሟት ችግሮች ቀድማችሁ መፍትሂውን በመገመት ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ምክንያቶቹ ሊያስከትሏቸው የሚችሉ ውጤቶችን በመገመት ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

"የውኃ አጠቃቀም" በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ዝርዝር ሀሳቦችን ከዋና ሀሳቦች ለይታችሁ በመረዳት ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

"ከሞት ጋር ድርድር" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የአንዱን ገጸባህርይ ንግግር ካነበባችሁ በኋላ የሌለው ምላሽ ምን ሊሆን  እንደሚችል በመገመት ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

"በላ ልበልሃ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በከሳሽና በተከሳሽ መካከል የሚፈጠረውን ስሜትና የአካል እንቅስቃሴ በአዕምሯቸው ምስል እየፈጠራችሁ ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

"እርስበርስ መረዳዳት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምልልሳዊ ምንባብ በቅድመንባብ ጥያቄዎች የሰጣችኋቸውን መልሶች እያረጋገጣችሁ ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

ቀጥሎ"ጫት መቃምና መዘዙ" በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያሉትን ሀሳቦች በምክንያትና ውጤት ግንኙነት እያደራጃችሁ ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

ቀጥሎ "የሱሰኝነት ተጽዕኖ" የሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የምክንያትና ውጤት ግንኙነትን በማጤን ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

ቀጥሎ"ከሱሰኝነት ነጻ መውጣት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የሀሳቦችን የምክንያትና ውጤት ግንኙነት በማጤን ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

"እቴጌ ጣይቱ ብጡል" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ በመሆን ንዑስ ርዕስ በመከፋፈልና ድምጽ ሳታሰሙ በማንበብ የተረዳችሁትን ለጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

"የሀገር ፍቅር" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ድምጽ ቀጥሎ "ማህበረሰብን ማገልገል" በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ጸሀፊው/ዋ ለምን ዓላማ እንደጻፈው/ ችው ለማወቅ ትኩረት ሰጥታችሁ ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ

ቀጥሎ"ተላላፊ በሽታዎች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በቅድመንባብ ተግባራት ላይ ከሰጣችኋቸው መልሶች ጋር በማገናዘብ ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

"የቲቢ በሽታ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በየንዑስ ርዕሶቹና በግራፉ የቀረቡትን ሀሳቦች አቀናጅታችሁ በመረዳት ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

ቀጥሎ"ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መልዕክቱን ከቀደመ እውቀታችሁ ጋር በማገናዘብ ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

## ምዕራፍ አስር

ተግባር ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በተጻፈና ባልተጻፈ ግጥም መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በማጤንና የግጥሞቹን ዜማ በመጠበቅ ለራሳችሁ በሚሰማ ድምጽ አንብቡ፡፡

ተግባር  ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞች ለራሳችሁበሚሰማ ድምጽ በማንበብ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ተረዱ፡፡

ተግባር ቀጥሎ "ቃላዊ ግጥሞች"በሚል ርዕስ የቀረቡትን ግጥሞች የተገተሙበትን ዓላማ በውል በማጤን ለራሳችሁ በሚሰማ ድምጽ አንብቡ፡

# አባሪ ሶስት

## አንብቦ መረዳት

## ምዕራፍ አንድ

## 1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡

ሀ. መስህቦች በስንት ይከፈላሉ?ምን ምን ተብለው ይጠራሉ?

ለ. የላሊበላ ውቅር አብያተክርስቲያናት አሰራር እንዴት ነው

ሐ. የራስ ዳሽን ተራራ ከባህር ወለል በላይ ስንት ሜትር ከፍታ አለው

መ. በኢትዮጵያ በከፍተኛው ቦታና በዝቅተኛው ቦታ መካከል ያለው ልዩነት በአሃዝ ሲገለጽ

ምን ያህል ነው?

ሠ. የሀገራችንን ጎብኝዎች የሚያስተናግዱ ተፈጥሯዊ መስህቦችን ጥቀሱ፡፡

ረ. የሀረር ከተማ ከአዲስ አበባ በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?

ሰ. ከምንባቡ የአድናቆት መግለጫ ቃላትን ለይታችሁ አውጡ፡፡

ሸ. የጣና ሀይቅ በአፍሪካ ካሉት ሀይቆች ጋር በስፋቱ ሲወዳደር በስንተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል?

ቀ. ኢትዮጵያ ካሏት ሰውሰራሽና ተፈጥሯዊ መስህቦች መካከል በሰፊው የተገለጸው የትኛው

ነው?

በ.ኢትዮጵያ ከቱሪዝም ሀብቷ ተጠቃሚ የምትሆነው እንዴት ነው?

ተ.ከራስ ዳሽንና ከዳሎል የተኛው ሞቃታማ ነው?እንዴት ይታወቃል?

## 2ኛ ሳምንት 4ኛ ቀን

ተግባር 1 ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ጻፉ፡፡

ሀ. ትረካው ወደ ሀዋሳ ይዞን የሄደው በምንድነው?

ለ. ሙቀቱ የጨመረው ከየት ጀምሮ ነው?

ሐ. የሞጆ ከተማ "የበርሃዋ ገነት" የተባለችበትን ምክንያት ምንድነው?

መ.ጎብኝዎች ዝዋይ ከተማ እንደደረሱ ምን ምን ዓይነት እጽዋትና የጓሮ አትክልቶችን ተመልከቱ?

ሠ. ከፈጣኑ መንገድ ላይ ሆኖ የሚታየው ተራራ ስሙ ማን ይባላል?

ረ. ከምንባቡ ውስጥ ያሉ የአድናቆት ቃላትን ወይም ሀረጋትን ለይታችሁ አውጡ፡፡

ተግባር 2

"ጉዞ ወደ ሀዋሳ" የሚለውን ምንባብ በአንድ አንቀጽ አሳጥራችሁ ጻፉ፡፡

3ኛ ሳምንት 7ኛ ቀን

ተግባር 1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ"እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለትና ምክንያት በመስጠት በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ.አፈር ውስን የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡

ለ.ደጋማ አካባቢ ያለው አፈር ለም ስለሆነ ለሰብል ምርት ምቹ ነው፡፡

ሐ.ተራራማ ቦታዎችን በደን መሸፈን አፈር እንዳይሸረሸር ያደርጋል፡፡

ተግባር 2 ቀጥሎ ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ጻፉ፡፡

ሀ. አፈር ህይወትን ለማስቀጠል የሚያስችል የተፈጥሮ ሀብት የተባለው ለምንድነው?አብራርታችሁ ጻፉ፡፡

ለ.የአፈር ለምነትን ከምንጠብቅባቸው ዘዴዎች መካከል ሁለቱን መርጣችሁ በራሳችሁ አገላለጽ ማብራሪያ ስጡ፡፡

ሐ.ከምንባቡ ከተጠቀሰው በተጨማሪ የአፈር ለምነትን ሊጨምሩ የሚችሉ ነገሮችን

አብራርታችሁ ግለጹ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

### 1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡

ሀ. ተናጋሪዋ ስለቤተሰብ ምጣኔ ምንነት ምን በማለት ገለጹ፡፡

ለ. የልጆችን ቁጥር መመጠን ለምን አስፈለገ?

ሐ. የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች ተፈጥሯዊና ዘመናዊ የተባሉት በምን ምክንያት ነው?

መ. ተናጋሪዋ"ይህ እኮ ትልቅ ነገር"ሲሉ "ይህ" የሚለው ምንን ያሳያል፡፡

ሠ.ወላጆች የወሊድ መቆጣጠሪያን ለመጠቀም ማንን ማማከር አለባቸው?

ረ.ተናጋሪዋ የቤተሰብ ምጣኔን በተመለከተ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላችኋል?

ሰ. የምንባቡን ዋና ሀሳብ በሶስት ዓረፍተ ነገሮች ግለጹ፡፡

### 2ኛ ሳምንት 4ኛ ቀን

ተግባር 1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት ምክንያት በመስጠት በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. የቤተሰብ ምጣኔ መጠቀም ልጆችን መጥኖ ለመውለድ ይረዳል፡፡

ለ. ብዙ ሰዎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትን በአሉታ ይመለከቱታል፡፡

ሐ. "የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትን መጠቀም ለመሀንነት ይዳርጋል" በሚለው ሀሳብ ብዙ ሰዎች ይስማማሉ፡፡

መ. ልጆችን እንደ ገቢ ምንጭ የሚቆጥሩ በገጠር የሚኖሩ ወላጆች ናችው፡፡

ተግባር 2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡

ሀ. "አንዳንድ ወላጆች በሁለቱም ጾታ ለማግኘት ሲሉ የቤተሰብ ምጣኔ አይደግፉም" ከሚለው

አገላለጽ ምን ተገነዘባችሁ?

ለ. ስለቤተሰብ ምጣኔ በአሉታዊነት ከተዘረዘሩት አመለካከቶች መካከል ምናልባት እናንተ በአወንታ የምትመለከቱት ካለ ግለጹ፡፡

ሐ. የቤተሰብ ምጣኔ ለወላጆችና ለልጆች የሚኖረው ጠቀሜታ ምንድነው?

መ.የቤተሰብ ምጣኔን በተመለከተ የማህበረሰቡ አመለካከቶች ምን ምን ናቸው?

3ኛ ሳምንት 7ኛ ቀን

ተግባር 1 ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ በቃላችሁ መልሱ፡፡

1.ወላጆች ለልጆቻቸው ማድረግ ከሚገባቸው ነገሮች ውስጥ የማይደገፈው የትኛው ነው?

ሀ. ህጻናትን በወቅቱ ማስከተብ ሐ.የወላጅ ፍቅር መስጠት

ለ. መብቶቻቸውን ማክበር መ.ህጻናትን ልቅ መተው

2. ህጻናት በስነልቦና የሚጎዱበት ምክንያት ምንድነው?

ሀ. እቤት ውስጥ ሰላም ማግኘት ሐ.የወላጅ ፍቅር ማግኘት

ለ.ጭቅጭቅ ባለበት አካባቢ ማደግ መ.ለሚጠየቁት ጥያቄ ተገቢ መልስ መስጠት

3.ሀገራችን ከፈረመቻቸው ዓለማቀፋዊ ስምምነቶች መካከል አንዱ የትኛው ነው?

ሀ.ለሕጻናት የሀገራቸውን ታሪክ ማሳወቅ

ለ. ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲወዱ ማድረግ

ሐ. የህጻናትን ሞት መቀነስ

መ. የህጻናትን መዝናኛ ቦታ መገንባት

ተግባር 2 በአረፍተነገሩ ውስጥ በተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ፍቻቸውን

ጻፉ፡፡

ሀ.ወላጆች ለልጆቻቸው ከሚያደርጉት እንክብካቤ አንዱ <u>የወላጅ ፍቅር</u> ማሳየት ነው::

ለ.ወላጆች ለህጻናት <u>በጨቅላነት</u> ዕድሜያቸው ልዩ እንክብካቤ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሐ. ወላጆች የህጻናት ጤንነት ከመጠበቅ በተጨማሪ በጥሩ ስነምግባር <u>አንፀው</u> የማሳደግ ሃላፊነት አለባቸው፡፡

መ.ህጻናትን ተረት እንዲያዳምጡ፣ባህላዊ ጨዋታዎችን እንዲመለከቱና <u>ወጎችን</u> እንዲሰሙ ማድረግ ከማዝናናት በተጨማሪ የሀገራቸውን ታሪክ ባህል እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

### 1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

ተግባር 1 ከዚህ በታች በክቡ ውስጥ የሰፈሩትን ሀሳቦች በምክንያትና ውጤት ግንኙነት በማዋቀር በደብተራችሁ ላይ ጻፏቸው፡፡

ምሳሌ፡-

| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| • የሰውነት የበሽታ መከላከል አቅም ሲዳከም | • ለተለያዩ በሽታዎች ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ |
| • | • |
| • | • |
| • | • |
| • | • |

ተግባር 2 በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመለያየት በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ.በኤች.አይ.ቪ.ና በኤድስ ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ለ.ኤች.አይ.ቢ. ከሚተላለፍባቸው መንገዶች በቀዳሚነት የሚጠቀሰው ምክንያት ምንድን ነው?

## 2ኛ ሳምንት 4ኛ ቀን

ተግባር ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡

ሀ.ባለታሪኩ ትምህርቱን ዳር ሳያደርስ የቀረበት በምክንያት ምንድን ነው?

ለ.ባለታሪኩን ለኤች.አይ.ቢ.ኤድስ እንዲጋለጥ ያደረጉትን ምክንያቶች ዘርዝሩ?

ሐ.በልጅነት እድሜ ገንዘብ ከተገኘ ምን ዓይነት ጥንቃቄዎችን ማድረግ ይገባል?

መ.ባለታሪኩ የተለያዩ የህመም ስሜቶች ሲሰሙትና የሰውነት ክብደቱ ሲቀንስ ምን አደረገ?

ሠ.በኤች.አይ.ቢ.ቫይረስ የተያዙ ሰዎች በሽታውን ወደ ጤነኞች እንዳያስተላልፉ ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ረ.ከባለ ታሪኩ ምን ተማራችሁ? ባለታሪኩን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

## 3 ኛ ሳምንት 7ኛ ቀን

ተግባር የሚከተለውን የቢጋር ሳጥን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ ምክንያቶቹ የሚያስከትሏቸውን ውጤቶች በትክክል አስፍሩ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ.የወጣቶችና የጎልማሶች በቫይረሱ መጠቃታ | • |
| ለ.የኤች.አይ.ቪ. መስፋፋት | • |
| ሐ.ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ በሰዎች ላይ መኖር | • |

ተግባር 2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡

ሀ. "በሚሊዮኖች የሚገመት ገንዘብ ኤች.አይ.ቢ.ኤድስን በሚመለከት ለሚይዙ መርሀግብሮች እንደሚወጣ መረጃዎች ያሳያሉ" በሚለው ዓረፍተነገር የተላለፈው ዋና መልዕክት ምንድነው?

ለ. በአንዲት ሀገር ትክክለኛ የሆነ የህዝብ ስብጥር አለ ለማለት የሚቻለው ምን ሲሆን ነው?

ሐ. ሰዎች በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ እንዳይያዙ ምን ትመክራላችሁ?

መ. ከኤች.አይ.ቪ.ጋር የሚኖሩ ሰዎች በሌሎች ሰዎች መገለል እንዳይደርስባቸው ለማድረግ መፍትሄው ምን ይመስላችኋል?

## ምዕራፍ አራት

### 1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

ተግባር የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ አዘጋጅታችሁ ዋና ዋና ሀሳቦችን አስፍሩ፡፡




### 2ኛ ሳምንት 4ኛ ቀን

ተግባር 1 በምንባቡ መሰረት የሚከተለውን የትረካ ቅደም ተከተል ቢጋር በማሟላት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡




3ኛ ሳምንት 7ኛ ቀን

ተግባር ቀጥሎ የቀረበውን የቢጋር ሰንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ በስሩ ሊካተቱ የሚችሉትን ነጥቦች ጻፉ፡፡






ምዕራፍ አምስት

2ኛ ሳምንት 4ኛ ቀን

ተግባር 1 በሰንጠረዡ ውስጥ ለቀረቡት ምክንያቶች ለእያንዳንዳቸው ቢያንስ ሁለት ውጤቶች ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡-

| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| ወንዞችና ሀይቆችን በአግባቡ መያዝ | የኤሌትሪክ ሀይል አገልግሎት በስፋት ማግኘት ይቻላል፡፡ |
| | በመስኖ እርሻ ምርታማነትን ማሳደግ ይቻላል፡፡ |

| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| ሀ.የውኃ ሀብትን በአግባቡ መያዝ ወይም መጠቀም | ሀ. |
| | ለ. |
| | ሐ. |

| | |
|---|---|
| ለ.የውኃ ለሀይል ምንጭነት አለመጠቀም | ሀ. |
| | ለ. |
| | ሐ. |

ተግባር 2 ምንባብን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ሀሳቦች በምክንያት አስደግፋችሁ በጽሁፍ ግለጿቸው፡፡




## ምዕራፍ ስድስት

### 1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

ተግባር 1 ምንባቡን መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ በትክክል አሟሉ፡፡

| መቼ | ገጸ | የክርክር እድገት ከየት ወደ | የግጭቱ ማዕከላዊ ነጥብ | የተደረሰበት |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

| ተ | ባህሪያት | የት | | ውጤት |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

ተግባር 2"ከሞት ጋር ድርድር" በሚል ርዕስ የቀረበውን የምንባብ ጭብጥ በራሳችሁ አገላለጽ በአንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

2ኛ ሳምንት 4ኛ ቀን

ተግባር 1 የ"በላልበልሃ" ምንባብን መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ያለውን ሰንጠረዥ በተገቢ ፍሬ ነገሮች አሟሉ፡፡

መቼት

- ቦታው፡-በአንድ የገጠር አካባቢ
- ጊዜው

መዋቅር

| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| | |

ዋና ገጸባህሪያት

ግጭት

መፍትሄው ምን ሆነ?

ተግባር 2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች "በላ ልበላሃ" በሚለው ምንባብ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡

2. ከሳሽ፣"መጣሁ እንደ ውሃ ስፈስ፣

እንደ.ጋዣ ስነፍስ፣"ሲል ከሳሹ ስለራሱ ምን መግለጹ ነው?

2. "እንዴት ለቀበሮ የላት ገሳ፣

ትገባለች አርባ ክንድ ምሳ"ብሎ ተከሳሽ ሲመልስ ምን ማለቱ ነው?

3. ተከሳሽ "ፍየል መንታ ትወልዳለች፣

አንዱን ለመጣፍ አንዱን ለወናፍ፣

መጣፉ እኔ ወናፍ አንተ"ሲል ከሳሹን ምን እያለው ነው?

3ኛ ሳምንት 7ኛ ቀን

ተግባር 1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ሰዎች እድር የሚያቋቁሙት ለምንድነው?

ለ. ወይዘሮ ብርቱካን ከእድሩ እርዳታ የሚያገኙ ይመስላችኋል?

ሐ. የእድር አባል መተዳደሪያ ደንብ ያወጡት ምን ሊያደርጉት ነው?

መ. የእድር አባላት መሆን የሚችሉት በአንድ ሰፈር የሚኖሩ ሰዎች ብቻ ናቸው?ለምን?

ሠ. በአካባቢያችሁ የተቋቋሙ ዕድሮች በምንባቡ ከተገነዘባችሁት እድር ጋር ያላቸውን አንድነትና  ልዩነት አብራሩ?

ተግባር 2 የአካባቢያችሁን ማህበራዊ ግንኙነት መሰረት በማድረግ የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ በትክክል አሟሉ፡፡






## ምዕራፍ ሰባት

### 1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

ተግባር 1"ጫት መቃምና መዘዙ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን የሀሳብ ግንኙነት ማሳያ የቢጋር ሰንጠረዦች አሟሉ፡፡

ሀ.

ጫት መቃም → ስኳር ያለአግባብ መጠቀም → ______

ለ.

ጫት መቃም → ______ → ለሳንባና ለልብ ህመም ያጋልጣል፡፡

ሐ.




ተግባር 2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች "ጫት መቃምና መዘዙ "በሚለው ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡

ሀ. "ጫት መቃምና መዘዙ"ከሚለው ምንባብ ከእያንዳንዱ አንቀጽ ውስጥ ዋና ሀሳቡን የያዘ አንድ ዓረፍተነገር ለይታችሁ ማውጣት ጻፉ፡፡

ለ. "ጫት መቃምና መዘዙ"ከሚለው ምንባብ ካወጣችኋቸው ዋና ዋና ሀሳቦች ውስጥ አንዱን ወስዳችሁ በምክንያትና ውጤት ስልት በራሳችሁ አገላለጽ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

2ኛ ሳምንት 4ኛ ቀን

ተግባር 1 የሚከተለውን የቢጋር ሰንጠረዥ ምንባቡን መሰረት በማድረግ በትክክል አሟሉ፡፡






ተግባር 2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡

ሀ. ሱሰኝነት ማህበራዊ ተቀባይነትን ሊያሳጣና ለማህበራዊ ህይወት እንቅፋት ሊሆን የሚችለው እንዴት እንደሆነ አብራሩ?

ለ. ጫት መቃም ከግለሰብ አልፎ ለሀገር እድገት ፀር የሚሆነው እንዴት ነው?

3ኛ ሳምንት 7ኛ ቀን

ተግባር 1 የሚከተለውን የቢጋር ሰንጠረዥ ምንባቡን መሰረት በማድረግ አሟሉ፡፡

ተግባር 2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡

ሀ. ለሱስ ተገዢ የሆኑ ሰዎች ምን ምን ዓይነት ችግሮች ያጋጥሟቸዋል?

ለ. በሱስ ውስጥ የገቡ ሰዎች ራሳቸውን እንዴት ነጻ ማውጣት እንደሚችሉ በተግባር አንድ ያቀረባችኋቸውን የመፍትሔ ሀሳቦች በራሳችሁ አገላለጽ አብራሩ፡፡

ሐ. "ራስማወቅ ከሱስ ነጻ ለመሆን ይረዳል፡፡"ራስን ማወቅ ኤች.አይ.ቪን ለመከላከል ይረዳል፡፡"በሚሉት አገላለጾች የተሰመረበትን ሀረግ በማነጻጸር አብራሩ፡፡

መ. በሱስ የተጠመዱ ሰዎች ራሳቸውን ከሱስ ነጻ ባያደርጉ ምን ችግር ይደርስባቸዋል ብላችሁ ታስባላችሁ?

ሠ. በምንባቡ በ7ኛው አንቀጽ ከሱስ ነጻ ያደረጉ ሰዎች የሚያገኛቸውን ጠቀሜታዎች በተመለከተ መስማማት አለመስማማታችሁን በምክንያት ግለጹ፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

## 1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

ተግባር አንድ:- ምንባቡን መሰረት በማድረግና የምልከታ ንባብን በመጠቀም የሚከተለውን

የጊዜ ሰሌዳ በትክክል አሟሉ፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ነሃሴ 12 ቀን 1832 ዓ.ም.እቴጌ ጣይቱ ከአባታቸው ከደጃዝማች ብጡልና ከእናታቸው ከወይዘሮ የውብዳር በደብረታቦር ከተማ ተወለዱ፡፡ → | ሚያዚያ ወር 1869ዓ.ም → | ሚያዚያ 25 ቀን 1875ዓ.ም → | ጥቅምት 27 ቀን 1882 ዓ.ም → | የየካቲ ት 23 ቀን 1888ዓ.ም → | የካቲት 4 ቀን 1990 ዓ.ም |

ተግባር 2፡-ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ አጭር መልስ ስጡ፡፡

ሀ. እቴጌ ጣይቱ ትልቅ ጀብድ በመፈጸም ድል ያደረጉበት ቦታ ምን ይባላል?

ለ. እቴጌ ጣይቱ ለጦርነት ሲዘምቱ ስንት እግረኛ ጦርና ፈረሰኞች ነበሯቸው?

ሐ. እቴጌ ጣይቱ "ውሉን ከመቀበል ጦርነትን እመርጣለሁ" ሲሉ ወስነዋል፡፡እናንተ ብትሆኑ ሌላ ምን ዓይነት አማራጭ ትወስዱ ነበር?ለምን?

መ. እቴጌ ጣይቱ ያንን የጦርነት ስልት ባይቀይሱ ኖሮ ምን ሊፈጠር ይችል ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ?

ሠ. ከምንባቡ የተማራችሁት ቁም ነገር ምንድነው?

2ኛ ሳምንት 4ኛ ቀን

ተግባር 1 "የሀገር ፍቅር መገለጫዎች"የሚለውን ሀሳብ መነሻ በማድረግ በዙሪያው ያሉትን የቢጋር ሠንጠረዦች በምንባቡ መሰረት አሟሉ፡፡




ምዕራፍ ስምንት ተግባር 2 ለሚከተሉት ጥያቄዎች የተብራራ መልስ ጻፉ፡፡

ሀ. የሀገር ፍቅር ስሜትን ለመግለጽ ከአርበኝነት ተግባርና ከበጎ አድራጎት ተግባር የትኛው የተሻለ ይመስላችኋል?ለምን?

ለ. በዓለም የውድድር አደባባዮች ተሰልፈው ድል ማድረግ የተሳናቸውን አትሌቶች የሀገር ፍቅር ስሜት የላቸውም ማለት ይቻላል? ለምን?

3ኛ ሳምንት 7ኛቀን

ተግባር 1 "ማህበረሰብን ማገልገል" የሚለውን ምንባብ ለመረዳት ያገዟችሁን ጥያቄዎች መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት በማዘጋጀት እርስበርሳችሁ ተጠያየቁ፡፡

ተግባር 2 በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡

ሀ. የበጎ አድራጎት ስራ መስራት ፋይዳው ምንድነው?

ለ.የዚህ ጽሁፍ ጸሀፊ ስለማህበረሰብ አገልግሎት ያለው/ያላት አመለካከት ምን

ይመስላችኋል?

ሐ. ተመራማሪዎች ከሚሰጡትና የሀገር ሽማግሌዎች ከሚሰጡት ማህበረሰባዊ አገልግሎት

የተሻለው የትኛው ይመስላችኋል?ለምን?

## ምዕራፍ ዘጠኝ

### 1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

ተግባር 1 ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ በቫይረስ ብቻ የሚመጣ በሽታ የቱ ነው?

ሀ. ቲቢ  ለ. ጉንፋን  ሐ. ተቅማጥ  መ. ወባ

1. የማንቀጥቀጥ፣የማቃገርገት፣የማቅለሽለሽና የማስመለስ ምልክቶች የሚታዩባቸው ሰዎች በምን የተያዙ ይመስላችኋል?

ሀ. ኤች.አይ.ቢ.  ሐ. በማጅራት ገትር

ለ. ለቲቢ  መ. በወባ

4. ከሚከተሉት መካከል የተቅማጥ በሽታ መተላለፊያ መንገድ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የንጽህና ጉድለት　　　　ሐ. ቫይረስ

ለ. የትንኝ ንክሻ　　　　መ. ትንፋሽ

ተግባር 2 ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ጻፉ፡፡

ሀ. የማጅራት ገትር በሽታ የተኛውን የአካል ክፍል ያጠቃል?

ለ. በባክቴሪያ አማካኝነት የሚመጡ በሽታዎችን ዘዝሩ፡፡

ሐ. የትክትክ በሽታ ከጉንፋን በሽታ የሚለየው በምንድነው?

መ. በኤች.አይ.ቪ./ኤድስና አባላዘር በሽታ መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድነው?

ሠ. በአካባቢያችሁ በጣም ተደጋግሞ የሚከሰት ተላላፊ በሽታ ምንድነው? ይህን በሽታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የአካባቢያችሁ ኗሪዎች ምን ማድረግ ያለባቸው ይመስላችኋል?

2ኛ ሳምንት 4ኛ ቀን

ተግባር 1 ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ጻፉ፡፡

1. ከቲቢ. በሽታ ሙሉ በሙሉ ከተፈወሱት መካከል በመቶኛ ከፍተኛው ቁጥር የታየው በየትኛው ዓመት ነው?

ሀ. 2003ዓ.ም　　ለ. 2004 ዓ.ም　　ሐ. 2005 ዓ.ም　　መ. 2006ዓ.ም

2. የቲቢ. በሽታ ህክምና ከወሰዱት መካከል አነስተኛ ቁጥር የታየው በየትኛው ዓመት ነው?

ሀ. 2003ዓ.ም　　　　ሐ. 2005ዓ.ም

ለ. 2004ዓ.ም　　　　መ. 2006ዓ.ም

ተግባር 2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡

ሀ. የቲቢ. በሽታን እንዴት መከላከል ይቻላል?

ለ. የሳንባ ቲቢ. ዋና ምልክት ምንድነው?

ሐ. የሳንባ ቲቢ. በሽታ በምን በምን ይተላለፋል?

መ.የፀረ ቲቢ. መድሃኒቶችን በተለመደ ቲቢ.ና ባልተላመደ ቲቢ. መካከል ምን ልዩነት አለ?

ሠ. "የቲቢ. በሽታን መከላከልና መቆጣጠር ይቻላል " ማለት ምን ማለት ነው?

ረ. የቲቢ. በሽታ ስርጭት መጠን በግራፉ ባለው መረጃ ዓይነት የሚቀጥል ከሆነ ወደፊት ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?

3ኛ ሳምንት 7ኛ ቀን

ተግባር 1 የሚከተለውን የቢ.ጋር ሰንጠረዥ በምንባቡ መሰረት በትክክል አሟሉ፡



ተግባር 2 በአረፍተነገሮች ውስጥ ለቀረቡት ክፍት ቦታዎች ተስማሚ ቃል (ሀረግን) በመምረጥ

አሟሉ፡፡

| | |
|---|---|
| አትክልት | ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች |
| በሽታ | |
| ጀርሞች/ተህዋስያን | መከላከል |

ሀ. የእናት ጡት ወተት በተገቢው የተመገቡ ህጻናት_________የመቋቋም አቅም አላቸው፡፡

ለ. ብርቱካን፣አቦካዶ፣ማንጎ የመሳሰሉትን ፍራፍሬዎችና ሠላጣ፣ቲማቲም የመሳሰሉትን_________________አጥቦ መመገብ ያስፈልጋል፡፡

ሐ. የተላላፊ በሽታ ----------በመጸዳጃ ቤት ቆሻሻ ውስጥ በፍጥነት ስለሚረቡ በቀላሉ እጃችንን ሊበክሉ ይችላሉ፡፡

መ. ከፋብሪካና ከየቤቱ የሚወጡ ----------በተገቢው መንገድ መወገድ አለባቸው፡፡

ሠ. ተላላፊ በሽታዎች ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት አስቀድሞ--------ያስፈልጋል፡፡

## ምዕራፍ አስር

### 1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

ተግባር 1 በተጻፈና ባልተጻፈ ግጥም መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በተመለከተ ከዚህ በታች የቀረበውን ቢጋር በደብተራችሁ ላይ አዘጋጁ፡፡




ተግባር 2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡

ሀ. በፉከራ ግጥምና በእርሻ ግጥም መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድነው?

ለ. "በእርሻ ግጥም"ና "በፋኖስና ብርጭቆ" በሚል ርዕስ በቀረበው ግጥም መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድነው?

ሐ. ፋኖስና ብርጭቆ"በሚል ርዕስ ከቀረበው ግጥም የተማራችሁትን ቁም ነገር ግለጹ፡፡

2ኛ ሳምንት 4ኛ ቀን

ተግባር 1 ለሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. በልጆች ጨዋታ የቃላዊ ግጥም ተደጋጋሚ ስንኞችን ለይታችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. በልጆች ጨዋታና በቀረርቶ ግጥሞች መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድነው?

ሐ. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውንና በግጥም የሚቀርቡ የልጆች ጨዋታዎችን ስማቸውን ተናገሩ፡፡

ተግባር 2 ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላዊ ግጥሞች ውስጥ ሃሳቡን አጉልቶ ለማሳየት የሚያስችለውን ቃል ወይም ሀረግ መሰረት በማድረግ መልዕክቱን በጽሁፍ ግለጹ፡፡

ሀ. በርዬ አንተናኔ የወረድንበቱ፣

ከካራ ይብሳል የድንጋይ ስለቱ፡፡

ለ. በርዬ አሸምድ ጎናቴ አሸምድ፣

ተሸከርክር እንደአየር አድርገው አመድ፡፡

ሐ. በሬዬ እንዳተ እሚዞር የሚሽከረከር፣

አያ እንዳንተ እሚዞር የሚሽከረከር፣

እንዝርትም አይገኝ ከፈታይ መንደር፡፡

መ. በሮች ጥቋቁር ገበሬው ሙጫ፣

ማን ይለቀዋል እርፉ ቢንጫጫ፡፡

3ኛ ሳምንት 7ኛ ቀን

ተግባር ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላዊ ግጥሞቹ መሰረት በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡

ሀ. ከ"ሀ" እስከ" ረ" የቀረቡት ግጥሞች እያንዳንዳቸው ምን አጋጣሚዎችን መሰረት በማድረግ የተገጠሙ ይመስላችኋል?

ለ. ከ"ሀ" እስከ"ረ"የቀረቡት ግጥሞች እያንዳንዳቸው የቀረቡበትን ስሜት አብራርታችሁ ጻፉ፡፡

ሐ. ከሚከተሉት ስንኞች የተረዳችኋቸውን ሀሳቦች በዝርው ጽሁፍ ግለጹ፡፡

- ሥራ እንደኮሶ እየመረረው፣

  ጠቅልሎ መጉረስ ማን አስተማረው፡፡

- አህያ መጣች ተጭና ሞፈር፣

  ቅቤ እንደጭቃ እህል እንደ አፈር፡፡

## አባሪ አራት

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በ2010 ዓ/ም ሁለተኛ ወሰነ ትምህርት በተመረጡት የአዲስ አበባ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ፡-

**ውድ መምህር/ት!**

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል የክፍል ደረጃ ተዘጋጅቶ በ2008ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ምን እንደሚመስል ከመምህራን መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡ ጥናቱ ግቡን ይመታ ዘንድ በመጠይቁ የተካተቱትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ገንቢ የሆነ አስተያየትዎን በመሙላት ይተባበሩኝ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

ውድ ጊዜዎን መስዋዕት በማድረግ ለሚያደርጉልኝ ቀና ትብብር በቅድሚያ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** ሀ. በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡

ለ. ጥናቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ የእርስዎ ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ ትክክለኛ መረጃ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

ሐ. የመጠይቁን ጥያቄዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር በመመካከር ቢሞላ በጥናት ውጤት ላይ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር ብቻዎትን ይሙሉት፡፡

መ. ከቀረቡት ጥያቄዎች በተጨማሪ ሀሳብ ካለዎት በመጠይቁ መጨረሻ ላይ ማስፈር ይችላሉ፡፡

**ክፍል አንድ፡- አጠቃላይ መረጃ**

ጾታ ____________________

ዕድሜ ____________________

የትምህርት ደረጃ_______________

የተመረቁበት የትምህርት ዓይነት_____________

በዋናነት _________________________________

በንዑስ_____________________________

የሰለጡነበት ልዩ መስክ (አሁን ያሉበት ደረጃ)

ዲፕሎማ

በመጀመሪያ ዲግሪ

በሁለተኛ ዲግሪ

የአገልግሎት ዘመን

በዲፕሎማ-----------------ዓመት/ታት

በዲግሪ--------------------ዓመት/ታት

ሌላ ካለ ይገለጽ---------------------------

**ክፍል ሁለት፡- የምርጫ ጥያቄዎች**

***መመሪያ አንድ፡-*** ለእያንዳንዱ ጥያቄ በመመዘኛ መስፈርቶቹ ላይ በተቀመጡት መግለጫዎች አማካኝነት ተገቢ ነው የሚሉትን መልስ የ"X"ን ምልክት በማስቀመጥ ያመልክቱ፡፡

የፍረጃ ደረጃዎች፡-

በጣም ከፍተኛ =1

ከፍተኛ =2

መካከለኛ =3

ዝቅተኛ =4

በጣም ዝቅተኛ =5

| ተ.ቁ. | ዝርዝር ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በተማሪው መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያላቸው እገዛ | | | | | |
| 2 | ይዘቶቹ አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ያላቸው አመችነት | | | | | |
| 3 | ለአንብቦ መረዳትና ለመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ እንዲሆኑ የተዘጋጁት መልመጃዎች የትምህርቱን ዓላማ የማሳካት ብቃታቸው | | | | | |
| 4 | የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ተማሪዎቹ ቋንቋውን በሚገባ እንዲካኑ ለማድረግ ያላቸው አቅም | | | | | |
| 5 | መጽሀፉ የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያስችሉ ይዘቶችን አሟልቶ የመያዝ ሁኔታ | | | | | |
| 6 | የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ትምህርት ለደረጃው ተስማሚነታቸው | | | | | |
| 7 | የንባብ ክሂል መልመጃዎች ለክሂሉ ማስተማሪያ የሚሆኑ ብልሃቶችን ትኩረት የማድረግ ሁኔታ(ለምሳሌ፡-ጥያቄ መጠይቅ፣ማብራራትና መተርጎም፣ ማጠቃለል፣ አንድምታና ትንበያ)፡፡ | | | | | |
| 8 | አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርቡት ይዘቶች ከተማሪዎች ህይወት ጋር ያላቸው ግንኙነት | | | | | |
| 9 | በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አንብቦ የመረዳትን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ተገቢነት | | | | | |
| 10 | ለክሂል መልመጃዎቹ ተገቢ የሆኑ መመሪያዎች የመስጠት ሁኔታ | | | | | |
| 11 | ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች አካያ ሲታይ በመጽሀፉ ውስጥ ለአንብቦ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | መረዳትና ለመጻፍ ክሂል የተሰጠው ቦታ | | | | | |
| 12 | የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ተግባራት ዳራዊ እውቀትን ከግንዛቤ ውስጥ የማስገባታቸው ሁኔታ | | | | | |

**ክፍል 3፡- ክፍት ጥያቄዎች**

***መመሪያ ሁለት፡-*** ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢ ነው የሚሉትን መልስ በተሰጠው ክፍት ቦታ ያስፍሩ፡፡ ምናልባት የተሰጠው ክፍት ቦታ በቂ ካልሆነ በመጨረሻ ላይ ባለው ነጻ ወረቀት ላይ መጠቀም ይችላሉ፡፡

13. የተማሪው መጽሐፍ ፣የመምህሩ መምሪያና መርሃ ትምህርቱ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች እርስበርስ ተያይዘው እንዲቀርቡ እገዛ በማድረግ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለመምራት ምን ያህል አጋዥ ናቸው?

____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________

14. አንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ተቀናጅተው ቢቀርቡ በተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ላይ ለውጥ ያመጣል ብለው ያስባሉ? ከሆነ እንዴት?____________________________

____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________

መጠይቁን በመሙላት ላደረጉልኝ ትብብር ምስጋናየ የላቀ ነው!

# አባሪ አምስት

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ትምህርት ቅንጅታዊ አቀራረብ ምልከታ ማከናወኛ ቅጽ (Check list)

አጠቃላይ መረጃ፡-

ምልከታ ቁጥር ----------------------

ቀን ------- ወር ------ ዓም. ---

የትምህርት ቤቱ ስም -------------------

ትምህርቱ የተጀመረበት ጊዜ---------

ትምህርቱ የተጠናቀቀበት ጊዜ-------------

ሴክሽን ------------------

ክፍለ ጊዜ------------------

የተማሪ ብዛት--------------------------

የእለቱ ትምህርት ርዕስ--------------------

የእለቱ የትምህርት ዓላማ(ዎች)፡-

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________::

መመሪያ አንድ፡- ቀጥሎ ከቀረቡት መስፈርቶች መካከል አንዱን በመምረጥ በተሰጠው መልስ መስጫ ቦታ ላይ ትክክለኛ መልሱን የ(X) ምልክት በማድረግ ማሳየት፡፡

የፍረጃ ደረጃዎች፡-

.በጣም ከፍተኛ =1

ከፍተኛ =2

መካከለኛ =3

ዝቅተኛ =4

በጣም ዝቅተኛ =5

| ተ.ቁ. | የመከታተያ ነጥብ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የክፍለ ጊዜው ይዘት አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀት ያለው እገዛ | | | | | |
| 2 | የክፍለ ጊዜው ይዘት አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ | | | | | |
| 3 | አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርበው ይዘት ከተማሪዎች ህይወት ጋር ያለው ግንኙነት | | | | | |
| 4 | መ/ሩ (/ሯ) ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 5 | አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚረዱ ብልሃቶችን የመተግበር ሁኔታቸው ለምሳሌ፡-(ጥያቄ መጠየቅ፣መተንበይና መገመት፣ማብራራትና መተርጎም፣ማጠቃለል) | | | | | |
| 6 | መ/ሩ (ሯ) አንብቦ መረዳትን ከመጻፍ ክሂል ጋር ትኩረት ሰጥተው የማቀናጀት ሁኔታቸው | | | | | |
| 7 | መ/ሩ (/ሯ) ተማሪዎች አንድን ምንባብ ካነበቡ በኃላ በራሳቸዉ አባባል እንዲፅፉ የማድረግ ሁኔታቸው | | | | | |
| 8 | መ/ሩ(ሯ)ተማሪዎች የሚፅፏቸውን ፅሁፎች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 9 | መ/ሩ(ሯ) ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሑፍ እንዲገልፁ በቂ ጊዜ የመስጠት ሁኔታ | | | | | |
| 10 | መ/ሩ(ሯ) ከተማሪ መፅሀፍ ውጭ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት እና የመጻፍ ፍላጎት የሚያነሳሳ ይዘት የማካተት ሁኔታቸው | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | መ/ሩ(ሯ) የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ የማድረጋቸው ሁኔታ | | | | | |
| 12 | የክፍል ስራዎች አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ብቃት | | | | | |
| 13 | መ/ሩ(ሯ) የሚሰጧቸው የቤት ስራዎች (መልመጃዎች) የአንብቦ መረዳትንና የመፃፍ ክሂልን በማቀናጀት የሚሰሩ ናቸው፡፡ | | | | | |

14. መ/ሩ (ቷ) አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማቀናጀት ይሞክራሉ?

____________________________________________________

______(ከሞከሩ በምን በምን ስልት?)______________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

____________________፡፡

15. መ/ሩ (ቷ) ከመማሪያ መጻሐፉ ላይ ካለው በተጨማሪ የቋንቋ ክሂሎችን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎችና ብልሃቶች ምንድ ናቸው?

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

______________________________________________፡፡

16. አጠቃላይ በመማር ማስተማር ሂደቱ የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ አጠር ያለ ግላዊ አስተያየት

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

_______________________________________፡፡

# አባሪ ስድስት

## ለመማሪያ መጽሐፉ አስማምቶ አዘጋጆች የቀረበ ቃለ መጠይቅ

1. ከዚህ በፊት መጽሐፍ በማዘጋጀት ወይም በማሻሻል ስራ ተሳትፎ ነበረዎ?

2. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱን የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂል የአቀራረብ

   ስልት በተመለከተ ምን አይነት አዘገጃጀት ተጠቀሙ?

3 ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች አንጻር ሲታይ በመጽሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳትና ለመጻፍ ክሂል የተሰጠው ቦታ ምን ይመስላል? ቢገልጹልኝ፡፡

4. አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን አቀናጅቶ ማቅረብ ምን ዓይነት ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለው ያስባሉ?

5. የአንብቦ መረዳት ተግባራት ከመጻፍ ክሂል ጋር የይዘት ቅንጅት አላቸው ብለው ያምናሉ? ከሆነስ በምን መልኩ?

6. አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚረዱ ብልሃቶች ምን

   ያህል ተካተዋል ብለው ያምናሉ?

7.የአንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በተመለከተ የቀረቡትን ይዘቶች ከተማሪዎች

   ፍላጎት፣ዳራ፣ ችሎታ ጋር የተዛመዱ ናቸው ብለው ያምናሉ? ከሆነ እንዴት?

8. የንባብ ክሂልን ለማስተማር ሲታሰብ ሌሎችም ክሂሎች ይከተላሉ? ይህ የቋንቋ

   ክሂሎችን ለማቀናጀት በቂ ነው ይላሉ? ለምን?

9. ስለአንብቦ መረዳትና ስለ መጻፍ ክሂል ተግባራት ቅንጅት የሚሉት ነገር ካለ?

   ቢገልጹልኝ፡፡

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስምና ፊርማዬ የተጠቀሰው የድህረ ምረቃ ተማሪ ይህ ጥናት የራሴ ስራ መሆኑን እና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሁፎች በሙሉ በትክክል የተጠቀሱ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ፡-እመቤት እሸቴ

ፊርማ፡-__________

አድራሻ፡-ደብረ ብርሃን ዩኒቨርስቲ፣የማህበራዊ ሳይንስና ስነ-ሰብዕ ኮሌጅ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል